For more spiritual book join our official telegram channel
https://t.me/amharicspritualbooks

# የጸሎት ተጋዳይ ምስጢራት

ትርጉም - ተስፋዬ መስፍን

እርማት - የማነብርሃን እንዳለ(ፓስተር)

የኮምፒውተር ጽሑፍ - ትዕግስት ሹመቴ

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
Printed by Yemanberehane Endale
Gospel Center Library
2012

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
SECERETS OF A PRAYER WARIOR
DEREK PRINCE
ከሚለው መጽሐፍ ነው

ለማንኛውም ጥያቄና አስተያየት
በሚከተለው አድራሻ ያግኙን
P.o.box 21980
Tel. 002519220701
002511270941(Res)
E– mail ora. International @ethionet .et
Addis Ababa
Ethiopia

# ማውጫ

| ርእስ | ገፅ |
|---|---|
| መግቢያ | 4 |
| 1. የካህናት መንግስት | 9 |
| 2. ለጸሎት መልስ መሠረታዊ ሁኔታዎች | 19 |
| 3. የመንግስት ጸሎት በምድር ላይ | 50 |
| 4. አስራ ሁለት የተለያዩ የፀሎት ዓይነቶች | 61 |
| 5. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ | 97 |
| 6. ለመንፈሳዊ ውጊያ መንፈሳዊ መሣሪያዎች | 120 |
| 7. የእግዚአብሔር አቶሚክ መሣሪያ፣ የኢየሱስ ደም | 138 |
| 8. ጾም፣ ለእግዚአብሔር ዓላማ የእኛ ምላሽ | 153 |
| 9. የከበረች ቤተክርስቲያን | 172 |
| ስለ ደራሲው | 197 |

# መግቢያ

ዴሪክ ፕሪንስ የጸሎት ተጋዳይ ነበሩ፡፡ እርግጥ ነው፣ ሌሎች ስጦታዎችና ባህርያትም ነበሩዋቸው፡፡ ከሁሉም የበለጠ ዴሪክ ከ600 በላይ ሪከርድ የተደረጉ መልዕክቶች፣ ወደ 60 የሚጠጉ ህትመት ላይ የዋሉ መጽሐፎች፣ ከ100 በላይ የትምህርቶቻቸው ቅጂ ቪዲዮዎች የነበሩዋቸው በጣም ታዋቂ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ነበሩ፡፡ በጣም ጥልቅ የሆኑ ትምህርቶች ያስተማሩ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ነበሩ፡፡

ዴሪክ ፕሪንስ ሚስታቸውን አፍቃሪ ባል ነበሩ(ከ53 በበለጡ ዓመታት ውስጥ)፣ ሁለቱም ቀድመዋቸው ወደ ክብር ሄደዋል፡፡ የመጀመሪያ ጋብቻቸው ከጌታ በተቀበሉት ድንቅ ምሪት ነበር የተፈጸመው፡፡ በ1945 የመጀመሪያ ባለቤታቸውን ሊዲያን አገቡና ወዲያውኑ ታሳድጋቸው ለነበሩ ስምንት ሴት ልጆች አባት ሆኑ (ዘጠነኛዋ የማደጎ ልጃቸው ጀሲካ ወደ ቤተሰቡ የተቀላቀለችው ዴሪክና ሊዲያ በኬንያ አገልግሎት ላይ በነበሩ ጊዜ ነበር፡፡) የዚህ፣ «ፈጣን ቤተሰብ» አስጋራሚው ገፅታ ዴሬክ ሁሉም በተሟላለት የእንግሊዝ ባህል መባል በሚችል ውስጥ ብቸኛ ልጅ ሆነው ማደጋቸው ሲሆን፣ በዚያ ጊዜ የሰላሣ ዓመት ወንደላጤ ነበሩ፡፡ ከሩት ጋር ትዳር የመሰረቱት በ1978 ሊዲያ ካለፉ ሦስት ዓመት በኋላ ሲሆን፣ ይኸኛውም ቢሆን እንደ መጀመሪያው በሚያስገርም የጌታ ምሪት የተፈጸመ ነበር፡፡

ዴሬክ ፈላስፋና የተዋጣላቸው ምሁርም ነበሩ፤ በምሁራዊ መስክ ያገኙት ክብር ራሱ አንድ ሙሉ ገጽ ይወጣዋል፡፡ ሌላው ለየት ያለ ልምምዳቸው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማለትም ከጌታ ጋር እንደተገናኙ ብዙም ሳይቆዩ በሰሜን አፍሪካ በረሐ በሕክምና ምድብ ማገልገላቸው ነበር፡፡ ዴሬክ ብዙ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገራሉ፡፡ አዲስ ኪዳናቸውን በዋናው ግሪክ ቋንቋ ያነብቡ ነበር፤ በተጨማሪም የዕብራይስጥ ምሁር ነበሩ፡፡ ዕውቀትና የአእምሮ ብሩኅነታቸው ሰፋ ያሉ ቅርንጫፎችን ይሸፍናል፡፡ ምንም እንኳ ይህን እንደ አንድ ተጨማሪ ጉዳይ ባይመለከቱትም በብዙ መንገድ እውነተኛ የሕዳሴ ሰው ነበሩ፡፡



መምህር፣ ደራሲ፣ ባል፣ አባት፣ በብዙ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥና መስራች የሚሉትን የመሳሰሉ የማንነታቸው መገለጫ እንደሆኑ ረጅም ዝርዝሮች ሁሉ፣ በዴሬክ ሕይወትና አገልግሎት የተፈፀሙ የተለያዩ ሁኔታዎችና ስኬቶችን ረጅም ዝርዝሮችም ማቅረብ ይቻላል፡፡ ያም ቢሆን፣ ዴሬክ በዚያ ዝርዝር ደስ እንደማይሰኙ ይታወቃል፤ ምክንያቱም፣ ሕይወታቸው የእርሳቸው ታሪክ ነው ብለው አያስቡም፡፡ ሕይወታቸው የጌታ ታሪክ መሆኑን ነው የሚያምኑት፡፡ ዛሬ በሕይወት ቢሆኑ ኖሮ ዴሬክ በእንዲህ ያሉ ዝርዝሮች ምቾት አይሰማቸውም ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ በየትኛው ገላጭ ዝርዝር ውስጥ ተቀዳሚውን ቦታ መያዝ ያለበት አንዱ፣ ዴሬክ በጸሎት ተጋዳይ መሆናቸው ነው፡፡

በ1970 መጀመሪያዎቹ ዓመታት አንድ መጋቢ ከዴሪክና ከሊዲያ ጋር ምሳ በልቶ እንደነበር ይናገራል፡፡ በምሳውና በጭውውታቸው መሐል አልፎ-አልፎ የዴሬክን ክንዶች ነካ በማድረግ «ለጂምና ጃኒስ መጸለይ እንዳለብን አስባለሁ» ይሉ እንደነበርና ይህም ለእርሳቸው በጣም የተለመደ መሆኑ ያስታውቅ ነበር፡፡ ከዚያ ያቆሙና ለጥቂት ጊዜ ይጸልዩ ነበር፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ፣ «ለፍራንክና ለቤቱ መጸለይ እንዳለብን አስባለሁ» ይላሉ፡፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ዴሬክ ያቆሙና ከሊዲያ ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝ ቀላልና ቀጥተኛ ጸሎት ያደርጋሉ፤ ከዚያ ወደ ጭውውታቸው ይመለሳሉ፡፡ ያ መጋቢ እንደተናገረው ከሆነ እርሱና ባለቤቱ ከተገኙበት በጣም ካልተለመደ የምሳ ግባዣ ዋናው ነበር፤ ሆኖም፣ ደስ በማያሰኝ ሁኔታ አልነበረም፡፡ ጸሎት ለዴሬክና ለሊዲያ፣ በኋላም ለዴሪክና ለሩት ተፈጥሮአዊና የዘወትር ጉዳይ ነበር፡፡

ዴሬክ ፕሪንስ የጸሎት ተጋዳይ ነበሩ፡፡

ዐሬፍት ነገሩ ሲብራራ

ዐረፍተ ነገሩ፣ ለመሆኑ የጸሎት ተጋዳይ ማለት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡ ገላጭ በሆነ መንገድ ለዚያ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በጣም የተሻለው መንገድ ይህን መጽሐፍ ማንበብ ነው፡፡

ለዚህ ጥያቄ መልስ የመስጠቱን ሂደት ስንጀምር ውስብስቡ ጉዳይ

የሚነግው ጸሎት በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ካለበት ሁኔታ ነው። የጸሎት ተጋዳይ በክርስቲያኖች ዙሪያ የተለመደ ሐረግ ሲሆን፣ ግዴለሽ በሆነ ሁኔታ ጣል ይደረጋል። በችኮላና በጥድፊያ፣ በልመናና በመንፈሳዊ እወጃ የሰማይ ደጆችን የሚያንኳኳ ሰውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህን መጽሐፍ ስታነቡ እንደምትመለከቱት ዴሬክ «የጸሎት ተጋዳይነትን» ምንነት በተመለከተ በሚገባ ያልታሰበበት አቋም የላቸውም (ለእንዲህ ዓይነቱ በሚገባ ያልታሰበበት ጉዳይ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ የመዝሙር መሪ በጣም ፈንድቆ በነበረ ጊዜ ፣ «በዚህ ምሽት ደስታ ይሰማኛል የገሃነም እሳትን በአንድ ባልዲ ውሃ ማጥፋት እንደሚቻል ይሰማኛል» በማለት የተናገረው ነው። ከሌሎች ባህርያቶቻቸው በተጨማሪ ግሩም ጨዋታ አዋቂ የነበሩት ዴሬክ በመካከላችን ቢኖሩ ኖሮ በእንዲህ ያለው አነጋገር ከእኛ ጋር አብረው ከልባቸው ይስቁ ነበር። ጸሎትን ወደሚመለከት ርዕሰ ጉዳይ ስንመጣ እርሳቸውን በተመለከተ ብዙ ሌሎች ነገሮች ማለት ቢቻልም በፍጹም ያልታሰበበት አቋም አልነበራቸውም።

ስለ የጸሎት አስደንጋጭ አባባል ተጋዳይነት፣ «በሚገባ ያልታሰበበትን ጉዳይ ይህን ያህል አጥብቀን የምናጠናው ገና በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ዴሬክ ከተናገሩት ነገር ምክንያት ነው። ምናልባት አባባሉ ደስ ላያሰኛችሁ ይችላል።

የምዕራፍ 1 መጀመሪያ አንቀጽ ላይ ዴሬክ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ደፋር የሆነ አባባል ተጠቅመዋል፤ መጀመሪያ ሲያነቡት (ወይም ሲሰሙት … ስለ ጸሎት በሚያስተምሩት ጊዜ ሁሉ ደሬክ ደጋግመው ይናገሩታል) ሰዎች ደስ ላይሰኙ ይችላሉ። እንዲህ ነበር ያሉት፣ «በበኩሌ መጸለይ እወዳለሁ ከዚያ በላይ ግን፣ የጸለይኩትንም አገኛለሁ።»

ያን ዐረፍተ ነገር መጀመሪያ ስንመለከተው ደፋርና ብዙም ባልታሰበበት ሁኔታ የተነገረ ይመስላል። «የጸለይኩትን አገኛለሁ።» ቀጥሎ በሚሰጡት ተስፋ ዴሬክ በጣም ርቀው ይሄዳሉ፤ «ላስተምራችሁ



የምፈልገውም ያንን ነው- እንዴት እንደምትጸልዩና የጸለያችሁበትን እንደምታገኙ » አባባሉ፣ «ሳንቲሞቹን ክተት ከዚያ ከረሜላዎች ታገኛለህ» ከሚለው አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለጸሎት ካላቸው አስተሳሰብ ጋር በአደገኛ ሁኔታ የሚቀራረብ ይመስላል። እግዚአብሔር እሺ እስኪለውና የሚፈልገውን እስኪሰጠው ድረስ የሚለምን፣ የሚለማመጥና እንዲያውም የሚቆጣ ያልተቀጣ ልጅ ምስል ወደ አእምሮአችን ይመጣል። ከስድብ ባልተናነሰ ሁኔታ አንዳንዶች፣ «በሰማይ ያለ ሁሉንም የሚሰጥ» በማለት ይናገራሉ።

በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ እንዲህ ዐይነቶቹ ዝንባሌዎችና አቀራረቦች በዚህ ዘመን በክርስቲያኖችም ዘንድ በጣም የተለመዱ መሆናቸው ነው። ይህ መጽሐፍ በጣም ጠቃሚ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው። ከየምዕራፎቹ እንደምታነቡት ዴሬክ ስግብግብ፣ ራስ ወዳድ ጸሎቶቻችንን መልስ እንደምናገኝ አይደለም የሚያስተምሩት። ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንድንጸልይና እኛ የምንፈልገውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለዘለቄታ የሚፈልገውን እንድናገኝ በዝንባሌያችንና በልምምዳችን ከእግዚአብሔር ጋር ማጣጣም ነው።

«በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፤ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል» በሚለው መዝሙር 37፡4 ላይ ባለው ቃል ይህ ጽንሰ ሐሳብ በሚገባ ተገልጾዋል። በክርስትና እምነት ያሉ አንዳንዶች ይህ ስግብግብ አይነት ጸሎት እንድናቀርብ የሚያበረታታ ጥሪ እንደሆነ ይገምቱ ይሆናል። እንዲያውም ወደ ልባችን ወይም ወደ አእምሮአችን የሚመጡ ጥቃቅን ምኞቶቻችንን ሁሉ እግዚአብሔር ይሰጠናል በሚል መልኩ ብዙዎች ይህን ቃል ተረድተውታል። አንድ የዴሬክ ፕሪንስ አገልግሎት ወዳጅ የሆነ ሰው ሙሉ በሙሉ ዴሬክ በዚህ መጽሐፍ ከሚያስተምሩት ጋር የሚስማማ ግንዛቤ ይዟል። የደረሰበት ግንዛቤ የሚከተለው ነበር- «በጌታ ደስ በመሰኘት የምንጸልይበት ነገር እርሱ ለእኛ ካለው ፈቃድ ጋር የሚስማማ ይሆን ዘንድ ራሳችንን ከእርሱ ልብ እና ፍላጎት ጋር እናጣጥማለን» የሚል ነበር። ይህ ቀደም ሲል ከተመለከትነው ያልተቀጣ ልጅ ምሳሌ በጣም የተለየ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዴሪክ መሟላት ያለባቸው ጉዳዮችን፣ ማዳበር የሚገቡን ልማዶችንና ለጸሎት ሕይወት ስኬት የተረጋገጡ መክፈቻዎችን በጣም ግልጽ አድርገዋል። እነዚህ ሁኔታዎችን ስናሟላ በጸሎታችን ውጤታማነትን እናያለን። እንዲህ ያለ ውጤታማነትን ዴሪክ በህይወት ዘመናቸው አይተዋል። ምክንያቱም ዴሪክ የጸሎት ተጋዳይ ነበሩ።

የጸሎት ሕይወታቸው ሚስጥር ከእንግዲህ ሚስጥር አይደለም። በዚህ መጽሐፍ ዴሪክ በግልጽና በስፋት ያካፍሉናል። በመሠረቱ፣ እንደ አብዛኞቹ የክርስትና እምነት ሚስጥሮች ሁሉ መጀመሪያውኑ ግልጽና በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚታዩ ነበሩ። ሆኖም፣ ባላቸው ስጦታና የራሳቸው በሆነ መንገድ ዴሪክ ከእግዚአብሔር ቃል በማውጣት ግልጽ ያደርጉልናል። ምክንያቱም… ዴሪክ ፕሪንስ የጸሎት ተጋይ በመሆናቸው ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን እውነቶች ተግባራዊ በማድረግ እናንተም የጸሎት ተጋዳዮች እንደምትሆኑ እንተማመናለን።

የዴሪክ ፕሪንስ አገልግሎት ዓለም አቀፍ ሕትመት ቡድን



1

# የካህናት መንግስት

## ኢየሱስ ለአባቱ ለእግዚአብሔር መንግስትና ካህናት አደረገን።(ራዕ 1፡6)

በዚህ መጽሐፍ በጣም ከምወዳቸው ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን ማለትም ጸሎትን የሚመለከት ርዕሰ ጉዳይ አነሣለሁ። ለአንዳንድ ሰዎች ጸሎት አታካች ሃይማኖታዊ ተግባር ሊመስላቸው እንደሚችል አስባለሁ። በበኩሌ ግን መጸለይ እወዳለሁ ከዚያም በላይ የጸለይኩበትን ነገር አገኛለሁ። የማስተምራችሁም እንዴት እንደምትጸልዩና የጸለያችሁትን ነገር እንደምታገኙ ነው። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ፣ እንድንጸልይ እንደሚወድ በመረዳት መጀመር ይኖርብናል። ምናልባትም ብዙዎቻችን ስለእግዚአብሔር ያለንን አሉታዊና ደስ የማይል አመለካከት መለወጥ ይኖርብን ይሆናል። እኔ ራሴም እንዲህ ያለ አመለካከት እንደነበረኝ አውቃለሁ። እንዲህ ያሉ አመለካከቶች በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል ይገቡና ጸሎቶቻችንን ያሰናክሉብናል።

ልጅ በነበርኩበት ጊዜ በብሪታኒያ አዳሪ ትምህርት ቤት ረጃጅምና አታካች ዓመታት ማሳለፌን አስታውሳለሁ፣ እግዚአብሔር አንድ የትምህርት ቤት መምህር መስሎ ይታየኝ ነበር። እውነት ለመናገር ለትምህርት መምህራን ይህን ያህል ፍቅር አልነበረኝም፤ ሆኖም እግዚአብሔርንም ቢሆን የማየው፤ ከረጅሙ ኮሪደር መጨረሻ ወንበርና ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ እንዳለ መምህር ነበር የማየው። ይህን መምህር ለማናገር የምትፈልጉ ከሆነ የእግራችሁ ኮቴ እንኳን እንዳይሰማ እየተሳቀቃችሁ እርሱ ወዳለበት መሄድ ይኖርባችኋል። የቱንም ያህል ጥንቃቄ ብታደርጉ የወለሉን ጣውላ በረገጣችሁ ቁጥር እየተንጫጫ መንገድ ላይ መሆናችሁን ያስታውሳችኋል። ከዚያ ቀስ ብላችሁ

በሩን ታንኳኳላችሁ፤ አንድ ጎርነን ያለ ድምፅ እንድትገቡ ይነግራችኋል፤ ምናልባትም ስላደረጋችሁት ወይም ማድረግ ሲገባችሁ ስላላደረጋችሁት ነገር መቆጣት ይጀምር ይሆናል።

ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መጸለይ እንድችል፤ እግዚአብሔርን በተመለከተ ያለኝ ምስል መለወጥ ነበረበት። ብዙዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው ምስል በጣም ሩቅ ቦታ ያለና ማንም እንዲያውከው የማይፈልግ፣ ምናልባትም የሚቆጣን ዓይነት እንደሆነ ተረድቻለሁ፤ ስለሆነም የተሻለው መንገድ በተቻለ መጠን ከእርሱ መራቅ ነው።

እግዚአብሔርን በተመለከተ ግን በፍጹም ይህ አይደለም። ወደ እርሱ ስንመጣ ይቀበለናል እንጂ በቁጣ አያመናጭቀንም። የሚለን ነገር ቢኖር እንኳ «ለረጅም ጊዜ ስጠብቃችሁ ነበር» የሚል ነው የሚሆነው።

እንዴት ደስ የሚል አቀባበል!

ወደ እርሱ ስንመጣ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደሚቀበለን መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግሩም ምሳሌ ይሰጣል። ከቤቱ ኮብልሎ የነበረ፣ ኑሮውን ሁሉ ያባከነ፣ በመከራ አረንቋ የዘቀጠና ብቅ ጥልቅ በማለት ላይ ስላለ አባካኝ ልጅ ኢየሱስ የተናገረው በጣም የታወቀ ምሳሌ ነው። ይህ ወጣት ያለውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ *«ወደ ቤት መመለስ ይሻለኛል። ምናልባት አባቴ ይቀበለኝ ይሆናል። እንደ ልጁ እንዲቀበለኝ ልጠይቀው አልችልም፤ ነገር ግን ከአገልጋዮቹ እንደ አንዱ እንዲቀበለኝ እጠይቀዋለሁ»* የሚል ሐሳብ ወደ ልቦናው መጣ። ይህ አባት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደተቀበለው ልብ እንድታደርጉ እፈልጋለሁ።

> ስለዚህም ተነስቶ (ልጁ) ወደ አባቱ ሄደ። ነገር ግን እርሱ
> ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አይቶት ራራለት፤ ወደ እርሱም
> እየሮጠ ሄዶ ዐቅፎ ሳመው።ሉቃ 15:20

ወደ ልቦናው ተመልሶ ወደ ቤቱ መመለስ ሲወስን ይህ ወጣት እንዴት አይነት አቀባበል እንደተደረገለት አያችሁ? «ከአገልጋዮችህ አንዱ አድርገኝ»



ብሎ ለመናገር እንኳ እድል አላገኘም፤ ምክንያቱም አባቱ እየሳመውና እንደልጅ እየተቀበለው ነበር።

በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እግዚአብሔር እንደሚቀበለን በጣም ጥሩ ምሳሌ ነው። በቁጣ አያመናጭቀንም፣ አይወቅሰንም፣ ፊቱ ጨፍጋጋና ሊቀርቡት የማይቻል አይደለም። አፍቃሪና ጥሩ አቀባበል ያለው ቸር ነው። ያዕቆብ 1:5 እግዚአብሔር፣ «ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጥ» እንደሆነ ይነግረናል። ስለጸሎት ስታስቡ ይህን በአእምሮአችሁ ያዙ። ስለ እግዚአብሔር የዚያ ዓይነት ዓመለካከት ሲኖረን፣ የምንጸልይበት መንገድ በፍጹም ይለወጣል።

ኢየሱስ የመጣው ለሰው ልጅ እግዚአብሔርን በመወከል ነበር፤ ጸሎትን በተመለከተ ኢየሱስ ያስተማረው እንደሌሎች ትምህርቶቹ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ቀና ነው። በተራራው ስብከቱ የተናገረውም ይህን ነው።

> ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፣ ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ፣ በሩም
> ይከፈትላችኋል። የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤ የሚፈልግም
> ያገኛል፤ ለሚያንኳኳም በሩ ይከፈትለታል። ማቴዎስ 7:7-8

እነዚህ ሦስት ቀና ዐረፍተ ነገሮችን ልብ አድርጉ። የሚለምን ይሰጠዋል፤ የሚፈልግ ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል። ማቴ 21:22 ላይ ኢየሱስ፣ «እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ» ብሏል። እንደ ገና ማርቆስ 11:24 ላይ ኢየሱስ፣ «ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁ አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል» ብሏል። እንግዲህ ከዚህ የበለጠ ሁሉንም የሚያጠቃልል ምን ሊኖር ይችላል? ማንኛውንም። የትኛውንም።

በዩሐንስ ወንጌል ለደቀመዛሙርቱ በሰጠው መደምደሚያ ትምህርት እንደገና እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ እንደሚሰጥ ኢየሱስ ሦስት ጊዜ አረጋግጦልና። እነዚህ ቃሎችን ስሙ -

> አብ ወልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ
> አደርገዋለሁ፤ ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ
> እኔ አደርጋለሁ። ዩሐ 14:13-14

*__ማንኛውን ነገር ብትለምኑ አደርግለሁ።__* ምንኛ ሁሉን የሚያካትት ነው? በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፣ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ ይሰጣችኋልም። ዩሐንስ 15፡7

*__የምትገልጉትን ሁሉ ለምኑ።__* ከዚህ የበለጠ ምን ማለት ይቻላል? እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ለምኑ ትቀበላላችሁ፤ ደስታችሁም ሙሉ ይሆናል። ዩሐንስ 16፡24

*__ለምኑ ትቀበላላችሁ።__* የጸሎታችንን መልስ በመቀበል የሚገኝ የተለየ ዓይነት ደስታ አለ። ኢየሱስ ያ ደስታ እንዲኖረን ይፈልጋል፤ ስለዚህም «ለምኑ» ይለናል።

ሁሉን የሚችል፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣ የመላው አጽናፈ ዓለም ገዢ፣ በግል የምናቀርበውን ጸሎት እንደሚሰማ፣ እንዲያደርግልን የለመንነውን እንደሚያደርግልን ማወቅ አንድ ሰው ሊኖረው ከሚችለው ድንቅ ልምምድ በጣም የሚበልጥ ነው።

በቃል ብቻ ሳይሆን፣ በምሳሌነትም ጭምር ኢየሱስ ያስተማረው ይህንኑ ነው፤ ምሳሌነቱ ዛሬም ቀጥሏል። እስቲ በዚህ የጸሎት አቅጣጫ እንዴት ኢየሱስን መከተል እንደምንችል እንመልከት።

ቀጣይ የኢየሱስ ጸሎት ሕይወት

ኢሳያስ 53፡12 በጣም የታወቀውንና ክቡር የሆነውን የኢየሱስን ቤዛነት ሥራ ያቀርባል። ቁጥሩ እንዲህ ይላል።

> ስለዚህ ድርሻውን ከታላላቆች ጋር እሰጠዋለሁ፤ ምርኮውን
> ከኃያላን ጋር ይካፈላል፤ እስከሞት ድረስ ሕይወቱን
> አሳልፎ በመስጠቱ፣ ከክፉ አድራጊዎችም ጋር በመቆጠሩ የ
> ብዙዎችን ኃጢአት ተሸከመ ስለ ዐመፀኞችም ማለደ።
> ኢሳይያስ 53፡12

እዚህ ላይ አራት የኢየሱስ ሥራዎች መስፈራቸውን ታያላችሁ።

*__እስከሞት ድረስ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ።__* ዘሌዋውያን 17፡11 «የፍጡር



ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና» ይላል። እያንዳንዱ የደሙን ጠብታ ባፈሰሰ ጊዜ ኢየሱስ እስከ ሞት ድረስ ሕይወቱን አፈሰሰ።

*__ከክፉ አድራጊዎች ጋር ተቆጠረ።__* የተሰቀለው ከሁለት ወንበዴዎች ጋር ነበር።

*__የብዙዎችን ኃጢአት ተሸከመ።__* ለሁላችንም የኃጢአት መሥዋዕት ሆነ። ስለ ዐመፀኞች ማለደ። መስቀል ላይ ኢየሱስ እጅግ በጣም ከባዱን ምልጃ አደረገ። «አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» አለ (ሉቃስ 23፡34) «እነርሱ ላይ የታሰበው ፍርድ እኔ ላይ ይሁን» ማለቱም ነበር። እንዳለውም ሆነ።

ሆኖም የኢየሱስ የጸሎት ሕይወት በሞቱና በትንሣኤው አላበቃም። የዕብራውያን መልእክት ላይ እንዲህ የሚል እናነባለን።

> ኢየሱስ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ፣ ክህነቱ የማይሻር
> ነው። ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት
> ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን
> ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ዕብራውያን 7፡24-25

እነዚህ ቁጥሮች የኢየሱስን ሕይወት በተመለከተ ትኩረት የሚያሻው ዕይታ ያቀርባሉ። ምንም ሳይታወቅ ለሰላሣ ዓመት የቤተሰብ ሕይወት ኖረ። ሦስት ዓመት ተኩል አስደናቂና ብርቱ አገልግሎት ነበረው። አሁን ደግሞ ከሁለት ሺህ ዓመት በላይ በምልጃ አሳለፈ! ስለዚህ ቀጣይ የኢየሱስ አገልግሎት የዕብራውያን ጸሐፊ ተጨማሪ ሐሳብ ይሰጠናል -

> ከመጋረጃው (ሁለተኛው) በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛው
> መቅደስ ይገባል። ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ ዕኛ ቀድሞ
> የገባበት ነው። እርሱም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት
> ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖአል። ይህ መልከ ጼዴቅ የሳሌም
> ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። ዕብራውያን 6፡19-7፡1

እነዚህን ቁጥሮች ሳነብ ሁልጊዜ የሙሴ መገናኛ ድንኳን እስባለሁ፤ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሁለት ትልልቅ መጋረጃዎች ተሰቅለው ነበር። የመጀመሪያውን መጋረጃ አልፎ መሄድ በትንሣኤው ከክርስቶስ መተባበር ጋር ይመሳሰላል። እምነቱን የአገልግሎት ስጦታዎች ማለት ሐዋርያትን፣

ነቢያትን፣ ወንጌላውያንን፣ እረኞችንና አስተማሪዎችን የምናገኘው እዚህ ነው። «ቅድስተ ቅዱሳን» በመባል የሚታወቀው ሁለተኛውን መጋረጃ አልፎ መሔድ ከትንሳኤው አልፎ ወደ ዕርገቱ መሄድ ማለት ነው። አማኞች ከኢየሱስ ጋር በትንሳኤው አንድ የሚሆኑት በዙፋኑ ከእርሱ ጋር የሚቀመጡት እዚህ ነው። (ኤፌሶን 3:2፣6 ይመ)። ከሁለተኛው መጋረጃ ባሻገር ሁለት ታላላቅና የመጨረሻ አገልግሎቶችን ማየት እንጀምራለን።

የዕብራዊያን ጸሐፊ እንደመልከ ጼደቅ ክህነተ ሹመት ኢየሱስ ወደ ሁለተኛው መጋረጃ ገባ ሲል ሰማያዊው ሹመት ንጉስና ካህን ነው ማለቱ ነው። በዚህ ምድር ሐዋርያ ወይም ነቢይ መሆን በጣም ደስ የሚል ነው። ድንቅ ስጦታዎች ናቸው። ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ይበልጥ የሚያስገርም የአገልግሎት ደረጃ ተስፋ ይሰጡናል። ከሁለተኛው መጋረጃ ወዲያ ኢየሱስ ካህንና ንጉሥ ነው። እኛም ብንሆን ያንን አገልግሎት የመካፈል ዕድል አለን።

## የካህን አገልግሎት

ብዙ ሰዎች የአንድን ንጉሥ ተግባር ይረዳሉ፤ መግዛት ነው። እንደካህን ያለንን ተሳትፎ ግን በሚገባ አይረዱትም። እስቲ ልዩ የካህን አገልግሎት በሚገልጽ አንድ ቃል እንጀምር፤ መስዋዕት ማቅረብ። በእብራውያን መልዕክት እነዚህ ግንኙነቶች የተጠቀሱባቸው ብዙ ቦታዎች እናገኛለን። ለምሳሌ ያህል ዕብራውያን 5:1 «እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት ከሰዎች መካከል ይመረጣል፤ የእግዚአብሔርም በሆነው ነገር ላይ ሰዎችን በመወከል ለኃጢአት የሚሆነውን መባንና መስዋዕትን ለማቅረብ ነው» ይላል። ካህናት መሥዋዕት ያቀርባሉ። ያንኑ መልሰን በመጽሐፍ ቅዱስ ለእርሱ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ እግዚአብሔር ሥልጣን የሰጣቸው ሰዎች ካህናት ብቻ ነበሩ ማለት እንችላለን። (ሁለት ንጉሦች ማለትም ሳኦልና ዖዝያን መሥዋዕት አቅርበው ነበር፤ ካህናት ስላልነበሩ ግን ሁለቱም በጣም ተቀጥተዋል።)

እንግዲህ ከእነዚህ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ያ ሰው ካህን ካልሆነ በቀር



ማንኛውም ሰው መስዋዕት ወይም መባ ይዞ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደማይችል እንረዳለን ማለት ነው። ያ ስጦታ ዐሥራት ቢሆን እንኳ ሰዎች በጠቅላላ ወደ እግዚአብሔር በመምጣት ስጦታ ማቅረብ አይችሉም። በካህን በኩል መምጣት ነበረባቸው።

ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ጴጥሮስ የጻፋቸው አንዳንድ ቃሎች እርስ በርስ የሚቃረኑ ሊመስሉ ይችላሉ። «እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕት ታቀርቡ ዘንድ፣ ቅዱሳን ካህናት ለመሆን እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ትሠራላችሁ» በማለት መሥዋዕት ይዘው ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ለጥንት ክርስቲያኖች ነግሮአቸዋል(1ጴጥሮስ 2:5)። ግሡ «አቅርቡ» የሚለው ሲሆን ስሙ ደግሞ «መሥዋዕት» የሚለው መሆኑ ግልጽ ነው። በማይነጣጠል ሁኔታ ሁለት ቃሎች ካህን ከመሆን ጋር ተያይዘዋል። ከእነዚያ የጥንት ክርስቲያኖች አብዛኞቹ ካህናት አልነበሩም፤ እኛም ብንሆን አብዛኞቻችን ካህናት እንዲያውም ሌዋዊ ካህናት እንኳ አይደለንም። ታዲያ ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ምን ማለት ነው? አሁንም መልሱን የምናገኘው ኢየሱስ ካኖረው ምሳሌ ነው።

## የበለጠ ክህነት

በዚህ ምድር ባሳለፋቸው ቀኖች ኢየሱስ ሌዋዊ ካህን አልነበረም። «እርሱ በምድር ቢኖር ኖሮ ካህን ባልሆነም ነበር፤ ምክንያቱም በሕግ በታዘዘው መሠረት መባን የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ» በማለት የዕብራውያን ጸሐፊ ይህን በጣም ግልጽ አድርጎታል (ዕብራውያን8:4)። ኢየሱስ ከሌዊ ነገድ የተገኘ አልነበረም። ስለሆነም የሌዋውያን ካህናትን መሥዋዕት ለማቅረብ ምንም መብት አልነበረውም።

ኢየሱስ የተለየ ዓይነት የክህነት ሥርዓት ነበረው፤ ያ ክህነት በዕብራውያን 6-7 ተገልጿል። ከጥቂት ጊዜ በፊት የጠቀስኳቸውን ጥቅሶች እንደገና ተመልከቱ፣«... ከመጋረጃው በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ

ይገባል። ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ የገባበት ነው። እርሱም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖአል። ይህ መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉስና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር» (ዕብራውያን 6፡19-7፡1)

ከዚህ በላይ ማየት አያስፈልገንም። በዕብራይስጥ መልከጼዴቅ የሚለው ስም «የጽድቅ ንጉስ» ማለት ነው። ስሙ ንጉሥነቱን ይገልጻል፤ ደረጃው የሳሌም ካህን ማለትም የሰላም ካህን ነበር። የእርሱ ዓይነት ክህነት በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጥቀስ የመጀመሪያው ነው (ዘፍጥረት 14፡18ይመ)።

በሙሴ ሕግ የሆነው የሌዋውያን ክህነት ሁለተኛ ደረጃ ማለትም ዝቅተኛ ክህነት ነበር። ዘላቂና ዘላለማዊ ክህነት የሆነው የመልከ ጼዴቅ ክህነት ነበር፤ የኢየሱስ ክህነት በዚህ ሥርዐት መሠረት ነበር።

አብርሃም ዐሥራቱን ለመልከጼዴቅ ማቅረቡን ማስተዋል ተገቢ ነው። መልከጼዴቅ በተራው ለአብርሃም ሁለት ነገሮች ሰጠው-እንጀራና የወይን ጠጅ። በመጨረሻው እራት ኢየሱስ እንጀራና ወይን ጠጅ ለደቀመዛሙርቱ በሰጠ ጊዜ፣ «በእነዚህ ነገሮች የመልከ ጼዴቅ ክህነት በእኔ ተግባር ላይ መዋሉን ታያላችሁ» የማለት ያህል ነበር። በቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሁለት ልምምዶች ማለት ዐሥራትና ቅዱስ ቁርባን በጌታ ክህነት አገልግሎት ውስጥ በጣም ጥንታዊ ሥርዓቶች ናቸው።

ምንም እንኳ ሌዋዊ ካህን ባይሆንም፣ ኢየሱስ ካህን ስለ ነበር በዚህ ምድር በነበረ ጊዜ እንኳ መሥዋዕት አቅርቧል። እንደገና ወደ ዕብራውያን መልዕክት ስንመለስ እርሱ ስላቀረበው መሥዋዕትና ያ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እኛን እንደሚመለከት እናያለን። እዚህ ላይ ጸሐፊው ከመዝሙር 110 እየጠቀሰ ነው፤ እንዲሁም በሌላ ስፍራ፣ «እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ» ይላል። «በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትንና ልመናን ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር አቀረበ »(ዕብራውያን 3፡5፤6-7)

እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለም ካህ ነህ የሚለው ቃል ለኢየሱስ ተነግሯል። ከዚያም በክህነት ተግባሩ ሦስት ተከታታይ የኢየሱስ መሥዋዕቶችን እንመለከታለን። በመጀመሪያ፣ በምድር በነበረ ጊዜ



ወደ እግዚአብሔር በመጮህ ጸሎትና ልመና አቀረበ፤ ሁለተኛ መስቀል ላይ ራሱን አቀረበ፤ ሦስተኛ በሰማይ፣ ቀጣይ የክህነት አገልግሎቱ የሆነው ምልጃ እያቀረበ ነው።

## የኢየሱስን ምሳሌ መከተል

ኢየሱስ ያኖረው ምሳሌ እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን ያሳያል። «ለወደደንና ለኃጢአታችንም በደሙ ነጻ ላወጣን አምላኩንና አባቱን እንድናገለግልም መንግስትና ካህናት ላደረገን ለእርሱ ክብር ኃይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን! አሜን የሚለው የሚገኘው ዩሐንስ ራዕይ ውስጥ ነው (ራእይ 1፡5-6)።

ኃጢአታችን ይቅር በመባሉና በኢየሱስ ደም በመንጻታችን መንግሥትና ካህናት ሆነናል። ሌሎች ትርጉሞች፣ «ነገስታትና ካህናት» ወይም ፣ «የካህናት መንግስት» ይላሉ። ምንም ይባል ምን ለሰው ልጅ የተሰጡ ሁለት ከፍተኛ ተግባሮችን እንመለከታለን። እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለው ዓላማና ፍጻሜ የካህናት መንግሥት መሆን ነው።

ነገስታትና ካህናት መሆን ማለት በልምምድ ደረጃ ለእኛ ምን ማለት ነው? እንደ ነገሥታት በመንግስት ውስጥ እንድንሆን ታቅዷል፤ እንደ ካህናት መሥዋዕቶች እናቀርባለን። ሆኖም፣ መንግሥት እና ካህናት ወይም የካህናት መንግስት የተሰኙትን ግልጽ ተያያዥ ቃሎች አስተውሉ። የእግዚአብሔር ሕዝብ አንዱን ወይም ሌላኛውን አይደለም። እንደ የመንግስት ሰዎች የእግዚአብሔርን ዓለም የመግዛት ኃላፊነት አለብን። ያን ማድረግ የምንችለው እንደ ካህናት ማገልገል ስንማር ብቻ ነው። ምን ዓይነት መንፈሳዊ መሥዋዕቶችን እንድናቀርብ ነው እግዚአብሔር የሚጠብቀው? በዚህ ምድር ባሳለፈው ህይወቱ ኢየሱስ ጸሎትና ልመና እንዳቀረበ ሁሉ እኛም ያንን ማቅረብ ይኖርብናል። መጸለይ ስንማር ያኔ ለመግዛት ብቁ እንሆናለን።

## እግዚአብሔር እየጠራችሁ ይሆን?

ከጥቂት ዓመታት በፊት አሜሪካዊ ዜጋ ሆኛለሁ። ያን ያደረግሁት በራሴ ምርጫ ነበር። ያንን ውሳኔ በጥንቃቄ ማውጣት ማጡረዴን ስነግራችሁ

እመኑኝ። ምንም እንኳ መለኮታዊ ፍርድ አሜሪካ ላይ ሊመጣ እንደሚችል ብመለከትም፤ ለመልካም ይሁን ለክፉ ራሴን ከዚህ ሕዝብ ጋር አንድ ማድረግ እንዳለብኝ ወሰንኩ።

የጸሎትን ኃይል ለመረዳትና እንደ የጸሎት ሰው በእግዚአብሔር መንግስት ያላችሁን ስፍራ ለመያዝ መምረጥ ከዚያ ያነሰ ጉዳይ አይደለም። በሚገባ አስቡበት «እግዚአብሔር ሆይ፤ የመንግሥትህ ካህን ካደረግኸኝ የሚገባውን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ» ለማለት ዝግጁ ናችሁ?

ከዚህ የበለጠ ጥሪ እንደሌለ ልንገራችሁ። ስትጸልዩ፣ ወደ ዙፋኑ ትቀርባላችሁ። ከሁለተኛው መጋረጃ በስተጀርባ ከዕይታ ውጪ በሆነ ቦታ ስላላችሁ ሌሎች ላያዩዋችሁ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ በጊዜ ውስጥም ሆነ በዘላለም ሕይወታችሁ በእግዚአብሔር ዘንድ ቦታ አለው።

አሁን ራሳችሁን እንደ ብርቱ የጸሎት ሰው ላትቆጥሩት ትችላላችሁ፤ ሆኖም፣ ራሳችሁን ስታቀርቡ እግዚአብሔር ያበጃችኋል። ምናልባት ነገሮችን የምታደርጉበትን መንገድ መለወጥ ሊሆን ይችላል፤ ልዩነቱ መልስ ያገኘ ጸሎት ይሆናል። በጣም ከባድ አይደለም፤ በጣም ተግባራዊ ነው። መልስ ለሚያገኝ ጸሎት መሠረታዊ ከሆኑ ሁኔታዎች ጋር በመጣጣም ረገድ እንዴት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደሚገባ ከዚህ መጽሐፍ እንማራለን።

ልመናና ትእዛዝ የመሳሰሉ ስለ ብዙ የጸሎት ዓይነቶች እንማራለን። መንፈሳዊ ውጊያ ስላለው ቦታ እንረዳለን። እንዴት የእግዚአብሔርን ፍቃድ እንደምናውቅና በዚያው መሠረት ለእርሱ መጸለይ እንማራለን። በልበ ሙሉነት መጸለይ ይቻላል። እንድንጸልይና የጸለይንበትን እንድንቀበል እግዚአብሔር እንደሚፈልግ አስታውሱ።

ለእናንተ የማቀርበው ጸሎት እግዚአብሔር በዚህ ጥሪ እንዲባርካችሁ፣ እጁን በላያችሁ እንዲያደርግና ራስን በመግዛትና በመማር መንገድ እንደመራችሁ ነው መሆን የምትፈልጉትን እንድትሆኑ እግዚአብሔር ያስችላችሁ። ተዘጋጅታችኋል? እንሂድ።



## 2

# ለጸሎት መልስ መሠረታዊ ሁኔታዎች

## ይጠራኛል፤ እመልስለታለሁ

ጸሎት ለክርስቲያኖች ሁሉ ከታላላቅ ዕድሎች አንዱ፣ ከታላላቅ መብቶች አንዱና ከታላላቅ አገልግሎቶች አንዱ ነው። ኢየሱስ እንዴት እንደሚሰብኩ ለደቀመዛሙርቱ እንዳስተማረ የማነበው የለም፤ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ግን አስተምሯቸዋል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር መሆን የሚፈልግ፣ በእግዚአብሔር የክህነት መንግስት ውስጥ ስፍራውን መያዝ የሚመኝ ሁሉ፣ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዴት መጸለይ እንደሚገባው መማር እንዳለበት አምናለሁ። እግዚአብሔር ስንጸልይ እንደሚቀበለን ብቻ ሳይሆን እንድንጸልይም እንደሚጠብቅ ማስታወስ አለብን።

ስለሆነም እዚህ ላይ መልስ በሚያስገኝ መንገድ እንዴት በጸሎት ወደ እግዚአአብሔር መቅረብ እንዳለብን ቅዱሳት መጻሕፍት ስምንት ሁኔታዎች ሰጥተውናል። እነዚህ መሠረታዊ መስፈርቶች ጸሎታችን መልስ እንዲኖረው የመጀመሪያ ርምጃዎች ናቸው።

1.ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘዝ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ዕብራውያን 5:7 ስለ ኢየሱስ የዚህ ምድር ሕይወትና እንዴት እንደ ጸለየ ይናገራል፤ «ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትና ልመናን ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር አቀረበ፤ ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘዙም ጸሎቱ ተሰማለት።»

እንደ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ምሳሌያችን ከመሆኑ አንጻርና በዚህ ምድር

በኖረበት ዘመን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ለእግዚአብሔር ጸሎትንና ልመናን እንዳቀረበ ከዚህ ጥቅስ የሞጀመሪያ ክፍል አጥንተን ነበር። ጥቅሱ መጨረሻ ላይ ግን አንድ ሌላ በጣም አስፈላጊ ነገር ተነግሮናል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የልጁን ልመና ይሰማ ስለነበረበት ምክንያት ተናግሮናል። ኢየሱስ የተሰማለት ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘዙ ነበር። ይህ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ መሟላት ያለበት የመጀመሪያ ጉዳይ ነው። ይህ የኢየሱስ ፍጹም ትሑት ሆኖ መታዘዝ የተገለጠው እንዴት ነበር? እዚህ ላይ የዕብራውያን ጸሐፊ እየተናገረ ያለው ኢየሱስ በጌቴ ሴማኒ ስላቀረበው ጸሎት ነው። ቀጥሎ የማቴዎስ ወንጌል ስለዚህ ሁኔታ የሚሰጠውን ገለጻ እንመለከታለን።

> - ጥቂት እልፍ ብሎ በግንባሩ በመደፋት፣ «አባቴ ሆይ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፤ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን» ብሎ ጸለየ... እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ ሄዶ፣«አባት ሆይ፣ይህ ሳልጠጣው የማያልፍ ጽዋ ከሆነ፣ ፍቃድህ ይፈጸም ብሎ ጸለየ»ማቴዎስ 26፡39፣42

ስለሆነም ፍጹም ትሑት ሆኖ መታዘዝ፣ «እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን» ማለትን ያካትታል። የራሳችንን ፈቃድ ክደን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበልን ያካትታል።

ኢየሱስ እንደ ምሳሌ የምንከተለው ጸሎት አኑሮልናል፤ ይህም የጌታ ጸሎት በማለት የምንጠራው ነው። በዚህ ጸሎት ውስጥ ይህንኑ መርሕ ጨምሯል። «መንግስትህ ትምጣ። ፍቃድህ በሰማይ እንደ ሆነ እንዲሁ በምድር ይሁን» በማለት እንድንጸልይ አስተምሮናል።(ማቴዎስ 6፡9-10)።

ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ፣«ፈቃድህ ይፈጸም» ማለት ይኖርብናል። በዚህ ጸሎት ውስጥ፣ «የአንተ ፈቃድና የእኔ ፈቃድ የማይስማማ ከሆነ፣ የአንተ ፈቃድ እንዲፈጸም የእኔን ፈቃድ እተዋለሁ» የሚል ትርጉም አለ። ሁለቱ ፈቃዶች ሲጋጩ ቅድሚያ መያ| ያለበት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።



በዚህ ግዴታ ውስጥ፣«አሮጌውን ባህርይ» የማስገዛት ገጽታ ይታያል። ለኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ጳውሎስ በዚህ መንገድ ገልጾታል፤

> ቀድሞ ስለነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞት የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው። ኤፌሶን 4፡22-24

ሁለት፣ ‹‹ሰውነቶች›› አሉ፤ አሮጌው ሰውነት እግዚአብሔር እኛን ከመለወጡ በፊት የነበረው ነው፤ አዲሱ ሰውነት እግዚአብሔር እኛን ማድረግ የሚፈልገው ነው። አዲሱ ሰውነት እንዲገለጽ፣ አሮጌው ሰውነት ወልቆ መጣል አለበት። ይህ እኛ የምናደርገው እንጂ እግዚአብሔር የሚያደርግልን ነገር አየይደለም። ስለሆነም፣ «የእኔ ፈቃድ አይሁን ስንል» አሮጌውን ሰውነት አውልቀን መጣላችን ነው። «የአንተ ፈቃድ ይሁን» ስንል፣ አዲሱን ሰውነት መልበሳችን ነው። በአእምሮአችን ዝንባሌ የምንለውጠውና የምንታደሰው በዚህ ሁኔታ ነው።

በእያንዳንዳችን ውስጥ ላለው አሮጌ ሰውነት ጸሎት እግዚአብሔር መልስ ሰጥቶ ቢሆን ኖሮ አጽናፈ ዓለም ይቃወስ ነበር። እስቲ አንድ ቀላል ምሳሌ ብቻ ልስጣችሁ የእሁድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽርሽር ለመሄድ ስላሰቡ «ጌታ ሆይ ዝናብ እንዳይዘንብ አድርግ» በማለት እየጸለዩ ነበር። በዚሁ ጊዜ የምስኪኑ ገበሬ ሰብል እየጠወለገ ስለ ነበር «ጌታ ሆይ ዝናብ አዝንብ ዝናብ ያስፈልገናል» በማለት እየጸለየ ነበር። ታዲያ እግዚአብሔር ለሁለቱም ጸሎት መልስ መስጠት የሚችለው እንዴት ነው? እውነቱ የራሱን ፈቃድ የተወው ለአዲሱ ሰው ጸሎት ካልሆነ በቀር የአንዳቸውንም ጸሎት አይሰማም የሚለው እንደሆነ ይታወቃል።

ወይም ደግሞ አንድ የተለመደ አይነት ምሳሌ እናንሣ። ሁለት አገሮች እርስ በርስ እየተዋጉ ነው። በሁለቱም አገሮች ያሉ ክርስቲያኖች፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ለአገራችን ድልን ስጥ» በማለት እየጸለዩ ነው። እግዚአብሔር እንዴት ያንን ማድረግ ይችላል? እግዚአብሔር እንደዛ አያደርግም። እግዚአብሔር መልስ የሚሰጠው ለአዲሱ ሰውነት ጸሎት ሲሆን፣ የራሱን ፈቃድ መፈጸም የሚፈልገውን የአሮጌና አመፀኛ ሰውነት ጸሎት መልስ አይሰጥም።

ስለሆነም፣ ስለማንኛውም ነገር ስንጸልይ፣ ስለዚህ ጉዳይ የምጸልየው እኔ ስለምፈልገው ነው ወይስ እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነው? በማለት ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። እንዲህ ያለው ጸሎት ትልቅ ልዩነት አለው። እኔ ስለምፈልገው ብቻ ከሆነ ጸሎቴ መልስ አያገኝም፤ እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ከሆነ ግን ጸሎቴ መልስ ያገኛል።

ከበሽታ እንዲፈወሱ ወይም፣ የገጠማቸው የገንዘብ ችግር እንዲፈታ መጸለይን የመሳሰሉ ሰዎች ጸሎትና ልመናቸውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡበት አንዳንድ ልማዳዊ ገጽታዎች አሉ። እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንዳለን ብናስብ እንኳ፣ እንድፈወስ የምንጸልየው እንድፈወስ ስለምፈልግ ብቻ ነው? የገንዘብ ችግሬ እንዲፈታ የምጸልየው ያንን ስለምፈልግ ነው ወይስ እግዚአብሔር ስለሚፈልግ? በማለት ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። ለዚያ ጉዳይ መፍትሔ ካገኘን ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበትን ሁኔታ ይለውጠዋል።

አንደ ጊዜ ከጥቂት ዓመት በፊት ልጇ ሆስፒታል ገብቶ የነበረ ሴት መጥታ ስለ ልጇ እንድጸልይ ጠይቃኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ልጁ አሥራ ሁለት አመት ያህል ይሆነው ነበር፤ ሕመሙም ፈውስ እንደሌለው ተነግሮም ነበር። ከእርሷ ጋር ለመጸለይ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነበርኩ፤ ግን በፍጹም ሳላስበው «ለመሆኑ ልጅሽን ለጌታ ሰጥተሸዋልን?» አልኳት። ያንን ተራ ጥያቄ ሳቀርብላት ሴትየዋ በጣም ተቆጣች። ልጇ እንደሚሞት ልነግራት እየሞከርኩ እንደሆነ አሰበች። ያ ሐሳብ በአእምሮ፣ አልነበረም። ልነግራት የፈለግሁት



የእርሷን ፈቃድ ብቻ የምትፈልግ ከሆነ የእግዚአብሔር ሊፈጸም እንደማይችል ብቻ ነበር። እጇን ልጇ ላይ እስካደረገች ድረስ የእግዚአብሔር እጅ ሊነካው አይችልም። የራሳችንን ፈቃድ ማስፈጸም የምንሞክር እስከሆነ ድረስ፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስፍራ አንሰጥም።

የራሳችሁን ፈቃድ ክዳችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ መቀበል ስታስቡ ሦስት እውነቶችን በአእምሮአችሁ መያዝ አለባችሁ። ከሁሉም መጀመሪያ፣ እናንተ ራሳችሁን ከምትወዱት የበለጠ እግዚአብሔር ይወዳችኋል። ሁለተኛ፣ እናንተ እራሳችሁን ከምትረዱት የበለጠ እግዚአብሔር ይረዳችኋል። ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ የሚፈልገው የተሻለውን ነገር ብቻ ነው። በእውነት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስትገዙ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ማለትም «ደስ የሚያሰኝና ፍጹም» መሆኑን ትረዳላችሁ (ሮሜ12:2)።

ትሑት ሆኖ መታዘዝ ጸሎት እኛ የምንፈልገውን እግዚአብሔር የሚያደርግበት መንገድ እንዳይደለ ይገነዘባል። «ፈቃድህ ይፈጸም» ስንል እርሱ የሚፈልገውን ለማድረግ የእግዚአብሔር መሣሪያዎች እንሆናለን።

ኤፌሶን 3:20 ላይ ጳውሎስ የተናገረውን አስቡ፣ «እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው እንደ ኃይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው…» የእግዚአብሔር ጸሎታችንን የመመለስ ችሎታ እኛ ከለመነው ወይም ካሰብነው በላይ እጅግ አብልጦ ይሄዳል። ምናልባትም፤ «እንዴት ሊሆን ይችላል? እኔ ከምለምነው፣ ከማስበው፣ ከምገምተውና ምክንያታዊ ከምለው በላይ ምን ሊኖር ይችላል?» በማለት ትጠይቁ ይሆናል። መልሱ እግዚአብሔር ማድረግ የሚፈልገውን ማንኛውም ነገር የሚል ነው።

አያችሁ እግዚአብሔር ማድረግ የሚፈልገው፣ እናንተ ወይም እኔ ለራሳችን ከምንገምተው ወይም ከምናስበው እጅግ ታላቅና እጅግ ከፍ ያለ፣ እጅግም የበለጠ ነው። እኛ የምንፈልገውን ብቻ እንዲያደርግ እግዚአብሔርን እስከወሰንነው ድረስ እግዚአብሔር የሚፈልገው ያመልጠናል። ስለሆነም

በጸሎታችን ከእግዚአብሔር የበለጠውን እንድንቀበል ኢየሱስ በመጣበት መንገድ ወደ እግዚአብሔር መምጣት ይኖርብናል - ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘዝ «እግዚአብሔር ሆይ፣ እንደ እኔ ሳይሆን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን። እግዚአብሔር ሆይ እንደፈወስ የምጸልየው፣ እንድፈወስ ትፈልጋለህ ብዬ ስለማምን እንጂ እኔ እንድፈወስ ስለምፈልግ አይደለም» ማለት አለብን።

ለአንድ ዓመት ያህል ሆስፒታል ተኝቼ ነበር፤ ዶክተሮችም ሊፈውሱኝ አልቻሉም ነበር። እኔ እንድፈውስ ስለ ፈለግሁ ሳይሆን፣ እንድፈወስ ስለሚፈልግ እግዚአብሔር እንደሚፈውሰኝ እስክማር ድረስ ተፈውሼ ከሆስፒታል አልወጣሁም። ይህን ትምህርት በአእምሮአችሁ ይዛችኋል? ትሑት ሆኖ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ ስትጸልዩ፣ የራሳችሁን ፈቃድ ባትፈልጉ ኖሮ ከምትደርሱበት በላይ እጅግ ከፍ ብላችሁ ትሄዳላችሁ።

## 2. እምነት ይኑራችሁ

የዕብራውያን መልዕክት ወደ እግዚአብሔር ለሚቀርቡ ሁሉ ፍጹም የማይለወጥ አንድ መሠረታዊ ነገር መኖሩን ይነግረናል፤ ይኸውም «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት»(ዕብራውያን 11:6)።

ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብና ተቀባይነት ለማግኘት እምነት በጣም አስፈላጊ ሁኔታ ነው። ወደ እርሱ የሚመጣ ሁሉ ማመን አለበት። ከዚያም በላይ ሁለት ነገሮች እንድናምን ተጠይቀናል፤ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚፈልጉት ዋጋ የሚሰጥ መሆኑን።

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር መኖሩን የማመን ችግር የለባቸውም። የሚፈለገው ይህ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ የእምነት ቅድመ ሁኔታን እናሟላ ነበር። ግን የሚፈለገው ያ ብቻ አይደለም። ከልብ ለሚፈልጉት ዋጋ የሚሰጥ መሆኑንም ማመን አለብን።

ያንን ታምናላችሁ? ምናልባትም «እሞክራለሁ፤ ግን የሚገባኝን ያህል



የፈለግሁት አይመስለኝም ስለ አስተምህሮ(ዶክትሪን) ወይም ነገረ መለኮት ቲዎሎጂ ብዙ አላውቅም» ትሉ ይሆናል። የምሥራች ልንገራሁ። የዚህ ዓይነቱ እምነት ከአስተምህሮ ወይም ከነገረ መለኮት ጋር በዋነኛነት ደረጃ የተያያዘ አይደለም። ይልቁንም ግንኙነት ማድረግ ነው። እንደ ሰብዕና በእግዚአብሔር መተማመን ነው። እምነትን በባሕርዩና በታማኝነቱ ላይ ማድረግ ነው። እንዲያውም በእምነት ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ውስብስብ ከሆነ ነገር መራቅ ይኖርባችኋል።

ይህ መጽሐፍ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ዕይታ መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የጀመረው በዚህ ምክንያት ነው፤ ምክንያቱም እምነት የሚነሳው ከዚያ ነው። በእግዚአብሔር መልካምነት እናምናለን፣ በታማኝነቱ እናምናለን፣ ሊደገፉት የሚቻል በመሆኑ እናምናለን። ይህ አለማመን ኃጢአት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ለምን እንደሆነ ለማወቅም ይረዳናል። አለማመን በእግዚአብሔር ባህርይ ላይ ተገቢ ያልሆነ ነገር ይጥላል። ሐሰት የሆነና ደስ የማይል የእግዚአብሔር ምስል ይስላል።

ይህ የእምነት ሁኔታ በማንኛውም መንገድ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ዓለም አቀፍ ተቀባይት ያላው ነው፤ ሆኖም በጣም በተለየ መልኩ ጸሎትን ይመለከታል። ለምሳሌ ያህል፣ «እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ» (ማቴዎስ21:22) የሚለውን እንደ ገና ተመልከቱ። እዚህ ላይ ቁልፍ የሆነው ቃል ማመን የሚለው ነው። ከዚያም በላይ 1ኛዮሐንስ 5:14፣«በእግዚአግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፍቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል» የሚል እናነባለን። እንደ ሰብዕና በራሱ በእግዚአብሔር በመልካምቱ፣ በባሕርዩ ድፍረት ቢኖረን ያኔ እንደሚሰማን ማመን እንችላለን።

እንዲህ ያለው በድፍረት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብን እምነት ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው? አዲስ ኪዳን እምነት እንዲኖረን የሚነግረን ብቻ ባለ መሆኑ እግዚአብሔር ይመስገን፤ እምነት እንደምናገኝም ይነግረናል። ይህን የምናገኘው ከሮሜ 10:17 ነው፤ «እምነት የሚገኘው

መልእክቱን ከመስማት ነው፤ መልእክቱም በክርስቶስ ቃል ነው »።

ይህ ለጸሎት ሕይወት ቁልፍ ቃል ነው። እውነቱን ለመናገር ከብዙ ዓመት ሕመም በኋላ እኔን ከሆስፒታል ያወጣኝ ቃል ነው ጤንነቴን፣ ረጅም ዘመኔንና ብርታቴን በተመለከተ ከዚህ ጥቅስ ስለ እምነት የተማርኩበት ባለ ውለታየ ነው።

ራሴን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሳስገዛ፣ የእርሱ ፈቃድ ጤና እንዲኖረን መሆኑን አወቅሁ። እምነት ቢኖረኝ እግዚአብሔር እንደሚፈውሰኝ ብገነዘብም እዚያ ተኝቼ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ወደዚያ ግንዛቤ በመጣሁ ጊዜ ሁሉ ቀጥሎ የሚኖረው ሐሳቤ፣ እምነት የለኝም የሚል ነበር።

ከዚያ አንድ ቀን «እምነት የሚገኘው መልእክቱን ከመስማት ነው» ወደሚለው ሮሜ10፡17 መንፈስ ቅዱስ መራኝ። በድንገት ሁለት ቃሎች ያዝኩኝ፤ እምነት የሚገኘው የሚለውን። እንግዲህ እምነት ባይኖረኝ እንኳ ላገኘው እችላለሁ ማለት ነው።

እምነት የሚገኘው እንዴት ነው? እምነት የሚገኘው ከመስማት ነው። እግዚአብሔርን ከመስማት ይገኛል። አያችሁ ጸሎት ለእግዚአብሔር መናገር ብቻ አይደለም፤ ጸሎት በሁለት መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ነው። በግል ከእርሱ ጋር የቀረበ ግንኙነት ማድረግ ነው። በመሠረቱ ከሁለቱ እኛ ከምንናገረው ይልቅ እግዚአብሔር የሚናገረው እጅግ ይበልጣል።

«የእግዚአብሔር የመድኃኒት ብልቃጥ» በማለት ወደምጠራው ምሳሌ 4፡20-22 እግዚአብሔር መራኝ። የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መድኃኒት ከምግብ በኋላ በቀን ሦስቴ ለመውሰድ ወሰንኩ። ከእያንዳንዱ ዋና ምግብ በኋላ ብቻየን ወደምሆንበት ቦታ እሄድና መጽሐፍ ቅዱሴን እገልጣለሁ፤ ራሴን ዝቅ አደርግና «እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ ቃል ለሥጋዬ ሁሉ ፈውስ እንደሚሆን ቃልህ ይነግረኛል። አሁን በኢየሱስ ስም እንደ መድኃኒት እወስደዋለሁ» እል ነበር። በዚያ ለጤና የማይመች የሱዳን አየር ውስጥ ብሆንም፣ የእግዚአብሔር ቃል የተሟላና ዘላቂ ጤና ሰጠኝ።

አባታችን የሚያስፈልገንን በሚገባ እንደሚያውቅ ኢየሱስ ነግሮናል



(ማቴዎስ 6፡8)። ወደ እግዚአብሔር በመምጣት የሚያስፈልጉንን ነገሮች ስንነግረው ቀድሞውኑ የማያውቀውን ነገር እየነገርነው አይደለም። በጸሎት ስትጠይቁት የሚያስፈልጋችሁን እንደምታገኙ ወደምታውቁበት ከእግዚአብሔር ጋር ወዳላችሁ ግንኙነትና ዝንባሌ መምጣት ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ እምነት የሚገኘው እግዚአብሔር የሚናገረውን ከመስማት ነው።

አንድ ሌሊት እግዚአብሔር ለዳዊት ልጅ ለሰለሞን በህልም ተገልጦ፣ «የምትፈልገው ምንድን ነው? እኔ እሰጥሃለሁ» እንዳለው ከመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን። ሰለሞን በማስተዋል መለሰ። «ለባሪያህ አስተዋይ ልብ ስጠው» ነበር ያለው። ይህ የአማርኛው ትርጉም ነው። የዕብራይስጡ ግን፣«የሚሰማ ልብ» ነው የሚለው። እግዚአብሔርን ከሚሰማ ልብ የበለጠ የከበረ ነገር የለም።

ለመስማት ልባችሁን ለማዘጋጀት እንዲረዳችሁ፤ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ገልጣችሁ እንድትጸልዩ እነግራችኋለሁ። እንዲያውም ጠንከር ወዳለ የጸሎት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ሳታነቡ እንዳትገቡ ነው የምነግራችሁ። ለምን? በመጀመሪያ በዋነኛነት እግዚአብሔር የሚናገረው በቃሉ በኩል ስለሆነ ከእግዚአብሔር መስማት ከፈለጋችሁ ብዙውን ጊዜ የምትሰሙት በዚያ ውስጥ ነው። ሁለተኛ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ ማንኛውም ነገር ከእግዚአብሔር ባለመሆኑ አንዳንድ አሳሳች ድምፆች የእግዚአብሔርን ቃል አስመስለው ይመጣሉ፤ ግን ከእርሱ አይደሉም።

የመጀመሪያው የዩሐንስ መልእክት ይህን ይገልጻል-

በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤
ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ
ይሰማናል፤ የምንለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን፣
የለመንነውንም እንደ ተቀበልን እናውቃለን። 1ዩሐንስ 5፡14-15

በተዋጣ የጸሎት ሕይወት መሠረት የምንጸልየው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በማወቅ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ

በዋነኛነት የተገለጸው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር የሚናገረውን ስንሰማ የለመንነውን እንደምናገኝ በእምነት እናድጋለን።

### 3. በኢየሱስ ስም መጸለይ

የጸሎትን መልስ እንድንቀበል ቀጥሎ ያለው አስፈላጊ ነገር በጣም ግልጽና ቀጥተኛ ነው። በኢየሱስ ስም እንድንጸልይ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እስቲ አንድ ምሳሌ ብቻ እንይ በኢየሱስ ስም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በሁለቱም መንገድ ማለት በመለመንና ከእግዚአብሔር በመቀበል እንደሚሠራ እነዚህ ጥቅሶች ማመልከታቸውንም ልብ ማድረግ አለባችሁ። «እውነት እላችኋለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ለምኑ ትቀበላላችሁ» (ዩሐንስ 16:23-24)።

በተዘዋዋሪ መንገድ ቢሆን በኢየሱስ ስም ስንጸልይ እንደሚሆን የተናገረው ምንድን ነው? በበኩሌ ሦስት እውነቶች አቀርባለሁ።

ከሁሉም አስቀድሞ፣ በኢየሱስ ስም ስንጸልይ እኛን በተመለከተ ኢየሱስ ባደረገው ነገር መሠረት ወደ እግዚአብሔር መምጣታችን ነው። የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት 3:18፣ «ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ኃጢአት ሞቶአልና፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ ጻድቅ የሆነው እርሱ ስለ ዐመጸኞች ሞተ» ይላል። በእኛ ምትክ ሲሞት ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ከፈለ። በደላችንና የሚገባንን ፍርድ በመውሰዱ፣ በደለኝነትና እፍረት ሳይሰማን ወደ እግዚአብሔር የምንመጣበትንም መንገድ ከፈተልን። አሁን ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ነጻነት አለን።

ኤፌሶን 2:13 ላይ ጳውሎስ፣ «አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም አማካኝነት ቀርባችኋል» ይላል የክርስቶስ ደም ኢየሱስ ስለ እኛ ያቀረበው መሥዋዕት የሚታይና ዘላለማዊ ማስረጃ ነው። በኢየሱስ ስም ስንመጣ እርሱ ስለ እኛ ባፈሰሰው ደም አማካይነት መምጣታችን ነው።



ምዕራፍ 7 ላይ ስለ ኢየሱስ ደም በስፋት እንነጋገራለን፡፡ እዚህ ላይ ግን ስለ ሰማያዊ ነገር ይህን የሚለውን ዕብራውያን 12 እንመልከት «...ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም፤ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ መጥታችኋል... የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደ ሚናገረው ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል»(ቁጥር22፣24)።

በብሉይ ኪዳን የተፈጸመውን ነገር መሠረት በማድረግ ይህ በጣም ግሩም ንጽጽር ይሰጠናል። በዘፍጥረት ካለው ታሪክ ቃየል ወንድሙ አቤልን እንደ ገደለ ታስታውሳላችሁ። እግዚአብሔር «ምንድነው ያደረግኸው?» በማለት ጠየቀው ቃየል ምንም የማያውቅ ንጹህ መሆኑን በተናገረ ጊዜ እግዚአብሔር «በቀልና ፍትህ ፍለጋ የወንድምህ ደም ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል» አለው(ዘፍጥረት 4 ይመ)።

እዚህ ላይ የዕብራውያን ጸሐፊ የኢየሱስ ደም ስለ እኛ ሰማይ ላይ መረጨቱንና ከአቤል ደም ይልቅ የተሻለውን እንደሚናገር ያመለክታል። በሌላ አነጋገር የኢየሱስ ደም ስለ እርቅ፣ ምህረት፣ ይቅርታና ቤዛነት ይናገራል ማለት ነው።

እንዳንዴ መጸለይ ከባድ ሲሆንብኝ፣ ትልቁ መጽናኛዬ እንዴት እንደምጸልይ ባላውቅ እንኳ፣ የኢየሱስ ደም ስለ እኔ ሁሌም በሰማይ የሚናገር መሆኑ ነው። በኢየሱስ ስም ስጸልይና ኢየሱስ ያደረገልኝን መሰረት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር እየመጣሁ መሆኑን መገንዘቤ በከፊልም ቢሆን ይህ ነው።

በኢየሱስ ስም ስንጸልይ በተዘዋዋሪ የተነገረው ሁለተኛው እውነት በራሳችን ማንነት ሳይሆን በኢየሱስ ማንነት መሰረት ወደ እግዚአብሔር መምጣታችን ነው።

የዕብራውያን ጸሐፊ ወደ እግዚአብሔር ፊት የምንመጣው ታላቅ ሊቀ ካህናችን በሆነው በኢየሱስ በኩል እንደ ሆነ ይናገራል-

> እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ በኢየሱስ ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ድፍረት አግኝተናል... በእግዚአብሔር ቤት ላይ የተሾመ ታላቅ ሊቀ

> ካህናት ስላለን ከክፉ ህሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንም በንጹህ ውሃ ታጥበን፣ በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ።(ዕብራውያን10:19፣21-22)

በተጨማሪም ዩሐንስ፣ «ልጆቼ ሆይ፣ ይህን የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን ማንም ኃጢአት ቢሰራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» በማለት ጽፎአል(1 ዩሐንስ 2፡1)። «ጠበቃ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በቃል፣ «ከጎናችን መሆኑን እንረዳለን፤ ስለ እኛ ጉዳይ እንደሚሟገት የተጠራ ሰው» ማለት ነው።

ስለሆነም በኢየሱስ ስም ስንመጣ እንደ ሊቀ ካህናችንና ጠበቃችን ከእርሱ ጋር መምጣታችን ነው። እንደ ሊቀ ካህናችን በእኛ ቦታ ሆኖ ጸሎታችንን ለእግዚአብሔር ያቀርባል- ኢየሱስ ስላቀረበው ወደ እግዚአብሔር መድረሱን እናውቃለን። እንደ ጠበቃችን እኛን በተመለከተ በቀጥታ ለእግዚአብሔር ይናገራል። እኛ ለራሳችን ከምናደርገው የበለጠ ስለ ጉዳያችን ይሟገታል። ስህተትና በደል ብንፈጽም ሌላው ቀርቶ ኃጢአት እንኳ ብናደርግ፣ ከእግዚአብሔር እንደራቅንና ዘወትር በዕፍረት መሸማቀቅ የለብንም። ከኢየሱስ የተነሳ በነጻነት ወደ እግዚአብሔር መምጣት እንችላለን።

በኢየሱስ ስም የመጸለይ ሦስተኛው ገጽታ ይህ ነው፤ በኢየሱስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ያመለክታል።

ጳውሎስ የጻፈውን በተመለከተ -

> በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን፤ ይኸውም፣ በሚወደው በእርሱ በኩል በነጻ የተሰጠን ክቡር



የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን ነው። ኤፌሶን 1:3-6

ጊዜ ከመጀመሩ ወይም ፍጥረት ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር በሐሳቡ ዘላለማዊ ዓላማ ነበረው። እግዚአብሔር አስቀድሞ አውቆናል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ቤተሰቡ ውስጥ እንደ ልጆቹ ሊቀበለንም አስቀድሞ ወስኗል። ይህ ሁሉ የተፈጸመው ኢየሱስ በመጣና በእኛ ምትክ የሞተ ሰዓት በጊዜና በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ነበር። አዲሱ የንጉሥ ጀምስ ትርጉም በመባል የሚታወቀው ስድስተኛውን ቁጥር፣ «በውድ ልጁ ተቀባይነት እንድናገኝ ያደረገበት የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ» ይላል። በውድ ልጁ ተቀባይነት እንድናገኝ ያደረገበት የሚለውን ሐረግ በጣም እወደዋለሁ። ደግሞ እንደዚያ ነው የሆነው የእርሱ ውድ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣን ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ተቀብሎናል። ተቀባይነት ያገኘነው ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ እንጂ በራሳችን ማንነት አይደለም።

ብዙ ሰዎች ችላ የመባል፣ ያለመፈለግ፣ እንደሁለተኛ የመቆጠር ስሜቶችን ይዘው በሕይወት ውስጥ እያለፉ ነው። እንዲህ የሆነው ምናልባት በወላጆቻቸው የተሳሳተ ዝንባሌ ወይም ደግሞ በትዳር ውስጥ ባል ወይም ሚስት በሚኖራቸው የተሳሳተ ዝንባሌ ምክንያት ሊሆን ይላል። ምናልባትም ችላ የመባል ቁስልን ከባድ ቁስል ላይኖር ይችላል። ይህን ቁስል ለመፈወስ የመጀመሪያው ርምጃ በኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ ችላ የማንባል መሆኑን መገንዘብ ነው። እግዚአብሔር በፍጹም ልጆቹን ችላ አይልም። በውድ ልጁ ተቀብሎናል፤ ያ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር የምንመጣበትን መንገድ የተለየ ያደርገዋል።

ይህን መሠረት አድርገን አንዴ በኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ከመጣን አስደናቂ ጥቅሞች የእኛ ይሆናሉ። በመጀመሪያ «ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደምን በልግስና አይሰጠን?» (ሮሜ 8:32)። ይህ አስገራሚ ቃል አይደለም? ከእርሱ ማለትም ከኢየሱስ ጋር እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በልግስና ይሰጠናል። ሆኖም ሁሉም መሠረት ያደረገው ቀድሞውኑ ከእርሱ ጋር

መሆኑን እንደ ሆነ አስተውሉ። ከኢየሱስ ጋር ከሆንን እንደ እግዚአብሔር ልጆች ሁሉንም የመቀበል መብት አለን። ከእርሱ ጋር ካልሆንን ግን ማንኛውንም ነገር የመጠየቅ መብት የለንም።

ከዚያ «አምላኬም እንደ ታላቅ ባጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ይሞላባችኋል» የሚል አለ(ፊልጵስዩስ 4:19)። ይህም ማለት የማይሟላ ነገር አይኖርም ማለት ነው፤ ሙላቱ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ባለጠግነት ይሆናል ማለት ነው። ለልጆቹ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ለመስጠት እግዚአብሔር በጣም ባለጠጋ መሆኑን አምናለሁ፤ ይህ የሚገኘው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

## 4. በልበ ሙሉነት ወደ እግዚአብሔር መቀረብ

መልስ በሚያስገኝ መንገድ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ቀጥሎ ያለው መሟላት ያለበት ሁኔታ በልበ ሙሉነት ወደ እርሱ መቅረብ ነው። ይህ በሁለት መንገዶች ይገለጻል። አወንታዊ በሆነ መልኩ በድፍረት ወይም በልበ ሙሉነት፣ አሉታዊ በሆነ መልኩ ያለ አንዳች የበደለኝነት ስሜት፤ የበደለኝነት ስሜት ሁልጊዜ ልበ ሙሉነትን ያዳክማሉ። እያንዳንዳቸውን እንመልከት።

በድፍረት ወይም በልበ ሙሉነት

በዕብራውያን ያሉ ሁለት ጥቅሶች ለምን በልበ ሙሉነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንዳለብን ይነግሩናል። የመጀመሪያው ይህ ነው፣ «እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበልና ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት(በልበ ሙሉነት) እንቅረብ»(ዕብራውያን 4:16)።

የምንጸልየው ዙፋን ላይ ላለው ነው። ዙፋን ንጉሥን ያመለክታል። ይህ ንጉሥ ብቻ ሳይሆን፣ ንጉሠ ነገሥት ነው። የንጉሶች ሁሉ ንጉሥ የጌቶች ሁሉ ጌታ፣ አጽናፈ ዓለሙ ገዢ፣ «ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል» በማለት የተናገረ ነው(ማቴዎስ 28:18)። የምንለምነውን ሁሉ ለማድረግ ሥልጣንም ኃይልም ወዳለው ነው የምንጸልየው። ዓይኖቻችን ከራሳችንና፣ ከጉድለት ችግሮቻችን አንሥተን ወደ ከበረው ዙፋኑ እንመልከት።



የጸጋም ዙፋን ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጸጋ ቁልፍ ከሆኑ ቃላት አንዱ ነው። በራሳችን ጥረት ማግኘት ወይም ማሳካት ከምንችለው ሁሉ በላይ ዘልቆ ይሄዳል። የጸጋ ዙፋን በመሆኑ በሚገባን ነገር ወይም ማሳካት በምንችለው፣ ወይም በራሳችን ጥረት ማከናወን በምንችለው አንወሰንም።

በክርስትና ሕይወቴ ሁልጊዜም ቢሆን ያለኝ ግንዛቤ የእግዚአብሔር ምህረት የሚያስፈልገኝ ሰው መሆኔ ነው። ምህረት ለመጠየቅ በመጣሁ ቁጥር ምህረት እንደምቀበል እንዳምን ይህ ጥቅስ ያበረታታኛል። ብዙዎች ምህረት የማይቀበሉበት ምክንያት እንደሚያስፈልጋቸው ባለማሰባቸውና ያንን ለመቀበል በእምነት ባለ መምጣታቸው መሆኑን አምናለሁ።

ከዚያ በሚያስፈልገን ጊዜ እርዳታ ለመቀበል መምጣት አለብን። ሁኔታዎችን መመልከት የለብንም። «ሁኔታዎች አዳጋች በመሆናቸው፤ ችግሮቹም በጣም ከባድ በመሆናቸው ምንም ሊደረግ አይቻልም» ማለት የለብንም። ወደ እርሱ እንድንመጣ እግዚአብሔር ጥሪ የሚያቀርብልን በችግር ሁኔታዎችም በጣም ከባድ በሆኑበት ጊዜ ነው።

እስቲ በድጋሚ ይህንን በልበ ሙሉነት እንድንመጣ የሚያበረታታንን ዕብራውያን መልዕክት ውስጥ ያለውን ውብ ጥቅስ እንመልከት፤ «እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ በኢየሱስ ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ድፍረት አግኝተናል...በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ» (ዕብራውያን 10:19-22)

በሙሉ እምነት። በልበ ሙሉነት። የሚያመለክቱት ድፍረትን፣ የኢየሱስ ደም መፍሰሱንና በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት መርጨቱን መሠረት ያደረገ ድፍረትን ነው። እንዴት ምጸለይ እንዳለብን ባናውቅ እንኳ ደሙ ስለ እኛ ተረጭቷል።

እነዚህ ከእብራውያን የተመለከትናቸው ጥቅሶች፣ «እንዲህ እናድርግ...» የሚሉ መሆናቸውን ተመልክታችኋል። ይህም ሁለት ገጽታዎችን ያመለክታል። የመጀመሪያው ውሳኔን ይጠይቃል። ሁለተኛው፣ ከአንድ ሰው በላይ የተደረገ ጥንድ ውሳኔ ይጠይቃል። አንዳንዶ ወደ እርሱ

የምንመጣው በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን፣ በሕብረት የሚጸልይ አካል ብልት በመሆን በአንድነት ወይም በጋራ ነው።

## ያለ አንዳች የበደለኝነት መንፈስ

በድፍረት ወደ እግዚአብሔር የመምጣት አዎንታዊ ገጽታ በልበ ሙሉነት መምጣት ነው። ሌላው ገጽታ ደግሞ ያለ አንዳች የበደለኝነት ስሜት መምጣት ነው። ከፍርድ ወይም ከበደለኝነት ስሜት ነጻ ስለመሆን የሚናገሩ በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች አሉ። ይኸኛው የመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ ያለ ነው፣ «ኃጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን ኖሮ፣ ጌታ ባልሰማኝ ነበር » (መዝሙር66:18)። «ኃጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን ኖሮ» ማለት በደለኛ የሚያደርገኝ፣ የሚፈርድብኝ ነገር ቢኖር ኖሮ ማለት ነው። በእምነት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በሞከርኩ ጊዜ ሁሉ ሰይጣን ይህ ድካሜን፣ ይህ ያላስተካከልኩት ነገሬን ያስታውሰኛል። ምናልባትም ያልተናዘዝኩት ኃጢአት ወይም፣ ብናዘዘው እንኳ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ማግኘቴን ያልተቀበልኩበት ነገር ሊሆን ይችላል። ይህ የበደለኝነት መንፈስ ልቤ ውስጥ ካለ የጸለይኩበትን ነገር አልቀበልም። ይህን የኃጢአት ግንዛቤ ከልቤ ውስጥ ማስወገድና በልበ ሙሉነት ወደ ዙፋኑ ማምጣት ይገባኛል (ዕብራውያን 4:16 ይመ)።

በመሠረቱ የሚሆነው በእምነት ነው፤ ምክንያቱም በኃጢአታችን ብንናዘዝ እግዚአብሔር፣ «ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው»(1ዮሐንስ 1:9)።

አንዴ ከተናዘዝን፣ ንስሃ ካደረግንና ይቅርታንና ቃል በተገባለት መንጻት ከተማመንን ስለ ኃጢአታችን በመጫነቅ መቀጠል የለብንም። እንደዚያ ካደረግን፣ ስንጸልይ፣ «የበደለኝነት መንፈስ» የሚሰማን ከሆነ፣ እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይሰማንም። ግን፣ ዘማሪው ቀጥሎ ምን እንዳለ ታውቃላችሁ? «እግዚአብሔር ጸሎቴን አድምጦአል።» በሌላ አነጋገር እርሱን ለመክሰስ ሰይጣን ካደረገው ሙከራ በላይ ከፍ ብሏል ማለት ነው።

ዮሐንስም ተመሳሳይ ስለሆነ ሐሳብ ይናገራል፣ «ወዳጆች ሆይ፤



ልባችን የማይፈርድብን ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት አለን፤ ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና በፊቱም ደስ የሚያሰኘውን ስለምናደርግ የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እንቀበላለን» (1ዮሐንስ 3:21-22)። ከጽድቅ የጎደለ ነገር በውስጣችን መኖሩን የሚያመለክት ማንኛውንም ዝንባሌ ማስወገድ አለብን። ልበ ሙሉ ወደሚያደርገን በእግዚአብሔር ታማኝነት ወደምንተማመንበት ቦታ መምጣት አለብን።

ሮሜ 8:1 ላይ እንደ ገና ጳውሎስ፣ «ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» ብሏል። በተቀረው የምዕራፍ ክፍል መንፈስ የሞላበትና የሚቆጣጠረው ሕይወት ስላለው በረከት፣ መብትና ጥቅም በጣም አስደናቂ ገለጻ ይሰጣል። ወደዚያ ምዕራፍና ወደዚያ ዓይነት ሕይወት የምንገባው ከኩነኔ ወይም ከበደለኝነት መንፈስ ነጻ ስንሆን ነው።

የአብዛኞቹ ክርስቲያኖች ችግር ጻድቅ መሆን አለመሆናቸውን አለማወቃቸው እንደሆነ አስባለሁ። ይህ እውነት ነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከጸደቅሁ በእርሱ ጽድቅ ጻድቁአለሁ። ያንን ካወቅሁ፣ በዚያ ከቆምኩና በዚያ መሠረት ከኖርኩ ከክፋው የሚመጣው ፍርድ አያገኘኝም።

እንዲህ ሲባል ግን ክርስቲያን በዚህ ዓለም ምንም ችግር አይገጥመውም ማለት አይደለም። ለጽድቅ እንሰደዳለን። በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉ መንፈሳውያን ሰዎች እንደሚሰደዱ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይሁን እንጂ ለጽድቅ በመሰደድና በአመጽ ምክንያት በሚመጣ የበደለኝነት መንፈስ ወይም ኩነኔ መካከል መሠረታዊ ልዩነት አለ። ለጽድቅ መሰደድ አመፀኛው ጻድቁ ላይ ከሚፈጥረው ችግር ይመጣል። ዐመፃን የሚመለከት ፍርድ ጻድቁ እግዚአብሔር ዐመጸኛው ላይ የሚያመጣው ነው።

ስደትን በትዕግስት እንድንቀበል ሁላችን ተጠርተናል። ይሁን እንጂ አማኞች የሆንን ዐመፅ ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔር ፍርድ መቀበል የለብንም። በእውነት ይህንን ከተረዳችሁ እፎይታ እንደሚሰማችሁ ግልጽ ነው። ነገር ግን ቀደም ሲል እንዳልኩት አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የት ላይ እንደቆሙ በሚገባ አያውቁም።

ሉቃስ 21፡36 ላይ ኢየሱስ ስለዚህ ዘመን ማክተሚያ ተናግሯል። መልእክቱ መጨረሻ ላይ ለደቀመዛሙርቱ ሲናገር፣ «ስለዚህ ከሚመጣው ሁሉ እንድታመልጡና በሰው ልጅ ፊት መቆም እንድትችሉ ሁልጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ» ብሏል። በዐመፀኛው ዓለም ከሚመጣው ፍርድ ደቀ መዛሙርቱ እንዲያመልጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አመልክቷል። ይህ ከመላው የቅዱሳት መጻህፍት ትምህርት ጋር ይስማል። ይሁን እንጂ፣ «ተግታችሁ ብትጸልዩ ይሻላችኋል። አለበለዚያ ማምለጥ አትችሉም» በማለት ነግሮአቸዋል።

በተጨማሪም፣ «የሚገባችሁ ሆናችሁ እንድትገኙ...ትጉ...ጸልዩ...» ብሏል። መዳን የሚገባችሁ ናችሁን? አይደለም፣ የዳናችሁት በእምነት ነው እንደሽልማት ያገኛችሁት አይደለም፤ የሚገባችሁ ስለሆነ ያገኛችሁት አይደለም። ይሁን እንጂ፣ የዳናችሁ ጊዜ፣ እንዲህ ያለ የጽድቅ ሕይወት እንድትኖሩ ተጠይቃችኋል፤ እንደዚያ እየኖራችሁ እግዚአብሔር ከዐመፀኞች ጋር በአንድነት ቢፈርድባችሁ እንጂ፣ ከጽድቅ የጎደለው እርሱ ራሱ ይሆናል። ያ ነው የክርስትና ሕይወት።

በዚህ በመጨረሻ ዘመን የልዩነት መስመሩ እንዳይጠፋባችሁ ተጠንቀቁ፤ ምክንያቱም፣ የተሳሳተ ቦታ ላይ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ምዕራፍ 9 ላይ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ጸሎት ያለውን ዓላማ ስንማር በጻድቁና በኃጢአተኛው፣ በርኩሱና በቅዱሱ መካከል ያለው ገደብ በጣም እየሰፋ እንደሚሔድ እንመለከታለን። ኃጢአተኛውና ርኩሱ ይበልጥ እየባሰባቸው ይሄዳሉ። ጻድቁና ቅዱሱ በመጠኑ ሻል ይላሉ።(ራእይ 22፡11)። ከየትኛው ወገን እንደሆናችሁ ማወቅ ይበጃችኋል።

ራሳችንን ለማጽደቅ የምናደርገውን ሙከራ ትተን፣ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው በእምነት አማካይነት በውስጤ የተቀመጠውን የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ በእምነት እቀበላለሁ። ስለ ራሴ ኃጢአት አልጨነቅም። መልካም ተግባሮቼ የምላቸውን አልደረድርም። ስላለፈው በደሌ አልሳቀቅም። የሚገባኝን ያህል ጥሩ ሰው መሆን አለ መሆኔን በየጊዜው ውስጤን



አልመረምርም። የኢየሱስ ደም ከኃጢአቴ ሁሉ እንዳነጻኝ በእግዚአብሔር እተማመናለሁ። ስለዚህም አሁን በልበ ሙሉነት ወደ ዙፋኑ፣ ከሁሉም የበለጠ ቅዱስ ወደ ሆነው ቦታ እመጣለሁ ማለት አለብን።

ወደ እርሱ በመግባት ረገድ ይህ ክቡር መንገድ ነው። ወደ አንድ ንጉሥ መቅረብን አስመልክቶ መጽሐፈ አስቴር አንድ በጣም ውብ የሆነ ምሳሌ ያቀርባል። ይህ ጊዜ ብሔራዊና ግለ ሰባዊ መመሰቃቀል የሆነበት ጊዜ ነበር። የሕዝቧ ሕይወት አደጋ ላይ ነበር፤ ንጉሡም ወደ እርሱ እንድትገባ አልጋበዛትም። አቤቱታዋን ለእርሱ ለማቅረብ የገዛ ሕይወቷን ለአደጋ አጋልጣለች። ሦስት ቀን ከጾመች በኋላ የክብር ልብሷን ለብሳ ንጉሡ ፊት ቀርባለች። እርሱም ተቀበላት፣ የጠየቀችውንም አደረገላት። ወደ እርሱ የቀረበችው እንደ አንድ ንግስት እንጂ እንደ አንድ ተራ ለማኝ እንዳልነበረ ልብ አድርጉ። ቤተ ክርስቲያን ወደ እርሱ እንድትመጣ ክርስቶስ የሚፈልገው በዚህ መንገድ ነው። ከእርሱ ጸጋ እና ጽድቅ የተነሳ ተቀባይነት እንደም ታገኝ በማመን እንደ ንግስት ወደ እርሱ እንድትመጣ ይፈልጋል።

## 5. ትክክለኛ ዓላማ ይኑረን

የጸሎት መልስ በማግኘት ረገድ ቀጥሎ ያለው ቅድመ ሁነታ በትክክለኛ ዓላማ መጸለይ ነው።

ፈሪሳውያንን የመሳሰሉ ሃይማኖተኞች ውጫዊ ነገሮች ላይ ወደ ማተኮር ያዘነብላሉ። ሰዎች እንዴት መልበስ እንዳለባቸው፣ ምን ማድረግና ምን መብላት እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል። ውጫዊ ነገሮች ላይ ለሚያተኩሩ ሃይማኖተኛ ሰዎች እግዚአብሔር ከውስጠኛው ጀምሮ ወደ ውጩኛው መምጣቱን መገንዘብ ይከብዳቸዋል።

ወደ ፊት የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ከልጆቹ አንዱን እንዲቀባ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ወደ እሴይ ቤት በላከው ጊዜ፣ እሴይ ቆንጆዎቹን፣ ጠንካራዎቹንና ቁመናቸው ያማረ ወጣቶችን አቀረበ። እያንዳንዱን ልጅ ተራ በተራ ባየ ጊዜ ሳሙኤል፣ ይኸኛው መሆን አለበት በማለት አስቦ ነበር። በእያንዳንዱ ጊዜ ግን እግዚአብሔር ይህን ገለጻ ሰጠው፣ ይኸኛው አይደለም

በማለት ሞሳሳቱን ነገረው። ከዚያም «እግዚአብሔር የሚያየው፣ ሰው እንደሚያየው አይደለም። ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል»(1ሳሙኤል 16፡17)።

እግዚአብሔር የልባችንን ሐሳብና ዝንባሌ ይመረምራል፤ ዓላማችንን ለይቶ ያውቃል። ስንጸልይ ስለምንጠይቀው ነገር ብቻ አያስብም፤ ያንን የምንፈልገው ለምን መሆኑም ያሳስበዋል። ይህ በዚህ ጥቅስ በሚገባ ተገልጾአል፤ «አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም። ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ስጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና» (ያዕቆብ 4፡23)።

እንዲኖረን እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ነገሮችን የማናገኝበት አንዱ ቀላል ምክንያት ባለ ማመናችን ነው። ብንለምን እንኳ አናገኝም፤ ምክንያቱም በተሳሳተ ዓላማ ስለምንጸልይ። በተለይ ደግሞ ያዕቆብ የተሳሳተ የሚለው ለራሣችን ሥጋዊ ደስታ በማሰብ መጸለይን ነው። በሌላ አነጋገር ጸሎታችን በራሳችን ጉዳይ ላይ ብቻ ካተኮረ ዓላማችን የተሳሳተ ነው። የራሳችን ምኞትና እርካታ የሚሆን ነገር ላይ እያነጣጠርን ነው።

ስለሆም፣ በትክክለኛ ዓላማ መጸለይ ምንድን ነው? በማለት እንጠይቃለን። «አብ በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ» በማለት ኢየሱስ በሚገባ ገልጾታል(ዮሐንስ 14፡3)።

ኢየሱስ ሁሉን አቀፍ ተስፋ ሰጥቶአል፤ በስሙ የምንለምነውን ማንኛውም ነገር እርሱ ያደርገዋል። ሆኖም፣ እርሱ ያንን የሚያደርግበት መሠረት፣ «አብ በወልድ እንዲከብር» ነው። ትክክለኛው የጸሎት አላማ መልሱ ለእግዚአብሔር ክብር መዋሉ ነው። በመሠረቱ ይህ ለምናደርገው ነገር ሁሉ ትክክለኛ ዓላማ ነው። እምነትን መሠረት ያደረገ የጽድቅ ሕይወት ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጣል።

ይህን ከተቃራኒው አቅጣጫ ልንመለከተው እንችላለን። የኃጢአት መሠረታዊ ባህርይ ምንድን ነው? የግድ ባንክ መዝረፍ ወይም ዝሙት መፈጸም ወይም በሃይማኖተኞች ዓይን አስቀቀ የሆነ ነገር ማድረግ አይደለም። የኃጢአት



መሠረታዊ ባሕርይ ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር አለመፈለግ፣ የእርሱ የሆነውን ክብር አለመስጠት ነው።

በሚናገረው ቃልና ከንቱ በሆነ ሕይወቱ መላው የሰው ዘር እንዴት ከእግዚአብሔር እንደራቀና ወደ አለማወቅና አመፅ እንደ ዘቀጠ ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ገልጾአል። ወደዚህ ጥልቅ ጨለማ የደረሱ እርምጃዎችንም አመልክቷል፤ «እግዚአብሔርን ቢያውቁት እንኳ፣ እንደ አምላክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም አላቀረቡለትም፤ ነገር ግን ሐሳባቸው ፍሬ ቢስ ሆነ፤ የማያስተውል ልባቸው ጨለመ»(ሮሜ 1፡21)።

ወደ ታች ያወረዱት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው? የመጀመሪያው ለእግዚአብሔር ክብር አለመስጠት ነው። ሁለተኛው ለእግዚአብሔር ምስጋና አለማቅረብ ነው። እነዚህ የመጀመሪያ ሁለት ነገሮችን በተመለከተ ቁልቁል የወረደ ሰው የኋላ የኋላ ለማሰብ እንኳ ወደሚያስከፋ ሁኔታ በሚያደርስ ድጥ መንገድ ላይ ነው። ስንጸልይ እንዲህ ያለ ስህተት እንዳንፈጽም መጠንቀቅ አለብን።

እያንዳንዳችን ከአሉታዊ የኃጢአት ስበት ነጻ እንድንሆንና ወደ ትክክለኛ ዝንባሌና የአኗኗር ዓላማ እንድንመለስ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ወደ እርሱ ስንመጣና በዚያ ዓላማ ስንጸልይ፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ላደረግነው ጸሎት መልስ በመስጠት እግዚአብሔር ይከብራል፤ ያኔ አንድ በእውነት አስደናቂ የሆነ ነገር እንደሚሆን ይናገራል። ተስፋዎቹ ሁሉ እውን ይሆኑልናል፤ «በእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣ «አዎን» የሚሆኑት በእርሱ ነውና፤ እኛም በእርሱ አማካኝነት ለእግዚአብሔር ክብር «አሜን» የምንለው፤ በዚህ ምክንት ነው»(2ቆሮንቶስ 1፡20)።

ከአእምሮ በላይ አይደለም? ላለሁበት ሁኔታ የሚስማማና ለሁኔታዎች መፍትሔ የሚሆኑ ተስፋዎች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከለመንኩና የምለምነው ለእግዚአብሔር ክብር ከሆነ የእኔ ይሆናሉ። የእግዚአብሔር ተስፋዎች ምን ያህል መሆናቸው አያሳስበኝም - ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስምንት ሺህ ተስፋዎች መኖራቸው እንደሚገመት

ሰምቻለሁ - እነዚህ ሁሉ በክርቶስ፣ «አዎን» ይሆናሉ።

ለእግዚአብሔር፣ «አዎን» የእምነት ምላሽ፣ «ለእግዚአብሔር ክብር አሜን» ማለት ነው። የእግዚአብሔርን፣ «አዎን» አጥብቆ የሚይዘውና ተስፋዎቹን የእኛ የሚያደርገው፣ የእኛ «አሜን» ነው።

## 6. የበደሏችሁን ይቅር ማለት

በተራራው ስብከቱ ኢየሱስ ካስተማረን ነገሮች አንዱ፣ «እኛ ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን» እንድንል ነው(ማቴ 6:12)። ሁላችንም ይህን እንደምናውቅ አስባለሁ። እኛ ሌሎችን ይቅር እንደምንለው አንተም እኛን ይቅር በለን። ምናልባት እኛ ያልተረዳነው የጸሎትን መልስ በመቀበል ረገድ ይህ አስፈላጊ መሆኑን ነው።

በምክር አገልግሎትና በጠቅላላው ከሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት በመንፈሳዊ ሕይወትና የጸሎትን መልስ ባለመቀበል ረገድ ይህ በጣም ከተለመዱት ማነቆዎች አንዱ መሆኑን ተረድቻለሁ። ብዙውን ጊዜ ችግሩ የሚመለከተው አንዱን ሰው ነው። አንድ ጊዜ ከአንድ መንፈሳዊ ዕርዳታ ለመፈለግ ከመጣች ሴት ጋር እየተነጋገርኩ እያለ፣ «ይቅር ያላልሽው ሰው አለን?» በማለት ጠየቅኋት። «አዎን» አለችና፣ በዩናይትድ ስቴት ፍትሕ ክፍል ውስጥ ያለ የአንድ ታዋቂ ሰው ስም ጠቀሰች። እኔም፣ «መፈታት ከፈለግሽ ይቅር ልትይው ይገባል። ሌላ አማራጭ የለም ይቅር ካላልሽው፣ እግዚአብሔር ይቅር አይልሽም» አልኳት። እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንለው አንተም እኛን ይቅር በለን።

እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን የምንለምነው እኛም ሌሎችን ይቅር ባልንበት መጠን እንዲሆን ኢየሱስ ገደብ አድርጎብናል። ይቅር ለማለት ፈቃደኞች ናችሁ? ወገኖቼ ይህን አስታውሱ፤ ይቅር ማለት ውሳኔ እንጂ፣ የስሜት ጉዳይ አይደለም። ይህንን፣«ዕዳ ስረዛ» እለዋለሁ። ለምሳሌ አንድ ሰው ላይ የሦስት ሺህ ብር ዕዳ አላችሁ እንበል። ያንን ሰርዙት። ምክንያቱም፣ እናንተ ላይ ምን ያህል የእግዚአብሔር ዕዳ እንዳለ ታውቃላችሁ? ስድስት ሚሊዮን



ብር። ዕዳችሁ እንዲሰረዝ ትፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ እናንተም የሌሎችን ዕዳ ሰርዙ፤ ያኔ የእናንተንም ይሰርዛል። ይህ የማይለወጥ ሕጉ ነው። እግዚአብሔርን መለወጥ አትችሉም። እርሱ ይቅር እንዲለን የምንፈልግ ከሆነ ዕኛም ይቅር እንድንል ይጠይቃል።

በጌታ ጸሎት የቀረበው ልመና ከሰይጣን እንዲያድነን የቀረበው ልመና ነው።«ከክፉ አድነን» (ማቴዎስ 6:13)። እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዲለን እንደምንፈልገው እኛም ሌሎችን ይቅር እስክንል ድረስ ከክፋውእንዲያድነን የመጸለይ መብት የለንም።

ኢየሱስ፣ «እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ» በማለትም ተናግሮአል (ማርቆስ 11:25)። ይህ በጣም ግልጽ ነው- የሚናገረውም እግዚአብሔርን አባታችን በማለት ለሚጠሩ ክርስቲያኖች ነው። እኔና እናንተ ከመጸለያችን በፊት ይቅር ማለት አለብን። ማንኛውንም ሰው በማንኛውም ሁኔታ ይቅር አለማለትን በልባችሁ ይዛችሁ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መሞከር ምንም ጥቅም የለውም።

## 7. በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ

የመጨረሻዎቹ ሁለት ሁኔታዎች- በመንፈስ ቅዱስ ተመሩ፣ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት መለመን እንዴት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እንድናውቅ ይረዳናል።

«በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና» በሚለው ቃል ጀምሩ (ሮሜ 8:14)። በግሪኩ መሠረቱ ይህ ቀጣይ የሆነ ጊዜን ነው የሚያሳየው። ዘወትር በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። እንደ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች በየዕለቱ በዚህ ዓለም የምትኖሩት እንዴት ነው? ዘወትርና በቀጣይነት በእግዚአብሔር መንፈስ በመመራት ነው።

በኋላ ሮሜ 8 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን በመንፈስ የመመራትን ጉዳይ ከክርስትና ሕይወት በተለይም ከጸሎት ጋር አይይዞታል።

> እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል። ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና። ቁጥር 26-27

ማንኛችንም ብንሆን የተወሰነ ዓይነት ድካም እንዳለብንና መንፈስ ይህንኑ ድካማችንን ለማገዝ እንደሚመጣ ጳውሎስ ተናግሮአል። አካላዊ ሕመም አይደለም፤ በሽታ አይደለም። የሥጋዊ ተፈጥሮአችን ክፍል ነው። ይህ ድካም ምንድን ነው? እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም። በሌላ አነጋገር ለመግለጽ፣ ስለምን መጸለይ እንዳለብን ሁሌ አናውቅም፤ ብናውቅም እንኳ ብዙ ጊዜ ስለዚያ ጉዳይ እንዴት እንደምንጸልይ አናውቅም። ልጃችሁ ጸሎት እንደሚያስፈልገው ወይም ደግሞ አንድ ወዳጃችሁ ጸሎት እንደሚያስፈልገው ታውቁ ይሆናል፤ ያም ሆኖ ግን፣ እንዴት እንደምትጸልዩ አታውቁም። የእግዚአብሔር መፍትሔ ምንድን ነው? በዚህ ድካም ሊረዳችሁ መንፈስ መምጣቱ ነው። ቦታውን ይወስድና በውስጣችሁ ይማልዳል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይጸልያል። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ መጸለይ ሲያቅተን፣ አንድ ችግር ሲገጥመንና ያንን በተመለከተ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ሳናውቅ ስንቀር ምንድን ነው የምናደርገው? ወደ መንፈስ ቅዱስ ዘወር ብለን፣ «መንፈስ ቅዱስ፣ አንተ ቦታውን ያዝና በውስጤ ጸልይ» እንላለን። በእውነት በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ክቡር በረከቶች አንዱ ይኸው ነው። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አማኙ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በሚናገረው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ቋንቋ መገለጥ እንዳለበት የማምነው በዚህ ምክንያት ነው። በሌላ አነጋገር አማኙ የማያውቀውን ቋንቋ እንዲናገር መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ ይሰጠዋል። በዚህ መልኩ አማኙ ራሱን ሲሰጥ በማይነገር መቃተት ለእርሱ ለመማለድ መንፈስ ቅዱስ ራሱ በውስጡ ይጸልያል። እንደ እግዚአብሔር



ፈቃድ ለቅዱሳን ይጸልያል። እግዚአብሔር መስማትና መልስ መስጠት የሚፈልገውን ጸሎት ይጸልያል።

እንዴት እንደምንጸልይ ማወቅ ሲሳነን ወደ እግዚአብሔር ዘወር በማለት መንፈሱ እንደሚያግዝ መገንዘብ ምንኛ ግሩም ነው! በማይታወቅ ቋንቋ በውስጣችን ሲጸልይ፣ ትክክለኛውን ጸሎት እንጸልያለን። ያንን ጸሎት የሰጠን መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ስለምናውቅ ትክክለኛ ጸሎት መሆኑን እናውቃለን፤ እርሱ የሚጸልየው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የእኛን ሕብለ ሰረሰርና ውስጣዊ ተፈጥሮ በመጠቀም በውስጣችን ይጸልያል። ይህ እግዚአብሔር በክርስቶስ ለሚያምን ሁሉ የሰጠው ድንቅ ስጦታ ነው፤

አንድ ጊዜ የመጀመሪያዋ ባለቤቴ ሊዲያና እኔ ጥቅምት ወር ማለቂያ ላይ በትውልድ አገሯ በዴንማርክ እንደነበርን አስታውሳለሁ። በኅዳር ወር ወደ ብሪታንያ ለመሄድ እያሰብን ነበር። አንድ ጥዋት ሁሌም እንደምናደርገው አልጋችን ላይ ተቀምጠን ስንጸልይ ሊዲያ፣ «ጌታ ሆይ፣ ብሪታንያ በምንቆይበት ጊዜ ሁሉ ጥሩ የአየር ሁኔታ ይኑር» ብላ ስትጸልይ ሰማኋት።

በኋላ ላይ፣ «ምን እየጸለይሽ እንደ ነበር ታውቂያለሽ ?» ራስዋን ነቀነቀች። «ብሪታኒያ በሚኖረን ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ጥሩ የአየር ሁኔታ እንዲሰጠን ነው የጸለይሽው» አልኳት። እንደዚያ ብላ መጸለይዋ እንኳ ትዝ አላላትም። በመንፈስ ቅዱስ ተመስጦ እንጂ፣ ከእርስዋ አእምሮ የወጣ አልነበረም።

«ብሪታንያ በኅዳር ወር ምን እንደሚመስል ታውቂያለሽ። በጣም ቀዝቃዛ፣ ርጥብ፣ ጭጋጋማ፣ ደብዛዛና በፍጹም ደስ የማይል ነው» አልኩ። በብሪታንያ ረጅም ጊዜ ስለ ነበርን ኅዳር ምን እንደሚመስል እናውቃለን። ግን ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ወደ ብሪታንያ ሄደን ወሩን ሙሉ ኅዳር የጸለይነው ያህል ነበር የሆነው። እዚያ ባሳለፍኩት ዘመን ሁሉ ኅዳር እንደዚያ ሆኖ አይቼ አላውቅም። ኅዳር ማለቂያ ላይ ከዚያ ስንወጣ ሊሸኙን ወደ አውሮፕላን ጣቢያ የመጡ ወዳጆቻችንን «እንግዲህ ብትዘጋጁ ይሻላል -

የአየሩ ሁኔታ ሊለወጥ ነው!» አልናቸው።

ውስን ወደ ሆነ መረዳት ችሎታችን ማለቂያ ስንመጣ፣ የአእምሮ ኃይላችንን ሁሉ አሟጠን ስንጨርስ ምንድን ነው የምናደርገው? አሳልፈን ለመንፈስ ቅዱስ እንሰጠዋለን። እርሱ ብቁ ነው። ጸሎትን በተመለከተ የመጀመሪያ ባለቤቴ በጣም የምትወደው ጥቅስ፣ «አፍህን በሰፊው ክፈተው እኔም እሞላዋለሁ» የሚለው ነበር (መዝሙር81፡10)። አፋችሁን ለመንፈስ ቅዱስ ስጡትና እርሱ ይሙላ። በውስጣችሁ መጸለይ ይናፍቃል።

መጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር እንድንጸልይ፣ ያለ ማቋረጥ እንድንጸልይ ይናገራል(1 ተሰሎንቄ 5፡17፤ ኤፌሶን 6፡18ይመ)። በራሳችን ተፈጥሮ ዐቅምና መረዳት ዘወትር ያለ ማቋረጥ መጸለይ የሚችል ሰው አለ? በፍጹም፣ የለም። መንፈስ ቅዱስን ወደ ውስጥ ስናስገባውና ለእርሱ አሳልፈን ስንሰጠው ግን 24 ሰዓት ሙሉ የጸሎት ጊዜ ሊኖረው ይችላል።

በእንቅልፋችሁ መጸለይ እንደምትችሉ ታውቃላችሁ። ይህ እውነት ነው። በእንቅልፍ ልባቸው ለሰዓቶች በልሳን ሲጸልዩ ብዙ ሰዎች ተሰምተዋል። በመሐልየ መሐልይ ሙሽሪቷ፣ «እኔ ተኝቻለሁ፤ ልቤ ግን ነቅቷል» ትላለች (ማሕልየ መሐልይ5፡2)። ይህ አንዱ የክርቶስ ሙሽራ ውበት ነው አካልና አእምሮዋ በእንቅልፍ ዕረፍት ቢሆንም ልቧ ግን በመንፈስ ለመጸለይ ንቁ ነው። በጸሎት ብዙ ሰዓቶች ማሳለፍና ጠዋት ላይ እንደ አበባ ፈክታችሁ መንቃት ትችላላችሁ። ይህ ግልጽ በሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ደረጃ መጠን መጸለይ ነው። መንፈስ ቅዱስ በድካማችን እንዲረዳን መፍቀድ ነው፤ ያኔ እርሱ ቦታውን ይይዝና እግዚአብሔር እንድንጸልይ በሚፈልገው መንገድ ይጸልያል።

በተፈጥሮአዊ አእምሮአችን መገመት ወይም ማሰብ ከምንችለው እጅግ አብልጦ እግዚአብሔር ማድረግ እንደሚቻለው ጳውሎስ የተናገረውን አስቀድመን አይተናል። ማሰብ የምንችለው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ እግዚአብሔር ማድረግ ስለሚችለውና ስላለበት ተፈጥሮአዊ ሐሳቤና ምክንያቴ ገደብ ላይ ሲደርስ፣ ያኔ መንፈስ ቅዱስ ቦታውን እንዲይዝና ከፍ ወዳለው



የጸሎት ደረጃ እንዲሻገር እፈቅዳለሁ። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲኖር፣ እንዲንቀሳቀስና ሕልውና እንዲኖረው መብት የተሰጠው በእንዲህ ያለው ከፍተኛ የጸሎት ደረጃ ነው።

## 8. በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ

መልስ ለሚያገኝ ጸሎት የመጨረሻው መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ ዝርዝር በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ ነው። ይህ ካለፈው ቅድመ ሁኔታ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ከመመራት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። አያችሁ፣ ጸሎት ውስጥ ትልቁ ጉዳይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከጸለይኩ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንዳየነው እግዚአብሔር እንደሚሰማኝ አውቃለሁ። እግዚአብሔር እንደሚሰማኝ ካወቅሁ ደግሞ የጸሎት ጥያቄየን እንዴት እንደማቀርብ አውቃለሁ።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማውቀው እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለጸው የት ነው? መልስ፣ የእግዚአብር ቃል ውስጥ ነው። ትልቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ መገለጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የእግዚአብሔር ቃል በመለኮታዊ ተስፋዎች የተሞላ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ «እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነው» ተስፋ በማለት ይጠራዋል (2ጴጥሮስ 1፡4)። ይህ ተስፋ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ተስፋው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ስለሆነም ካላችሁበት ጋር የሚያያዝ ተስፋ ካገኛችሁና ለችግራችሁ መልስ ከሆነ፣ ያ ተስፈ ለእናንተ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር የእርሱ ፈቃድ ያልሆነ ተስፋ በፍጹም አይሰጥም፤ ከዚያ ውጭ የሆነው ትክክል አይደለም። ለምሳሌ ያህል ወደ እርሱ መጥታችሁ፣ «ጌታ ሆይ፣ እንዲህ የሚል ተስፋ ቃል ሰጥተሃል» ብትሉት፣ «አዎን፣ ሰጥቻለሁ፤ ግን ማድረግ አልፈልግም» አይላችሁም።

ስለዚህ የመጨረሻው ቅድመ ሁኔታ የጸሎት ሕይወትን አጥብቆ በመያዝ ረገድ ታላቅ ምስጢር ነው ማለት ነው፤ በቃሉ በተገለጸው መሠረት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጸልያለን።

እስቲ ይህን የሚያብራሩልን ሁለት ምሳሌዎች እንይ። የመጀመሪያው ብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው አዲስ ኪዳን ውስጥ ነው።

1ዜና መዋዕል ከዳዊት ሕይወት አንድ ሁኔታ እናያለን በዚህ ወቅት የዳዊት መንግስት ተረጋግቶ ነበር። ከጦርነት በድል ተወጥቷል፤ ሰላም ሰፍኗል፤ ሁሉም ተትረፍርፎአል፤ የሚኖርበትም ጥሩ ቤት ነበረው። በተሟላው ቤቱ ውስጥ ሆኖ ስለ ነገሮች ሲያስብ፣ «እነሆ እኔ ከዝግባ በተሰራ ቤት ውስጥ እኖራለሁ፤ የእግዚአብሄር ቃል ኪዳኑ ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል» የሚል ሐሳብ ወደ ልቡ መጣ (1 ዜና መዋዕል17፡1)።

ስለሆነም ለነቢዩ ናታን፣ «ለእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ታቦት ቤት ልሠራ ነው» አለው። ናታንም፣ «በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ያሰብከውን ሁሉ አድርግ» አለው። በዚያው ሌሊት ግን እግዚአብሔር ለናታን፣ «ሂድና ባሪያዬ ዳዊትን፣ ለእኔ ቤት የሚሠራልኝ የአንተ ልጅ እንጂ አንተ አይደለህም። ግን እኔ ለአንተ ምን ላደርግልህ እንደሆነ ታውቃለህ? ቤት ልሠራልህ ነው በለው» ሲል ላከው።

ይህ ድንቅ አይደለም? «እጅግ አብዝቶ የሚበልጥ» ለሚለው ምሳሌም ነው ዳዊት ለእግአብሔር አደርገዋለሁ የሚለውን ታላቅ ነገር ማሰብ ሞከረ፤ እግዚአብሔር ግን ከዚህ በሚበልጥ ነገር መለሰለት። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ቤት ሲባል በዋነናነት ደረጃ ሕንፃ ማለት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም ቤተሰብ የተሟላ ቤት ማለትም ነው። ዘሩ እና የእርሱ ትውልድ መስመር ለዘለቄታው እንደሚጸናና ከልጆቹ አንዱ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ መላው እስራኤልንና አሕዛብን ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም እንደሚገዛ እግዚአብሔር ለዳዊት ተስፋ ሰጠው።

መልእክቱን ከተቀበለ በኋላ «ንጉሥ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ተቀመጠ» (1ዜና መዋዕል 17፡16)። ይህ በእግዚአብሔር ፊት መቀመጡን ጉዳይ በጣም እወደዋለሁ። እናንተን በተመለከተ እንዴት እንደ ሆነ አላውቅም፤ በበኩሌ ግን በጣም ረጅም ጊዜ ከተንበረከክሁ ምቾት አይሰማኝም። መጸለይ ያለብን ተንበርክክን ብቻ ነው የሚል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም።



እንዲያውም በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የወረደ ጊዜ ሁሉም ተቀምጠው ነበር።

ስለዚህም ዳዊት መጥቶ ሁሉን በሚችል አምላክ ፊት ዘና ብሎ ተቀመጠና፣ «እግዚአብሔር ሆይ.አንተ ለእኔ እጅግ መልካም ነህ፤ አንተን ለማድነቅና ስለ መልካምነትህ ላመሰግንህ ጥቂት ጊዜ መውሰድ እፈልጋለሁ» ማለትዓ የመሰለ ነገር ተናገረ። ከዚያም ዳዊት«እግዚአብር ሆይ፣ አሁን ስለ ባሪያህና ስለ ቤቱ የሰጠኸው ተስፋ ለዘላለም የጸና ይሁን፤ የሰጠኸውንም ተስፋ ፈጽም»አለ (17፡23)።

እነዚህ ባለ አንድ መልዕክት አጫጭር ቃሎች የውጤታማ ጸሎትን ባሕርይ ይዘዋል። እንደ ተናገርከው አድርግ። ጌታ ሆይ፣ ተናግረኸዋልና እባክህ አድርገው። እግዚአብሔር ከተናገረው ያደርገዋል፤ እናንተም እንዲያደርገው ትጠይቁታላችሁ፤ እንደሚያደርገውም ታውቃላችሁ። ተስፋዎቹ የፈቃዱ መገለጥ ናቸው።

የዚህን ጸሎት ውበት አያችሁ? ጌታ ሆይ፣ የተናገርከው ቃል የጸና ይሁን። ጌታ ሆይ፣ የተናገርኩት እኔ አይደለሁም፤ ሌላው ቀርቶ አላሰብኩትም። ማሰብ፣ መመኘት ወይም መለመን ከምትለው እጅግ የበለጠ ነው። ግን ጌታ ሆይ፣ አንተ ተናግረኸዋልና እባክህ አንተ አድርገው።

ዳዊት በጸሎቱ ትክክለኛ ዓላማ እንደ ነበረውም ልብ አድርጉ። ቁጥር 24 ላይ፣ «ይህም ስምህ ጸንቶ እንዲኖርና ለዘላለም ታላቅ እንዲሆን ነው» የሚል እናነባለን። ዳዊት የእግዚአብሔር ስም እንዲከብር እንጂ እርሱ እንዲከብር አልለመነም። ይህ የጸሎት ፍጹም ምሳሌ ነው። «የሰጠኸው ተስፋ ለዘላለም የጸና ይሁን፤ የሰጠኸውንም ተስፋ ፈጽም፤ ይህም ስምህ ጸንቶ እንዲኖርና ለዘላለም ታላቅ እንዲሆን ነው።››

ጸሎት መልስ እንዲኖረው ከተፈለገ ይህ ዋና ቁልፍ ነው። እግዚአብሔር ቃሉ ውስጥ የሰጠውን ተስፋ ካላወቃችሁ ወደ እርሱ በመቅረብ፣ «ጌታ ሆይ፣ ተስፋ ሰጥተሃልና እባክህ አድርግ» የምትሉት እንዴት ነው? በጸሎታችን ቃልና መንፈስን በአንድነት ማምጣት አለብን፤ ምክንያቱም ያኔ

ሁሉን የሚችል አምላክ መላው ፈጣሪነት ኃይልና ችሎታ ለእኛ ይሆናል።

ስለዚህ ጉዳይ አስቡ፣ እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለምን ወደ ሕልውና ያመጣው እንዲህ ነው። «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተሠሩ፤ በአፉም እስትንፋስ ከዋክብትና ሰራዊቱ» (መዝሙር 33፡6)። የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ በአንድነት ፍጥረቱን ሁሉ ወደ ሕልውና አመጡ። እኔና እናንተ ቃልና መንፈሱን በአንድነት ስናመጣ እኛ መለመን ወይም ማሰብ ከምንችለው እጅግ የበለጠ ነገር ያደርጋል። ይህ ደግሞ የአዲስ ኪዳን ምሳሌ ነው። አንዳንዴ፣ «በጌታ ኢየሱስ ሕይወት ከተፈጸሙ ግላዊ ሁኔታዎች ውጪ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የተፈጸመ አንድ ታላቅ ተአምር ምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?» በማለት ሰዎችን እጠይቃለሁ። የተለያዩ መልሶች አግኝቻለሁ። አንዳንድ ሰዎች አራት ቀን መቃብር ውስጥ ከኖረ በኋላ የአልዓዛር ከሞት መነሣት ነው ብለውኛል። የተሰጡ መልሶችን በተመለከተ ምንም መከራከር አልፈልግም፤ ግን እኔ እንደማስበው በአንድ ተራ ሰብዓዊ ፍጡር ሕይወት የተፈጸመ ታላቅና ብቸኛ ተአምር ድንግል ማርያም መፀነስዋና የእግዚአብሔር ልጅ እናት መሆንዋ ነው።

ይህ የሆነው እንዴት ነበር? አንድ ቀላል ቃል በመናገርዋ ነበር። መልአኩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተወሰነውን ለማርያም ነገራት። የእግዚብሔር ኃይል እንደሚጸልላት ከገለጸላት በኋላ፣ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» አላት(ሉቃስ 1፡37)። እኔ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ አማራጭ ትርጉም፣ «የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ሳያስገኝ አይቀርም» የሚል ተቀምጧል። ወይም ደግሞ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል በውስጡ ተፈጻሚ የሚያደርገውን ኃይል ይዟል ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ማርያም በመልአኩ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔር ቃል ተቀበለች። እየተቀበለችው እያለ ፍጻሜውን እውን የሚያደርግ ኃይል ተቀበለች። «እነሆ፣ እኔ የጌታ ባሪያ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» (ሉቃስ 1፡38)። በማለት የሰጠችው መልስ የጸሎት አርዓያ ሊሆነን ይገባል። በእነዚህ ቃላት በሰው ልጅ ልምምድ ውስጥ እጅግ ታላቅ የሆነ ተአምር እውን ሆነ።



እኔና እናንተም እንዲሁ በዚህ ደረጃ መጸለይ እንችላለን። ታላላቅ ነገሮች፣ «ከምትለምኑትና ከምታስቡት እጅግ የበለጠ ነገር» የምትፈልጉ ከሆነ፣ መልሱ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ ነው።

እነዚህ የዳዊትና የማርያም ሁለት ጸሎቶች ከጌታ ኢየሱስ መምጣት ጋር በጥብቅ ተያይዘዋል። ዳዊት ከጌታ የቀደሙ አባቶች እነደገና ምንጊዜም በዙፋኑ ላይ የሚቀመጥ ልጅ እንደሚኖረው እግዚአብሔር ቃል የገባለት ነው። በማርያም ማሕፀን የተፀነሰው የኢየሱስ መወለድ ተስፋው ተፈጽሞአል። በእያንዳንዱ ሕይወት ለጸሎቱ መመለስ ቁልፍ የሆነው ተመሳሳይ ማለትም፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ተናግረኸዋልና አድርገው» ማለታቸው ነበር።

በመንፈስ ቅዱስ ስትመሩ የሚሆነውን ያህል እጅግ ከፍ ያለ ወይም የበለጠ ውጤታማ የሆነ ጸሎት ማቅረብ አትችሉም፤ የእግዚአብሔርን ቃል አጥኑ፤ ከእናንተና ካላችሁበት ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያለው ተስፋ ቃል ፈልጋችሁ አግኙና፣ «ጌታ ሆይ፣ ተናግረኸዋልና አድርገው» በሉት ቀደም ሲል የተሰጡትን የጸሎት ቅድመ ሁኔታዎች ካሟላችሁ በኋላ ይህን ስታደርጉ፣ ውጤታማ የጸሎት ምስጢርን ትረዳላችሁ።

# 3

## የመንግስት ጸሎት በምድር ላይ

**በስሜ የተጠራው ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ... ከሰማይ እሰማዋለሁ:: (2ዜና መዋዕል 7:14)**

ሦስት በጣም ጠቃሚተያያዥ እውነቶችን በተመለከተ እስከ አሁን በነበረው ጊዜ መሠረት አኑረናል:: በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር የመንግሥት ካህናት እንዳደረግን ተምረናል:: በዚህ መሠረት የእኛ ኃላፊነት በጸሎት መግዛት ነው:: ይህ ዓለም በእውነት የሚገዛው በፕሬዘዳንቶች፣ በጠቅላይ ሚኒስትሮችና በአምባ ገነኖች እንዳይደለ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል:: እነዚህ የሚገዙ ብቻ ይመስላል:: በእውነት ዓለምን የሚገዙ እንዴት እንደሚጸልዩ የሚያውቁ ናቸው::

ሁለተኛ፣ ውጤታማ ለመሆን መልስ በሚያሰኝ ሁኔታ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መሟላት ያለባቸው አንዳንድ ነገሮችን ተምረናል::

ሦስተኛ፣ የእነዚህ ሁኔታዎች አካል በመሆን፣ የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም በአንድነት እንደሚሰሩ ተምረናል:: የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በጸሎታችን አማካይነት የሚሠራው፣ ከእዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ ሲሆን ብቻ ነው:: ይህም ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንድንጸልይ ከተፈለገ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ማወቅ ይኖርብናል ማለት ነው::

አሁን ደግሞ እስከ አሁን የተማርነውን ራሱን ከቻለ ምሳሌ፣ በጣም ጠቃሚ ለሆነ ምሳሌ ተግባራዊ እናድርገው:: ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ የጻፈለትም



ይህንኑ ነው::

> እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገስታትና ለባለሥልጣናት ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ፤ ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፤ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር ነው:: ይህም በእግዚአብር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው፤ እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ይፈለጋል:: 1ጢሞቲዎስ 2:1-4

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከማውቃቸው በጣም ምክንያታዊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው:: ተከታታይ ሐሳቦችን በማቅረብ እነዚያ ሐሳቦች ምን ማለት እንደ ሆኑ ጤናማና ምክንያታዊ ገለጻዎችን ያቀርባል::

ጳውሎስ ይህን መልእክት ለጢሞቲዎስ የጻፈው በአጥቢያ ማኅበር ምዕመናን መኖር ስላለበት ሥርዐት ሊያስተምረው ነበር:: የማኅበረ ምዕመኑ መጀመሪና ታላቅ ተግባር ልመና፣ ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ማቅረብ መሆን እንዳለበት ይናገራል:: እነዚህ የተለያዩ ቃሎችን በአንድ ቃል ልናጠቃልላቸው ብንፈልግ ጸሎት ልንላቸው እንችላለን:: ስለሆነም ጌታን ለማገልገል አማኞች በአንድነት ሲሰባሰቡ ዋናው ተግባራቸው ጸሎት ነው:: ጸሎት መሰረታዊ ነው:: ይህ፣ በኢሳይያስ 56:7 ላይ እግዚአብሔር፣ «ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት ተብሎ ይጠራል» በማለት ለአማኞች ከተናገረው ጋር ይስማማል:: በሌላ አነጋገር መጸለይ ብቻ ሳይሆን፣ ጸሎታችን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ምህረት ማለት የወንጌል ስጦታን ያህል በጣም ሰፊ መሆን አለበት ማለት ነው::

ከዚያ ጳውሎስ የመጀመሪያውን የጸሎት ዐቢይ ሐሳብ ይገልጻል:: ጥቅሱ መጀመሪያ ላይ በደፈናው ለሰዎች ሁሉ ጸሎት ሊደረግ ይገባል ብሎአል፤ ቀጥሎ ደግሞ መጀመሪያ ለማን መጸለይ እንዳለብን ይገልጻል:: ከሰው ዘር

በሙሉ መጀመሪያ ለማን መጸለይ እንዳለብን ይገጻል። ከሰው ዘር በሙሉ መጀመሪያ መጸለይ ያለብን ለማን ነው? ለሚሲዮናውያን ነው? ለወንጌላውያን ነው? ለሕመምተኞች ነው? አይደለም። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ግልጽ ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጣጣሙት እዚህ ላይ ነው። እግዚአብሔር ቅድሚያ ለሰጠው ነገር ቅድሚያ አይሰጡም።

በአጥቢያ ማህበር ምዕመን ደረጃ በአንድነት ስንገናኝ ወይም ሁለት ወይም ሦስት ሆነን ስንሰበሰብ እንድናርግ የሚፈልገው መጀመሪያ ነገር ስለነገስታትና ሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ መጸለይ እንደሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። በዘመኑ አነጋገር ይህ መንግስታትን ይመለከታል። በጸሎቶቻችሁ ዋናው የእናንተ ኃላፊነት ለአገራችሁ መንግስት መጸለይ መሆኑን ተረድታችኋል? በብዙ ቤተክርስቲያኖች የታዘብኩት ሰዎች በፍጹም ሌላው ቀርቶ በወር አንዴ እንኳ እንደማይጸልዩ ነው ጳውሎስ ግን ቅድሚያ ሰጥቶታል።

ለመንግስት ወይም በመንግስት በኩል እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ ነው የምንለምነው? «በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር» እስቲ ይህን ቀላል ጥያቄ ራሳችንን እንጠይቅ? የምንኖርበት አገር መንግስት ሕይወታችን ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋልን? በማንኛውም መንገድ ሕይወታችን ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ ግልጽ ነው። ስለሆነም ጥሩ ሕይወት እንድንኖር ከተፈለገ ምክንያታዊነትና የራሳችን ፍላጎት እንኳ እንዲሟላ ለመንግስታችን መጸለይ እንዳለብን ያመለክታል።

መንግሥት ምን እንዲያሳካ ነው መለመን ያለብን? በዚያ መንግስት ያለን በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር ነው። በሌላ አነጋገር መንግስት ሥራውን በሚገባ እንዲሠራ መጸለይ አለብን ማለት ነው። ወይም ደግሞ በጣም ግልጽ ለማድረግ መልካም መንግስት እንዲኖር መጸለይ አለብን።

በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ ሕይታችንን እየመራን ነው ማለት የምንችል ከንቶቻችን ነን። ከጥቂት ዓመታት



በፊት በሳንፍራንሲስኮ ከሆንግኮንግ ከመጡ ሁለት ዲፕሎማቲክ ባለ ስልጣኖች አጠገብ ለቁርስ ተቀምጬ ነበር። እንዲሁ ለጨዋታ ያህል በሆንግ ኮንግ ሁኔታው ምን እንደሚመስል ጠየቅኋቸው፤ ከኮምኒስቶች፣ ስለሚቃጣባቸው ዛቻና ይህን ስለሚመስሉ ነገሮች ይነግሩኛል ብዬ ጠብቄ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እነርሱን በጣም ያስገረማቸው በሆንግ ኮንግ አንድ ሴት በየትኛውም በሌሊቱ ሰዓት ምንም ሳትፈራ መሄድ መቻሏ ነበር ያ ግን በሳንፍራንሲስኮ፣ እንዲያውም በአንዳንድ አካባቢዎች በቀን እንኳ የሚታሰብ አይደለም።

ይህ እውነት መሆኑን እናውቃለን። በአብዛኞቹ ዋና ዋና የአሜሪካ ከተሞች አንዲት ሴት በደኅና እና ያለ ምንም ስጋት ብቻዋን መሄድ አትችልም። በአንዳንድ አካባቢዎች ወንዱ እንኳ እንደዚያ ማድረግ አይችልም። ታዲያ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት በቅድስና በሰላምና በጸጥታ እየኖርን ነው?

የአሜሪካን ዜጋ ለመሆን የአሜሪካ ተቋሞች ሁሉ ማዕከል ሕገ-መንግስት መሆኑን ተረድቻለሁ፡ ፡ ሕገ-መንግስቱንና ዜጋ መሆን ለሚፈልጉ ማሻሻያዎቹን ሳነብ እዚህ መደምደሚያ ላይ ደረስኩ። በመሥራች አባቶች የተመሠረተው የአሜሪካ ሕገ-መንግሥት ዓላማ በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ውስጥ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ መኖር እንድንችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

እነዚህ ቃሎች የአሜሪካ ሕገ-መንገስትን ዓላማ መሠረት በትክክል እንደሚገልጽ ከልቤ አምናለሁ። ያ ዓላማ ከተሳካ፣ መልካም መንግስት አለን ማለት እንችላለን። በሌላ አነጋገር በአሜሪካ መስፈርት መሠረት ጥሩ መንግሥት እያንዳንዳችን በዕለት ተዕለት ሕይወታችንና ሥራችን በእውነተኛ መንፈሳዊነትና በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ መኖር እንድንችል የሕግና የሥርዐት እንዲሁም የአስተዳደር ሁኔታን የሚያመቻች ነው። መሥራች አባቶች ሕገ-መንግቱን ሲያውቁት ይህን እንደ ዋና ግባቸው ያስቀምጡት እንደ ነበር አምናለሁ።

በጥቅሱ ቀጣይ ቁጥር፣ «ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው» የሚል እናነባለን። ይህም ጥሩ መንግስት እጅግ በጣም አስፈላጊ

ነው ማለት ነው የእግዚአብሔርም ፈቃድ ነው።

ከዚያም፣ እግዚአብሔር መልካም መንግሥት እንዲኖር ለምን እንደሚፈልግና ለምን የእርሱ ፈቃድ እንደ ሆነ ጳውሎስ አንድ መሠረታዊ ምክንያት ይነግረናል፡፡ «እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል» (ቁጥር 4)። የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር ለመላው ሰው ዘር በሰፊው መቅረቡን ቀደም ሲል አመልክቻለሁ። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይፈልጋል፤ እውነትን ወደ ማወቅ ካልደረሱ ግን ሊድኑ አይችሉም። እውነቱ ማለትም የወንጌል እውነት ካልቀረበላቸው እውነትን ወደ ማወቅ መድረስ አይችሉም፡፡

እንግዲህ በዚህ ቀላልና አሳማኝ ምክንያት በየትኛውም ቦታ ላለ ሰው ሁሉ ወንጌል እንዲነገር እግዚአብሔር ይፈልጋል። እኛ ማድረግ ያለብን ራሳችንን አንድ ተጨማሪ ጥያቄ መጠየቅ ነው። ወንጌልን መስበክ ቀላል የሚሆነው በመልካም መንግስት አስተዳደር ነው ወይስ በክፉ? መልሱ ግልጽ ስለሆነ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስለኝም። መጥፎ መንግስት ወንጌልን መስበክ ያሰናክላል። መልካም መንግስት በተለያየ ብዙ መንገድ ለወንጌል መስበክ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ስለሆነም መልካም መንግሥት ግልጽ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለት ነው።

እንግዲህ ይህን ምሳሌ በተመለከተ ለተሳካ ጸሎት መሠረት የሚሆነንን እንመለከታለን። እንደ መንግስት ካህናት በጸሎታችን ይህን ዓለም ለእግዚአብሔር መግዛት የእኛ ኃላፊነት መሆኑን እናውቃለን። ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት ከልባችን እንተጋለን፤ ትሑት ሆኖ በመታዘዝ፣ በእምነትና፣ ከሌሎች መሰፈርቶች ጋር በመስማማት ወደ እርሱ እንቀርባለን። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቃሉን እናጠናለን፤ መልካም መንግሥት የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑንም ለይተን እንረዳለን። ስለዚህ መልካም መንግሥት እንዲኖር ስንጸልይ እግዚአብሔር እንደሚሰማን እናውቃለን። እግዚአብሔር እንደ ሰማን ካወቅን ደግሞ የለመንነውን ተቀብለናል።



እስቲ በሌላ መልኩ እንይ መልካም መንግስት ከሌለን ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን የምናምን ከሆነ ሁለት ምክንያቶች ብቻ ይኖራሉ።

የመጀመሪያው ምክንያት የሚገባንን ያህል አልጸለይንም ማለት ነው። ዩናይትድስቴትስን በተመለከተ ከግማሽ በላይ ክርስቲያን ነን የሚሉ ወገኖች እንደሚመለከት አስባለሁ። በዓላማና ሁኔታው አሳስቦአቸው በፍጹም ለመንግስት አይጸልዩም። በግዴለሽነት ትከሻቸውን በመነቅነቅ ብዙ ትችት ያቀርባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመንግስት እንድንጸልይ እንጂ፣ መንግሥትን እንድንነቅፍ የሚያዝዝ አንድ ቃል እንኳ እንደሌለ መናገር እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው ምክንያት ብንጸልይ እንኳ፣ የጸለይነው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለማወቅ ስለ ሆነ ሊሆን ይችላል። የጸለይንበትን አግኝተናል ማለት የምንችለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ስንጸልይ ብቻ ነው። እዚህ ላይ መልካም መንግስት የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እናውቃለን፤ ምክንያቱም ለወንጌል መሰበክ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ለዓለማችን ያለው ዋና ዓላማ ነው።

ብዙ ነገሮች በእኛ ጸሎት ተደጋፊ መሆናቸውን ለማመን ለክርስቲያኖች አዳጋች የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? እየሆነ ያለው ነገር ከቁጥጥራችን በላይ መሆኑን፣ መንግሥትን በተመለከተ ምንም ማድረግ የምንችለው የለም የሚል ዝንባሌ በመያዛችን ወይም ቅድመ ፍርድ፣ ጥላቻ ወይም በምንመለከታቸው ክፉ ነገሮች ምክንያት ሊሆን ይችላል። በግዴለሽነት ትከሻችንን እንነቀንቃለን። እንነቅፋለን። እናማርራለን። ግን አንጸልይም። በአመራር ደረጃም ሆነ በአኗኗር ደረጃ ዓለም አቀፍ የግብረ-ገብና የስነ-ምግባር ዝቅጠት የተፈጠረው ለዚህ ነው። በቃሉ በተገለጸው መሠረት እንደ እግዚአብር ፈቃድ መጸለይ ማስገኘት የሚችለውን ወሰን የሌለው ሥራ አልተረዳንም። ከዚህም የተነሣ እርሱ ባቀደው መንገድ ለእግዚአብሔር መንግስት መግዛት አቅቶናል።

## ሦስት የጸሎት ተለዋጭ ዘይቤዎች

ምናልባት በሁሉም የሕይወት ገጽታዎቻችን መልካም ተጽዕኖ ለመፍጠር እኛ ክርስቲያኖች ያለንን ዐቅም ተግባር ላይ አላማዋላችንን እንረዳ ይሆናል። ታዲያ ይህን ሁኔታ ለማስተካከል ማድረግ የምንችው ይኖር ይሆን?የእኔ መልስ አዎን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ ግልጽና ተግባራዊ መልስ አለው፤ ነገር ግን ወደዚያ ከመሔዳችን በፊት መጀመሪያ እንደ ክርስቲያኖች ያለንን ልዩና ወሳኝ ተጽዕኖ ተግባር ላይ ለማዋል- ያም ማለት የምንኖርበትን ማኅበረሰብ ለመግዛት ያለብንን ኃላፊነት በሚገባ መረዳት ይኖርብናል።

በተራራው ስብከቱ ኢየሱስ መመሪያዎች ሰጥቶናል። በተከታታይ ሦስት ተለዋጭ ዘይቤዎች ተጠቅሟል - ጨው፣ ብርሃንና በተራራ ላይ ያለች ከተማ እንዲህ ነበር ያለው-

> እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው የጨውነት
> ጣዕሙን ቢያጣ ጣዕሙን መልሶ ሊያገኝ ይችላልን?
> ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ጥቅም
> አይኖረውም። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤
> በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም።
> ማቴዎስ 5፡13-14

እያንዳንዱ ተለዋጭ ዘይቤ ያለውን የተለየ ፋይዳ እንመለከት። ኢየሱስ ከተጠቀመበት ቅደም ተከተል ግልባጭ በሆነ መልኩ ማቅረብ እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ፣ እኛ ክርስቲያኖች በተራራ ላይ እንዳለ ከተማ ነን። ይህ ምን ማለት ነው? በሚገባ ሊገልጸው የሚችል ቃል በግልጽ የሚታይ የሚለው እንደሆነ አስባለሁ። በአንድ ጊዜ ከሁሉም አቅጣጫ እንታያለን። ሁሌም የሚመለከተን አለ። በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምታምኑ፣ ተከታዩ ለመሆን የወሰናችሁ፣ ወደዚህ ወይም ወደዚያ ቤተክርስቲያን እንደምትሔዱ ሰዎች እንዲያውቁ ካደረጋችሁበት ጊዜ አንሥቶ፣ እናንተን በተለየ መንገድ ማየት ይጀምራሉ። የሕይወታችሁን፣ ጸባይና አኗኗራችሁን ይመረምራሉ።

የሚናገረው እውነቱን ነው ወይስ ሃይማኖታዊ አስመሳይነት ብቻ?



በማለት ያስባሉ። ቤተክርቲያን ውስጥ አያዩዋችሁም፤ እንደ መሥሪያ ቤት፣ ትምህርት ወይም ሰፈር አካባቢ በመሳሰሉ ቦታዎች ግን ያዩዋችኋል። በእርሱ እንደምናምን የምንናገር ሁላችን በአንድነት ሆነን በተራራ ላይ ያለ ከተማ ያህል በግልጽ እንደምንታይ ኢየሱስ ይናገራል።

ሁለተኛ፣ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን እንደ ሆንን ተንግሮአል። ብርሃንን በተመለከተ አንድ አስፈላጊ ነገር አለው - መተኪያ የለውም። ምንም ነገር የእርሱን ቦታ መያዝ አይችልም። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ይህ እኛን በተመለከተ እውነት ነው፤ የሚተካን የለም፤ ቦታችንን የሚይዝ ወይም የእኛን ሥራ የሚሰራ የለም። በተጨማሪም ብርሃን ብቸኛ የጨለማ መልስ ነው። ያም ማለት ብርሃን ሲመጣ፣ ጨለማን በተመለከተ ብዙ ችግር አይኖርም።

ኢየሱስ የተጠቀመበት ሦስተኛ ዘይቤ የምድር ጨው ነው። ጨው በጣም የታወቀ ነገር ነው። ስለ እርሱ ብዙ መናገር ይቻላል። ሁለት ዋና የጨው አገልግሎት ማለት ጣዕም መስጠቱንና ነገሮች እንዳይበላሹ ማድረጉን ብቻ አመለክታለሁ።

ምግብ ጣዕመ ቢስ ሲሆንባችሁ ወይም ውሃ ውሃ ሲላችሁ ምንድንነው የምታደርጉት ጥቂት ጨው ነስንሱበት። ጨው ጣዕመ ቢስ ለሆነው ነገር ጣዕም ይሰጠዋል።

እንግዲህ የምድር ጨው ከሆንን እንደ ጥቃቅን ቅንጣቶች በመላው ዓለም ተበተንን ማለት ነው። ኃላፊነታችን ለምድር ጣዕም መሥጠት ነው። ለማን ጣዕም እንዲሆን? ለእግዚአብሔር ጣፋጭ እንዲሆን። የእኛ መገኘት ምድር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራት ያደርጋል፤ በእርሱ ጸጋና ፍቅር እንደ ክርቲያኖች እርሱን በማምለክና በማመስገን፣ እንደ ፈቃዱ በመጸለይ ባንኖር ዓለም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ነበር። የእኛ መኖር ምድርን በሚመለከትበት ሁኔታ ልዩነት ያመጣል። መነጠቅ በመባል በሚታወቀው ታላቅ ክስተት እግዚአብሔር ሁላችንንም ከዚህ ሲወስድ አንድ ቀን ዓለም ይህን እንደሚረዳ አምናለሁ፤ ያ ቀን ገና አልመጣም። ባለው ጊዜ ጨው የመሆን ኃላፊነት አለብን።

ሁለተኛው የጨው ተግባር መበስበስ ወይም መበላሸት እንዳይኖር ማድረግ ነው። ከሪፍሪጅሬተር በፊት ሰዎች ምግባቸው እንዳይበላሽ የሚጠብቁት በጨው አማካይነት ነበር።

ዉተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ያለው የምሕረትና የጸጋ ዓላማ እስኪፈጸም ድረስ ግብረ ገባዊ ብልሽት፣ ማኅበረሰባዊ ብልሽት፣ ፖለቲካዊ ብልሽት ይታገድ ዘንድ የብልሽት ኃይልን የማስቆም ኃላፊነት አለብን።

ጣዕም በመስጠትና ብልሹነትን በማስቆም እንደጨው ያለብንን ተግባር ባንፈጽምስ? ኢየሱስ የተናገረውን ተመልከቱ፣ «ጨው የጨውነት ጣዕሙን ቢያጦ ለምንም አይጠቅምም።»

ይህ እኛን የሚመለከት መሆኑን ትረዳላችሁ? ማድረግ የሚገባንን ካላደረግን፣ ከእንግዲህ ለምንም አንጠቅምም። ወደ ውጪ ተጥሎ በሰዎች መረገጥን መጠበቅ አለብን። እንደዚያ ያለ ነገር ቢደርስባችሁ ምንድን ነው የሚሰማችሁ?

አያችሁ፣ በዚህ ዘመን በጣም አሳዛኙ እውነት በምድራችን ያሉ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ክርስቲያኖችን መርገጥ እንደ ትልቅ መብታቸው መቁጠራቸው ነው። እግዚአብሔር ወደ እዚህ ምድር ወርዶ አይረግጠንም፤ ይልቁንም ክርስትናንና ክርስትና የሚወክለውን ሁሉ ለሚጠሉ ሰዎች አሳልፎ ይሰጠናል። እንዲህ ያለው ሁኔታ ሲደርስ የሚኖረን መራራ ትውስታ፣ «የሚገባን ነው የደረሰብን። ኢየሱስ አስጠንቅቆን ነበር እኛ ግን አልሰማንም። የጨውነት ጣዕማችንን ካጣን ወደ ውጭ ተጥለን እንደምንረገጥ ነግሮናል» የሚል ይሆናል።

## መፍትሔው

ቀደም ብዬ እንዳልኩት መልካም ለማድረግ ያለንን አቅም ባለ መጠቀም ለደረሰብን ውድቀት መፍትሔ አለ። ከምሕረቱ የተነሣ እግዚአብሔር ሁኔታውን ወደ መልካም የምንለውጥበትን መንገድ እግዚአብሔር እንደሚሰጠን አምናለሁ። አቅጣጫ የሚያመለክተን ቁልፍ ጥቅስ በጣም የምናውቀው ነው። «በስሜ የተጠራው ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ፣ ፊቴን ቢፈልግና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ እሰማዋለሁ፤ ኃጢአቱን ይቅር እላለሁ፣ ምድሩንም እፈውሳለሁ»(2ዜና መዋዕል 7፡14)።



ይህ ለማን እንደተነገረ እስቲ አንድ አፍታ እንይ። እግዚአብሔር፣ «በስሜ የተጠራው ሕዝቤ» ይላል። ዕብራይስጡ ስሜ የተጠራባቸው ነው የሚለው። ይህ እንደ ክርስቲያኖች በትክክል እኔና እናንተን ይመለከታል። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እኛ ላይ ስለ ተጠራ ክርስቲያኖች ሆነናል። የእርሱ ሕዝብ ነን። እንዲህ ከሆነ ደግሞ፣ እግዚአብሔር አራት ነገሮች ይጠብቅብናል። እኛ እነዚህ አራት ነገሮች ካደረግን፣ እርሱ ደግሞ ሦስት ነገሮች ያደርግልናል።

እግዚአብሔር አደርግላችኋለሁ ካላቸው ሦስት ነገሮች እንጀምር ቀጥሎ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ናቸው፤ «ከሰማይ እሰማዋለሁ፤ ኃጢአቱን ይቅር እላለሁ።» እግዚአብሔር ሁሉንም ጸሎት እንደሚሰማ ቃል አልገባም፤ ነገር ግን ቅድመ ሁኔታዎቹን ብናሟላ ጸሎታችንን እንደሚሰማና ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚል ተናግሯል። እየተናገረ ያለው ስለ ሕዝቡ ኃጢአት መሆኑን አስተውሉ። ይህን መረዳት ይኖርብናል። ኃጢአታችን በእኛና በእግዚአብሔር ማዳን መካከል ጣልቃ ገብቷል።

እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለው ሦስተኛ ነገር፣ «ምድሩንም እፈውሳለሁ» ነው። አብዛኛው የዓለማችን ክፍል ፈውስ ያስፈልገው ይሆን? እንደ አንድ አሜሪካዊ ስናገር የአሜሪካ ሕዝብ በዚህ ዘመን የሚያስፈልገውን ያህል በታሪኩ ፈውስ አስፈልጎት አያውቅም እላለሁ። ምድሩን እንደሚፈውስ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ፣ በእርግጥ በዚህ ዘመን ለእኛ የሚሆን ተስፋ ነው። ሆኖም፣ ቅድመ ሁኔታ ማሟላትን የሚጠይቅ ተስፋ መሆኑን ልብ እናድርግ።

እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቃቸው አራት ነገሮች ምንድን ናቸው? በመጀመሪያ፣ ራስን በማዋረድ መምጣት መጽሐፍ ቅዱስ፣ «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለ ትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል» ይላል (1ጴጥሮስ 5፡5)። እንጸልይ ይለናል፣ ግን የምንጸልየው በትዕቢት፣ በእብሪትና ራስን በማጽደቅ ከሆነ እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይሰማም። ራሳችንን ካዋረድን ወይም ዝቅ ካደረግን በኋላ ሁለተኛውን መስፈርት በማሟላት እንጸልያለን።

ሦስተኛው ነጥብ የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ነው። ይህ በ 7 ሰዓት ተጀምሮ በ 9 ሰዓት ከሚያበቃ የጸሎት የበለጠ እንደ ሆነ አስባለሁ። የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ማለት እንዳገኘነውና የጸሎታችን መልስ መንገድ ላይ እንደ ሆነ እስክናውቅ ድረስ እንጸልያለን ማለት ነው።

አራተኛ፣ ከክፉ መንገዳችን መመለስ አለብን። ክፉ መንገዳችን በምድሪቱ ላይ ችግር እንዳመጣ ሐቁን መቀበል አለብን። አለመጸለያችን፣ እንደሚገባ አለመመስከራችን፣ እግዚአብሔርን የማይፈራና የማያምን ሰውን አለመገዳደር በግልጽ የሚታይ ጽድቅን አለማሳየታችን፤ እግዚአብሔር የለውጥን ኃላፊነት እኛ ላይ አድርጓል።

አሁን፣ ጸሎታችን መልስ እንዲኖረው ከተፈለገ መከተል የሚገባንን መርሖዎች ተረድተናል፤ ልመናና ምልጃ የመሳሰሉ የተለያዩ የጸሎት መንገዶች መመልከት ይቻላል። የተለያዩ የጸሎት ዓይነቶችን እንደ አንድ ታላቅ ሲምፎኒ /ስምረት/ ማሰብ እወዳለሁ። የሚቀጥለው ምዕራፍ ርዕሰ ጉዳይ ይህ ነው፤ እነዚህ መርሖዎች እንዲሠሩ ከፈለጋችሁ መከተል ያለባችሁ አስራ ሁለት የተለያዩ የጸሎት ዓይነቶች ወይም እርስ በርስ የሚስማሙ መንገዶች እንመለከታለን።



# 4

# አሥራ ሁለት የተለያዩ የጸሎት ዓይነቶች

**ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለ ምንም ነገር በመስማማት ብትጠይቁ በሰማይ ያለው አባቴ ያደርግላችኋል፤ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁና። ማቴዎስ 18:19-20**

ይህ ቃል ለውጤታማ ጸሎት መሠረት የሚኖር ጠቃሚ መርሕ ይሰጠናል። በበኩሌ «የሲምፎኒ ጸሎት» በማለት የምጠራው ሲሆን፣ ሲምፎኒ የሚለውን ቃል የምጠቀመው በምክንያት ነው። እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው በመስማማት የሚለው የሙዚቃ ቃል ነው። ሲምፎኒዮ(sumphoneo) ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ እንዳለ ቃሉን በመውሰድ ሲምፎኒ የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ይሰጠናል። መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቡ ስምምነትን የሚመለከት ነው።

መሰብሰብ የሚለው ቃል በቃል፣ «በአንድነት የተመሩ» ማለት ነው። ጸሎት ስለ መመራት ስንናገር፣ በማን መመራት ወደሚለው ጥያቄ እንመጣለን። መልሱ ሮሜ 8:14 ላይ ተሰጥቷል፤ «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚብሔር ልጆች ናቸውና።» ከቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድንረዳ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራን ሁሉ፣ ያንኑ ወደ እግዚአብሔር እንድናቀርበውም ይመራናል።

እንግዲህ በዚህ ቃል መሠረት ኢየሱስ የሚለው ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በኢየሱስ ስም ወደ ስብሰባ ስፍራ በመንፈስ ቅዱስ ከተመሩ መገኘቱ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን እርግጠኛ መሆን ይችላሉ። በተጨማሪም እነዚህ የተሰበሰቡ ሰዎች እንደ ሙዚቃ ስምምነት ስለ ማንኛውም ነገር ተስማምተው ከጸለዩ ይሆንላቸዋል።

እዚህ ላይ ኢየሱስ፣ «ሁለት ኦርቶዶክሶች በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁ» ወይም፣ «ሁለት ካቶሊኮች፣ ወይም ጴንጤቆስጤዎች በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁ» አለማለቱን ልብ አድርጉ። ብዙ ሰዎች ይህን ጥቅስ በተሳሳተ መንገድ ተግባር ላይ ያውሉታል። እርሱ ከእነርሱ በጣም ርቆ እያለ እነርሱ ግን ስለ ኢየሱስ በመካከላቸው መገኘት ይናገራሉ። እርሱ የሚገኘው ወደ ስሙ ለመምጣት በእግዚአብሔር መንፈስ ከተመሩ ጋር ብቻ ነው።

እዚህ ላይ የኅብረት ጸሎትን በተመለከተ እግዚአብሔር አዲስ ራእይ እየሰጠን እንደ ሆነ አስባለሁ። ጉዳዩ ሁለት ወይም ሦስት በመሆን በአንድነት መቀመጣችን ሊሆን ይችላል - ይህ ይህን ጥቅስ የምናይበት የተለመደ እይታችን ነው። ሆኖም፣ ጉዳዩ በአካል በተለያዩ ስፍራ ሆነን ለየብቻችን ብንጸልይ እንኳ፣ በስሙ ፈቃዱን ስንጸልይ በኅብረት እንዲደረግ ነው ጸሎት ወደ ጌታ ፊት መቅረቡም ሊሆን ይችላል።

የሙዚቃ ባለሙያ አይደለሁም፤ ሆኖም ሲምፎኒ በርካታ ግብዐቶችን እንደሚያካትት አውቃለሁ። መሪ፣ ድርሰትና ኦርኬስትራ ማለትም ሙዚቀኞችንና መሣሪያዎቻቸውን ይጠይቃል።

በእኛ ጸሎት ሲምፎኒ መሪው መንፈስ ቅዱስ ነው። ድርሰቱ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ሙዚቀኞቹ በኢየሱስ ስም በአንድነት የተሰበሰቡት ናቸው። እነዚህ ግብአቶች ቦታ ቦታቸውን ሲይዙ መንፈስ ቅዱስ የሥልጣን በትሩን ያነሣና የተለያዩ መሣሪያዎች ሙዚቃን ወደ ኅብረት ያመጣል።



ስለ ጸሎት ስታስቡ በኦርኬስትራ ውስጥ የሙዚቃ መሳርያ የምትጫወቱ ያህል ቦታ ቦታችሁን ስለ መያዝ እንድታስቡ እወዳለሁ። በአንድ የተለየ ኦርኬስትራ ውስጥ አንድ አይነት መሣሪያ እየተጫወቱ ቢሆንም፣ በአንድ መሣሪያ ብቻ የተወሰናችሁ አይደላችሁም። መሣሪያዎች ምስጋና፣ ውዳሴ፤ አምልኮ፣ ልመና፣ ምልጃ፣ ጸሎት፣ ትእዛዝ፣ መሰጠት፣ መለየት፣ ጽናት፣ መባረክና መርገም ናቸው። ይህ የተሟላ ዝርዝር አይደለም። ሌሎች ብዙዎችም ይኖራሉ። ግን፣ እኛን በሥራ ለመጥመድ እነዚህ ይበቃሉ! እነዚህ መሣሪያዎች፣ «በጸሎትና በልመና ሁሉ፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ» ለመጸለይ ዝግጁ ያደርጉናል (ኤፌሶን 6፡18)።

## ምስጋናና ውዳሴ

ምንጊዜም ቢሆን የጸሎት ጊዜን በእነዚህ ሁለት መሣሪያዎች - በምስጋናና ውዳሴ መጀመር እወዳለሁ። ምስጋና ስለ ማንነቱና በአጠቃላይ ስለሚያደርጋቸው ነገሮች የሚቀርብ ነው። ውዳሴ፣ በተለይ ለእኛ እግዚአብሔር ስላደረገው የሚቀርብ ነው። አስቸኳይ ጉዳይ ካለባችሁ፣ ብዙ በመናገር ጊዜ ማባከን የለባችሁም። እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥማችሁ ካልሆነ በቀር በእነዚህ ሁለት መሣሪያዎች መጀመር መልካም ነው።

መዝሙር 48፡1፣ «እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤ በአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል» በማለት ይነግረናል። ምስጋና በአንደበት የሚገለጽ ነው። ምስጋና ከራሱ ከእግዚአብሔር ማንነት ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ መቅረብ አለበት። እርሱ ታላቅ ነው - በጥበብ ታላቅ ነው፤ በኃይል ታላቅ ነው፤ በፍጥረት ሥራው ታላቅ ነው፤ በማዳን ሥራው ታላቅ ነው፤ ከእኛ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ታላቅ ነው። እግዚአብሔር በማንነቱና በሚያደርገው ሁሉ ታላቅ ነው። ስለሆነም በትልቁ መመስገን ይኖርበታል። ጌታን ስናመሰግን ጊዜ እያባከንን አይደለም። ብዙዎቻችን በጣም በጥቂቱ ነው የምናመሰግነው።

ውዳሴም እንዲሁ በአንደበት የሚገለጽ ነው። የእግዚአብሔር የሆነውን ታላቅነት ሁሉ፣ በተለይ እኛ ላለንበት ሁኔታ ተግባራዊ ያደርገዋል። ጳውሎስ የሚለውን ስሙ፣ «በነገር ሁሉ፣ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ውዳሴ ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለማንኛውም ነገር አትጨነቁ» (ፊሊ.4፡6)።

እኔ እንደምረዳው ምስጋናና ውዳሴ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብን ይሰጠናል፡፡ መዝሙር 100፡4 እነዚህ የተለመዱ ቃሎችን ይሰጠናል፤ «በምስጋና ወደ ደጆቹ በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡ፤ አመስግኑት ስሙንም ባርኩ፡፡» ወደ አደባባዮቹ፣ አደባባዮቹም ወደ ፊቱ ያመራሉ፡፡ ወደ ደጆቹ በውዳሴ፣ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ትገባላችሁ፡፡ እንግዲህ በቦታው ናችሁ ማለት ነው፡፡

ያለ እነዚህ መሣሪያዎች ርዳታ በመፈለግ ወደ ኢየሱስ መጥተው የነበሩ አስር ለምጻሞች እንመስላለን፡፡ በሩቅ ሆነው በመጮኽ፣ «ጌታ ሆይ፣ ማረኝ» አሉ (ሉቃስ 17፡17-19)፡፡ ምህረት አድርጎላቸዋል፤ ወደ ፊቱ ግን አልመጡም፡፡ እጅግ ብዙ ክርስቲያኖች የሚጸልዩት - በዚያ ሁኔታ ነው፡፡ ‹‹ጌታ ሆይ፣ እርዳኝ፡፡ ገንዘብ ያስፈልገኛል፡፡ ፈውሰኝ›› ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ወደ ፊቱ የሚያገባቸው ብርቱ መንገዶች ስለማይጠቀሙ የሚጮኹት ሩቅ ሆነው ነው፡፡

ከእነዚያ ለምፃሞች ታሪክ ውዳሴ ለማቅረብ የተመለሰው አንዱ ብቻ መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡ ያንን ሲያደርግ በቀጥታ ኢየሱስ ፊት መቅረብ ቻለ የተፈወሱት ዐሥሩም ቢሆኑም፣ የዳነው ግን አንዱ ብቻ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ውዳሴ በማቅረቡ እንደ አካዊ ሁሉ መንፈሳዊ ጥቅምም አገኘ፡፡

አንድ ጊዜ በኢየሩሳሌም እየተናገርኩ እያለ አንድ ሽማግሌ ሰው ወደ እኔ መጣ፡፡ ሰውየው በሁሉም ነገር ሽማግሌ ነበር - በዕድሜው እኔን ያክላል፤ ከእኔ የበለጠ ግን በጌታ ነበር፤ በጣም የተከበረ የእግዚአብሔር ሰው ነበር፡፡ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ እየተናገርኩ ነበር፤ ስለዚህ ጉዳይ ሁሉም የሚያውቁ መስሎኝ ነበር፤ ይህ ሰው ግን፣ «በውዳሴና በምስጋና ወደ እግዚአብሔር ፊት ስለ መቅረብ የሚገባኝን ነው የነገርከኝ» አለ፡፡ ለሃምሳ ዓመት ክርስቲያን ነበር፤ ሆኖም ይህን መርሖ በፍጹም አለማወቁ ግልጽ ነበር፡፡

ትንቢተ ኢሳያስ ውስጥ የምናገኘው አንድ ውብ ሐረግ ወደ እፍዚአብሔር ፊት መምጣትን አስመልክቶ ሌላ ምሳሌ ይሰጠናል፡፡ እግዚአብሔር ስለሚያድርበት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ መኖሪያ ስለሆነች



የእግዚአብሔር ከተማ ትንቢታዊ ገለጻ ነው፡፡ ስለዚህ ውብ ቦታ ሲናገር ኢሳይያስ፣ «ቅጥሮችሽን ድነት፣ በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያቸዋለሽ» አለ (ኢሳይያስ 60፡18)፡፡

የዚህ ከተማ አጥር ድንቅ ነው፡፡ ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ትሮታና ጥበቃ ያመለክታል፡፡ ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ ሞት በተገዛልን ማንኛውም ጥቅሞችና በረከት የሚያመለክት ታላቁና ሁሉን አቀፍ ቃል ነው፡፡ ቅጥሮቿ ድነት የሆኑት ከተማ በሮችም አሉዋት፡፡ ወደዚህች ክብርት ከተማ የሚገባው በበሮቹ እንደ ሆነ የራዕይ መጽሐፍ በግልጽ ይነግረናል (ራእይ 21፡25-27፤ 22፣14)፡፡ ወደ ድነት ከተማ መግባት ከፈለግን፣ ወደ እዚአብሔር ፊት መግባት ከፈለግን፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ልግስናና ጥበቃ፣ እንዲሁም በረከት ማግኘት ከፈለግን በምስጋና በር እንገባለን፡፡

ጆን ዌስሊ ጆርናሉ ላይ እንዲህ ጽፏል፣ «እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር የሚያደርገው በጸሎት እንደ ሆነና ከዚያ ውጪ ምንም እንደማያደርግ ወደ ማመን መጥቻለሁ፡፡» እኔም ለዚያ አባባሉ አሜን እላለሁ፡፡ ጳውሎስ፣ «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ...ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ፡፡ ይልና «ከምስጋናም ጋር» የሚል ጨምሯል (ፊልጵስዮስ 4፡6)፡፡ በሌላ አነጋገር ከልመናችሁ ጋር ወደ እግዚአብሔር ስትመጡ፣ በምስጋና መጀመርን አትዘንጉ ማለት ነው፡፡

በሰሜናዊ አየርላንድ ባንጎር የሚሉት ከተማ አለ፣ እኔና ባለቤቴ ሩት ከዚህች ከተማ ጋር የረጅም ጊዜ ግንኙነት ነበረን፡፡ በዚህች ከተማ ውስጥ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ በእያንዳንዱ ቀን 24 ሰዓት፣ በእያንዳንዱ ሳምንት፣ በእያንዳንዱ ዓመት 24 ሰዓት ሙሉ ያልተቋረጠ ምስጋና ለማቅረብ የተጉ መነኩሴዎች አሉ፡፡ እነዚያ በዕድሜ የገፉ መነኩሴዎች የዋዛ አይደሉም፡፡ ተግባራቸው ላይ እያሉ እንቅልፍ ቢይዛቸው እስከ አንገታቸው የሚደርስ ወንዝ ውሃ ውስጥ ገብተው ይቆማሉ፡፡ ወደዚያ ብትሄዱ ያንን ቦታ በተመለከተ የተለየ ነገር ሊሰማችሁ እንደሚችል አስባለሁ፡፡ ከሌሎች ከተሞች የተለየ ነው፡፡ የባንጎር ከተማ ሆሊውድ ከሚባል ከተማ አጠገብ ነው ያለችው፡፡ የማያቋርጥ ምስጋና ታሪክ ያላት ባንጎር ብዙየእግዚአብሔር ጉብኝት ታሪክም አላት፡፡ አጠገብዋ ያለችው ሆሊውድ ግን እስከ

ቅርብ ጊዜ ድረስ እንዲህ ያለ ጉብኝት ኖሯት አያውቅም። በነገራችን ላይ ሆሲውድ፣ ስሟን ያገኘችው ለድሩዶች አምልኮ ቅዱስ የሆኑ ዛፎች ስለ ነበሩዋት ነው። ለምን የእግዚአብሔር መንፈስ ሆሊውድ ላይ እንደማያርፍ ማወቅ እስከ ቻልንበት ጊዜ ድረስ በዚያ ምንም ነገር አልሆነም ነበር። በላይዋ ያለውን ሰይጣናዊ ኃይል መስበር እንደሚገባ ስንረዳ በዚያ ቦታ የእግዚአብሔርን መንፈስ መፈታት ሊሰማን ቻለ።

በአጭር አነጋገር፣ ስለታላቅነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ። ለእናንተ መልካም በመሆኑ፣ ላደረገላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን ወድሱት። ውዳሴ ማቅረብ ከፍ ያለ ሥነ - ልቦናዊ ተግባር አለው። እምነታችንን ይገነባል። ቆም ብለን ስላደረገልን እግዚአብሔርን ባመሰገንን መጠን፣ ቀጥሎ የምንለምነውን እንደሚያደርግልን ለማመን የበለጠ ይቀለናል። በተጨማሪ፣ መልካም ምግባርም ነው።

## አምልኮ

በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች ለአምልኮ ያለን አመለካከት በጣም ደካማ ነው። አምልኮ መዝሙሮችና አዝማቾች መዘመር አይደለም፤ አምልኮ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ማወጅ አይደለም። በአንደበት መግለጽ ምስጋና ውደሴን ይመለከታል፤ አምልኮ ግን የዝንባሌ ጉዳይ ነው።

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን፣ «አምልኮ» ተብለው የተተረጎሙ አብዛኞቹ ቃሎች በዋነኛነት አካላዊ ዝንባሌን የሚመለከቱ ናቸው። የተለያዩ ዝንባሌዎች በተለያዩ ቃላት ተወክለዋል። አንደኛው ራስን ዝቅ ማድረግ ማለት ነው። ሌላው፣ ላይኛው የአካል ክፍልን ወደ ፊት ሰበር አድርጎ እጆችን መዘርጋት ማለት ነው። ሦስተኛው በሚመለከው ፊት ፊትን ወደ መሬት አድርጎ ሙሉ በሙሉ መሬት ላይ መዘርጋት ማለት ነው። ውዳሴና ምስጋና በአንደበት የሚገለጹ ማለትም፣ ከአፋችን የሚወጡ ናቸው፤ አምልኮ ግን የሚኖረን ዝንባሌ(ወይም የሰውነት ሁኔታ ) ነው።

ስድስተኛው የኢሳይያስ ምዕራፍ ላይ ነቢዩ ስለ እግዚአብሔር ዙፋን ራዕይ ይገልጻል። ከዙፋኑ በላይ የእግዚአብሔርን ዙፋን የሚከብቡ



ነበልባላዊ ፍጡራን ሱራፌልን አየ። እያንዳንዱ ስድስት ክንፎች እንዳሉትና እንዴት እንደሚጠቀምበት አየ።

በአንዱ ክንፎች ጥንድ ሱራፌል ፊቶቻቸውን ይሸፍናሉ፤ በሁለተኛው ጥንድ እግሮቻቸውን ይሸፍናሉ፤ በሦስተኛው ጥንድ ይበርራሉ። ከዚህ ለአምልኮ ሁለት ጥንዶች እንደ ተሰጡትና (ፊቶቻቸውንና እግሮቻቸውን በመሸፈናቸው እንደሚታየው) ሦስተኛው ጥንድ ለአገልግሎት እንደ ተሰጠ (በመብረራቸው እንደሚታየው) እንረዳለን። ይህ ከማገልገል በፊት አምልኮ እንደሚደምቅና፣ አምልኮ ከአገልግሎት እጥፍ አስፈላጊ መሆኑን ይነግረናል።

አምልኮ ፊትንና አካልን የመሸፈን ያህል ነው። ጎንበስ ብሎ ራስን ሰበር ማድረግ ነው። እርግጥ ነው፣ ይህ አካልን ብቻ የሚመለከት መሆን የለበትም፤ እየተነጋገርን ያለነው በመንፈስ ስለሚሆን ነገር - መንፈሳችን ወደ እግዚአብሔር ስለ መቅረቡ ነው። ኢየሱስ፣ «በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል» ብሏል (ዮሐንስ 4:23)።

ይህ፣ «እናንተ ግን በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ» በሚለው በጌታ ጸሎት ቀርቧል (ማቴዎስ:6፣9)። መጀመሪያ እግዚአብሔርን ከጠራን በኋላ፣ «ስምህ ይቀደስ። ስምህ ቅዱስ ነው። በስምህ መጠቀም ራሱ መታደል ነው። በአክብሮት፣ ዝቅ በማለት፣ በቅዱስ ፍርሃት፣ በመደነቅና በክብር ስምህን እንጠራለን» እንላለን። ይህ አምልኮ ነው - ልብ በእግዚአብሔር ዝቅ የሚልበት ነው።

## ልመና

ሰዎች ስለ «ጸሎት» ሲናገሩ፣ ስለ ልመና አካላዊና ቁሳዊ ችግራቸው እንዲሟላ ስለ መጠየቅ ማለታቸው ነው። ጸሎት ግን ስለምንፈልገው ነገር ማሰብና እርሱን መለመን ብቻ እንዳይደለ አስታውሱ። ጸሎት በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ዓላማ መረዳትና ያ ዓላማ ይፈጸም ዘንድ መጸለይ ነው።

እንደ ገና 1 ዮሐንስ 5:14-15 እንመልከት፣ «በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል፤ የምንለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን፣ ያመንነውን ነገር እንደተቀበልን

እናውቃለን።»

ይህ ልመና ነው- ለነገሮችና ለሁኔታዎች መጠየቅ ነው። ምዕራፍ 2 ላይ ይህን ጥቅስ ተመልክተናል፤ እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ እንደሚሰማን ተምረናል። እንደሚሰማን ካወቅን፣ የለመንነውን ነገር አግኝተናል። ልመና ካቀረባችሁና የለመናችሁት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ የለመናችሁትን እንዳገኛችሁ አውቃችሁ ተነሡ።

ነገሮችን ከእግዚአብሔር የማግኘት ምስጢር መቀበል ነው። ብዙ ሰዎች ይለምናሉ፤ ግን አይቀበሉም። «በመስቀል፣ በመስቀል ብርሃን ባየሁበት» በሚለው ጥንታዊ መዝሙር እንደሚከተለው የሚነበብ አንድ ስንኝ አለ

ስትጸልይ፣ ስትጸልይ፣ በማመን እየጸለይህ ነው ወይ?

በመጠየቅና በመቀበል በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ እየጸለይህ ነው ወይ? ይላል።

ቁም ነገሩ መጠየቅና (መለመን) መቀበል እንጂ፣ መለመን ብቻ አይደለም። ይህን ብዙ ጊዜ አይቻለሁ። እግዚአብሔር አንድን ሰው በፈውስ ይነካዋል፤ ሰውየው ግን አይቀበለውም። የልመናን መልስ የማንቀበልበት አንዱ መንገድ ስለዚያው ጉዳይ መጸለይን መቀጠል ነው። አንዳንድ ሰዎች እስኪያምኑ ድረስ ይጸልያሉ፤ በመጨረሻ እምነትን በማጣት ይወጣሉ።

ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጠንከር ያለ ነው ኢየሱስ «ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት እድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል» ሲል መለመንን በተመለከተ ስለዚሁ ጉዳይ መናገሩ ነበር (ማርቆስ 11:24)። አንዳንድ ትርጉሞች፣ «እንደ ተቀበላችሁ እመኑ» ይላሉ፤ ሆኖም፣ ይህ ትክክል አይደለም - ወይም ቢያንስ ቃል በቃል አይደለም ። እዚህ ላይ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ይበልጥ ትክክል ነው። «እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ»። የለመናችሁትን ነገር የምትቀበሉት መቼ ነው? ሙልሱ ስትጸልዩ።



ሆኖም፣ ይህንን አስተውሉ - መቀበል ማግኘት ማለት አይደለም። መቀበል ስጉዳዩ አልባት ይሰጣል፤ ማግኘት ግን እሱን የሚከተል ልምምድ ነው። የለመናችሁትን በእውን የማግኘት ልምምድ ሊዘገይ ይችላል፤ ሆኖም፣ በእምነት ስንጸልይ የጸለይንበትን ነገር እንዳገኘን እንቀበላለን። ለምሳሌ ያህል ገንዘብ ነክ የሆነ ችግር ገጠማችሁ እንበል ትጸልያላችሁ። ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ተገናኛችሁ ነው። ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ሐሙስ ቀን ሁለት ሺህ ብር ያስፈልገኛል›› ትላላችሁ። ከዚያ በኋላ፣ «እግዚአብሔር ሆይ ተመስገን» ትላላችሁ። ተቀብላችሁታል። ሁኔታውን በተመለከተ ምንም የተለወጠ የለም ግን ተቀብላችሁታል ከዚያ ታገኙታላችሁ።

በመካከል ያለውን ጊዜ፣ አንዳንዴ፣ «መስመሩ እንደ ተያዘ መጠበቅ» እለዋለሁ። እስቲ ምሳሌ ልስጣችሁ። መጀመሪያ ሩትን በኢየሩሳሌም ሳገኛት ሙሉ በሙሉ ሽባ ነበረች። ደረጃ ስትወጣ ወድቃ ዲስኳ ክፉኛ ተጎድቶ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ የምታሳልፈው አልጋ ላይ ነበር፤ ፋታ የማይሰጥ ሕመም ነበራት። ከተሰበረው ዲስኳ በተጨማሪ የጀርባ አጥንት መታጠፍም ደርሶባት ነበር። በሁለቱም ከፋ ያለ ሕመም እያደረሰባት ነበር

የጀርባ ችግር ለነበረባቸው ሰዎች እግዚአብሔር የተለየ እምነት ሰጥቶኝ ነበር፤ ኃላፊነት ተሰምቶኝ ሄጄ ጸለይኩላት በዚያ ጊዜ እኔ ሚስት እየፈለግሁ አልነበረም። ያ ተጨማሪ ጥቅም ነበር!

ከጸለይኩ በኋላ ወዲያውኑ ወይም በሩት ሁኔታ አስደናቂ መሻሻል ባለመኖሩ በመጠኑ ቅር ብሎኝ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እርሷ የእምነት ሴት መሆንዋ እግዚአብሔር ይመስገን። ለሌሎች እንደምናገረው ሁሉ ለእርሷም፣ «ከእንግዲህ ከልዕለ ተፈጥሮአዊው ኃይል ጋር ተያይዘሻል፤ ይህ እንደተጠበቀ ይሁን» አልኳት።

ያንን የምታደርጉት እንዴት ነው? በመሠረቱ፣ እግዚአብሔርን በማመስገን ነው። ለምሳሌ፣ አካላዊ ፈውስን በተመለከተ ልመና አቅርባችሁ ከሆነ፣ «ጌታ ሆይ ተመስገን። ደስ ብሎኛል። ኃይልህ አካሌ ውስጥ በመሥራት ላይ ነው» እንላለን። ሕመም በተሰማችሁ ወይም ባያችሁ ቁጥር፣ «ጌታ ሆይ ተመስገን። ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይልህ አካሌ ውስጥ በመሥራት ላይ ነው» ትላላችሁ። በዚያ መልኩ ምላሽ ስትሰጡ ፈውሳችሁ የተሟላ ይሆናል።

ሩት ግንኙነቱ እንደ ተያያዘ እንዲቀጥልና ለፈውሷ ዘወትር እግዚአብሔርን ለማመስገን እምነቱና ጥንካሬው ነበራት። የጀርባ አጥንቷ በጥቂቱ መሻሻል ጀመረ። በዚህ ጊዜ እንደ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለሰውነቷ ጥንቃቄ ማድረግ በእውነት ምን ማለት እንደ ሆነ አስባ እንደማታውቅ ተረዳች። መስመሩ እንደ ቀጠለ እንዲቆይ ስታደርግ፣ እንቅስቃሴን በመሳሰለ ነገር ለሰውነቷ ጥንቃቄ ማድረግንም ጀመረች።

ከብዙ ወሮች በኋላ የሐሴት መንፈስ ሕዝቡ ላይ የወረደ ጊዜ ስብሰባው ውስጥ ነበረች። ስለ አካልዋ ሁኔታ እንኳ ሳታስብ ተነሥታ በጌታ ፊት ሽብሽባ ማድረግ ጀመረች የተሰበረ ዲስኳም ወዲያውኑ ተፈወሰ። ግን፣ የግንኙነት መስመሩ ሁሌም እንደ ተጠበቀ ነበር። ከዓመቶች በኋላ የተሰበረ ዲስክ አልነበረባትም፤ የጀርባ አጥንቷም ቀጥ አለ። ከልጅነቷ ጊዜ ጀምሮ ቀጥ ብሎ አያውቅም ነበር። ያ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር መያያዝ፣ የልመናችሁን መልስ እስከታገኙ ድረስ መስመሩ እንደተጠበቀ እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

ጸሎትን በተመለከተ የእምነት መኖር ብቻ በቂ አለመሆኑን አያችሁ? እምነትና ትዕግስት ያስፈልጋችኋል። አብርሃምን አስቡ። አንድ ልጅ እንኳ ሳይኖረው እግዚአብሔር የብዙ ሕዝብ አባት እንደሚያደርገው ቃል ገብቶለት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «አብርሃምም በትዕግሥት ከጠበቀ በኋላ የተሰጠውን ተስፋ አገኘ» ይላል (ዕብራውያን 6፡15)። ምን ያህል ጊዜ ቆዩ? ሃያ አምስት ዓመት። ልጅ የወለደ ጊዜ 99 ዓመት ሆኖት ነበር። የተጠራጠረበትን፣ የግንኙነት መስመሩን ለማቋረጥ የተፈተነበትን ብዙ ጊዜ አስቡ።

እብራውያን 10፡36፣ «የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽማችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃሉን እንድትቀበሉ፣ ጸንታችሁ መቆም ያስፈልጋችኋል» በማለት ይነግረናል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግና የተስፋውን ቃል በመቀበል መካከል ባለው ክፍተት ሁለት ነገሮችን ማድረግ ትችላላችሁ። የግንኙነት መስመሩ እንደ ተጠበቀ እንዲቀጥል ማድረግ ወይም ደግሞ ማቋረጥ። የግንኙነት መስመሩን ካቋረጣችሁ ምንም አታገኙም። የግንኙነት መስመሩ



እንደ ተጠበቀ እንዲቀጥል ካደረጋችሁ ማንኛውንም ነገር ታገኛላችሁ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድነው? ጸንታችሁ መቆማችሁ ነው። የግንኙነት መስመሩ እንደ ተጠበቀ እንዲቀጥል በማድረጉ ሂደት የሚረዳን ነገር ትክክለኛውን ቃል መመስከር - ማለትም እምነታችንን በድፍረት በአንደበታችን ማወጅ ነው። እጅግ ታላቅ ኃይል ያላቸው እምነታችንን የምንገልጽባቸው አንዳንድ መንገዶች መኖራቸውን ተረድቻለሁ - የእግዚአብሔር ኃይል እንዲፈታ ያደርጋሉ እኛንም ያበረታቱናል ያጠነክሩናል። ብዙ ጊዜ ጠዋት ወይም የቀኑ ማብቂያ ላይ ስጸልይ እነዚህ ቀላል ምስክርነቶችን አውጃለሁ። ለምሳሌ ያህል በሳምንቱ ውስጥ ጥቂት ቀናት የምናገረው አካልን የሚመለከት ዐረፍተ ነገር የሚከተለው ነው -

> ሰውነቴ በኢየሱስ ደም የተዋጀ፣ የነጻና የተቀደሰ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው። የአካል ብልቶቼ ለእርሱ አገልግሎትና ለእርሱ ክብር ለእግዚአብሔር የተገዙ የጽድቅ መሣሪያዎች ናቸው። ዲያብሎስ በእኔ ውስጥ ምንም ቦታ የለውም፤ በእኔ ላይ ምንም ኃይል የለውም፤ በእኔ ላይ እልባት ያላገኘ ያልተፈታ ነገር የለውም። በኢሱስ ደም ሁሉም መፍትሔ አግኝቷል። በበጉ ደምና በምስክርነቴ ቃል ሰይጣንን አሸንፋለሁ።

ሌላው በጣም የምወደው ጥቅስ 2ቆሮንቶስ 2፡14 ላይ ያለው፣ «ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድራጊነት እያዞረ ለሚመራኝ፣ የእውቀቱንም መዐዛ በእኛ አማካኝነት በየስፍራው ለሚገልጥ አምላክ ምስጋና ይሁን» የሚለው ነው። ያ ቃል ለእኔ እጅግ ውብ ነው - በክርስቶስ ድል ከተመላለስን፣ ከዚያ ድል፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚረጭና የምናገኛቸውን ሰዎች ሁሉ የሚባርክ መዐዛ ይወጣል።

ከእግዚአብሔር የምንለምናቸው ነገሮችን በተመለከተ ጥቂት ተጨማሪ ምሳሌዎች ልስጣችሁ። ይሁን እንጂ፣ ከማንኛውም ነገር በላይ ይህን አስታውሱ - አንዳች ነገር ከእግዚአብሔር የምትለምኑ ከሆነ ምንግዜም

በምስጋና ጀምሩ። በቀጥታ ወደ መለመን አትሂዱ። ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት የሌሎችን በደል ለመዘርዘር አትጠቀሙበት። አንዳንዴ በሌላው ሰው ሕይወት መስተካከል ያለበትን ነገር እናይ ይሆናል። ሁኔታው እንዲስተካከል ቀና በሆነ መልኩ ለመጸለይ ነፃነት ይሰማን ይሆናል፤ ይሁን እንጂ በዚያ ሰው ሕይወት ወይም አገልግሎት እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ነገር እስክናገኝ ድረስ እንደዚያ ያለ ጸሎት አለመጸለይን መርሕ እናድርገው።

ለምሳሌ አንዳንድ የአገልግሎቴ ገጽታዎችን በተመለከተ ከእግዚአብሔር አንዳች ነገር መለመን እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ አገልግሎቴ በየጊዜው እየሰፋ በመሄዱ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ከዚያም በዚያ ሥራ እየተሳተፉ ስላሉ ሰዎች ሁሉ አመሰግነዋለሁ። ከዚያ ልመናዬን ማቅረብ እጀምራለሁ። ለጥበቃና እየሰፋ በመሄድ ላይ ላለው የሬዲዮ አገልግሎት፣ በዚያ ውስጥ እያገለገሉ ስላሉ ሰዎች ምሪት እለምናለሁ። ከዚያ ይህን ጸሎት ስለሰማኝ ዘወትር እርሱን በማመስገንና እነዚህን ነገሮች እንደ ተቀበልሁ በማመን እጸናለሁ። ወይም ደግሞ ስለ እስራኤል እየጸለይሁ ነው እንበል። ኪዳኑን በመጠበቁና ለእስራኤል ታማኝ በመሆኑ፣ ተስፋው ለእነርሱ ይፈጸም ዘንድ ቃሉን እየጠበቀ በመሆኑ አመሰግነዋለሁ። ከዚያም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የተነሣሣ አመራር በእስራኤል እንዲኖር፣ ለዘመናት የዘለቀውን መከፋፈል የሚፈውስና እስራኤልን ወደ ርስቷ የሚያደርስ አመራር እንዲኖር በመጠየቅ የልመናየልመና ጸሎት አንዳንዴ አጥብቀን እንድንይዝ ከእኛ በኩል ጽናትና ትዕግሥት የሚጠይቅ የመቀበል ጸሎት ነው። ወደ ፊት እንደምንመለከተው ይህ መዝጊያን ማንኳኳቱን ከሚቀጥል ያለማቋረጥ ጸሎት የተለየ ነው።

## ምልጃ

ምልጃ ከክርስትና ሕይወት የላቁ ጥበቦች አንዱ ሲሆን፣ ለመጫወት በጣም የሚያስቸግር መሣሪያ ነው። ብዙ ልምምድ፣ ብዙ መረዳት፣ ብዙ በሳልነት ይጠይቃል። መማለድ ቃል በቃል፣ «በመካከል መግባት» ማለት



ነው። የሚማልደው ሰው በእግዚአብሔርና በሚጸልይላቸው ሰዎች መካከል የሚገባ ሰው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንዳንድ ገደብ ያለፉ ጉዳዮች ምሳሌ ይሰጣል። አንዱ በእግዚአብሔርና በዐመፀኛዋ የሰዶም ከተማ መካከል አብርሃም የቆመበት ጊዜ ነው። ዘፍጥረት 18 እግዚአብሔርና ሁለት መላዕክቶች ወደ አብርሃም ቤት የመምጣታቸውን ታሪክ ይነግረናል - ድንቅ እንግድነት አቀባበል። አብርሃም እግሮቻቸውን የሚታጠቡበት ውሃ አቀረበላቸው፤ ወይፈን አረደላቸው፤ ዛፉ ጥላ ሥር ሆኖ ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ።

ከዚያም ወደዚያ የመጣበትን ዓላማ እግዚአብሔር ለአብርሃም መናገር ጀመረ። ሁኔታውን ለማየትና ተገቢውን ነገር ለማድረግ ወደ ዐመፀኞች ሰዶምና ገሞራ ከተሞች እየሄደ ነበር።

ከእምነት ወደ ኋላ በማለት ሁኔታ ውስጥ ያለው የወንድሙ ልጅ ሎጥ በሰዶም እየኖረ ስለ ነበር ይህ ጉዳይ አብርሃምን አሳስበው ሰዶም ላይ ፍርድ ከመጣ ሎጥና ቤተሰቡ የፍርዱ ተጠቂዎች እንደሚሆኑ አብርሃም አውቋል። እዚህ ላይ፣ «ሰዎቹም (ማለት ሁለት መላእክት) ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅንተው ሄዱ፤ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቆመ ነበር» (ዘፍጥረት 18፡22)።

የማላጁ ቦታ ይኸው ነው። አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቆመ፣ «ጌታ ሆይ፣ እስቲ ጥቂት ቆይ። ለአንተ የምናገረው አለኝ» አለ። በአንድ መልኩ እግዚአብሔርን አዘግይቶታል ማለት ይቻላል። ከዚያ የድርድር ጊዜ ጀመረ። ሃምሳ ጻድቃን ቢያገኝ ከተሞቹን ይምራቸው እንደ ሆነ አብርሃም እግዚአብሔርን ጠየቀ፣ ከዚያ ዐሥር ጻድቃን ቢያገኝ ሰዶምን ለመማር እግዚአብሔር እስኪስማማ ድረስ ቁጥሩን ዝቅ እያደረገ ሄደ።

ይህ ታላቅ መገለጥ ነው። አብርሃም በነበረበት ዘመን የሰዶም ሕዝብ ምን ያህል እንደ ነበር ለማወቅ ሞክሬአለሁ። ወደ ሌላው ዝርዝር ሳልገባ ሰዶም ዋና ከተማ ነበረች፤ የነዋሪዎቿ ብዛት ከአሥር ሺህ ያነሰ አይሆንም እንደዚያ ከሆነ፣ ለአሥር ጻድቃን ሲል የከተማዋ አሥር ሺህ ዐመፀኞችን እንደሚምር እግዚአብሔር እየተናገረ ነበር ማለት ነው።

ይህን ተመጣጣኝ ለማወቅ የሒሳብ ባለሙያ መሆን የለባችሁም፤ ከሺህ አንድ ማለት ነው። ኢዮብ 33፡23፣ «ትክለኛውን መንገድ ለሰው ያመለክት ዘንድ፣ መካከለኛም ይሆንለት ዘንድ ከሺህ አንድ መልእክተኛ ቢገኝ ...» ይላል። መክብብ 7፡28፣ «ከሺህ ወንዶች መካከል አንድ ቅን ሰው አገኘሁ» ይላል። የአንድን ሰው ጽድቅ የሚያመለክት ተመጣጣኝ ቁጥር ይመስላል።

ያም ሆነ ይህ፣ ጌታ በከተማው ውስጥ አሥር ጻድቃን እንኳ እንዳላገኘ ከታሪኩ መደምደሚያ እንረዳለን፤ እርሱም፣ «የሚያቃጥል ዲንና እሳት አዘነበባቸው» (ዘፍጥረት 19፣24)።

ገደብ ያለፈ ሌላው የምልጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ሕዝቡ የወርቅ ጥጃ ከሠሩ በኋላ ሙሴ ለእስራኤል የጸለየ ጊዜ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆንና ከእርሱ ኪዳኑን ለመቀበል ሙሴ ወደ ሲና ተራራ ወጥቶ እንደ ነበር ከዘጸአት 32 እናነባለን። አርባ ቀን ያህል በአካባቢው ስላልነበረ ሕዝቡ፣ ‹‹ሙሴ ጠፍቶአል›› የሚል መደምደሚያ ላይ ደረሱ። ‹‹ምን እንዳገኘው አናውቅም። እኛ ደግሞ አምላክ ያስፈልገናል። አሮን ‹‹አምላክ ሥራልን›› አሉ። የወርቅ ጉትቻዎቻቸውን አቀለጠና የወርቅ ጥጃ ሠራላቸው። የእስራኤል ሕዝብ ዙሪያውን መጨፈርና ማምለክ ጀመሩ።

እግዚአብሔር በድንገት ንግግራቸውን ያቋረጠ ጊዜ ሙሴ ከተራራው ጫፍ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር። ‹‹ሙሴ፣ ከተራራው ግርጌ ምን እየተደረገ እንደ ሆነ ማወቅ አለብህ አለው። በሁለቱ መካከል የነበረ በጣም የመቀራረብ ንግግር በአንድ መልኩ አስደናቂ ነበር። ባነበብኩት ጊዜ ሁሉ ፈገግ እላለሁ። እግዚአብሔርም ሆነ ሙሴ ለእስራኤል ኃላፊነት መውሰድ አልፈለጉም። እያንዳንዳቸው ኃላፊነቱን ወደ ሌላው ወገን ገፍተዋል።

> ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ ከግብፅ ያወጣኻቸው ሕዝብህ ስተዋልና ውረድ አለው፤ ካዘዝኃቸውም ፈቀቅ ለማለት ፈጣኖች ሆኑ፤ ለራሳቸውም በጥጃ ምስል የተቀረጸ ጣዖትን ሠሩ፤ ለእርሱም ሰገዱለት፤ ሠውለቱም፤



> እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ እነዚህን ሕዝብ አይቻቸዋለሁ፤ አንገተ ደንዳኖች ናቸው፤ አሁንም በእነርሱ ላይ ቁጣዬ እንዲነድና እንዳጠፋቸው ተወኝ፤ ከዚያም አንተን ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ። ዘጸአት 32፡7-10

ሙሴ ካልተስማማ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ምንም ለማድረግ አለመፈለጉን እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። ‹‹ሙሴ፣ ከመንገዱ ዘወር በልልኝና በእነዚህ ሰዎች ላይ የማደርገውን ላድርግ። አየህ ሙሴ፣ ጨርሼ ላጠፋቸውና ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጠሁትን ተስፋ መፈጸም እችላለሁ አለው። አንተን ይህን ታላቅ ሕዝብ የማስገኝበት አድርጌ በቀላሉ አጸናሃለሁ›› አለው።

ይህ አባባል ትርጉም ይሰጣችኋል? ለእኔ ሰጥቶኛል። ሙሴ፣ ‹‹አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ ጨርሰህ አጥፋቸው። እንዲያውም እኮ ከግብፅ ምድር መርቼ ካወጣኋቸው ጊዜ ጀምሮ በእኔ ላይ ሸክም ከመሆናቸው ውጪ ምንም ማለት አይደለም። በእኔ ጀምር የዚያ ታላቅ ሕዝብ አባት እሆናለሁ›› ማለት ይችል ነበር።

ሙሴ ግን እንደዚያ አላለም። ‹‹ነገር ግን ሙሴ የአምላኩን የእግዚአብሔርን ቸርነት ፈለገ፤ እንዲህም አለ፣ ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ፣ በታላቅ ሥልጣንህና በኃያል ክንድህ ከግብፅ ባወጣኸው ሕዝብህ ላይ ቁጣህ ለምን ይነዳል?›› አለ (ቁጥር 11)። በሌላ አነጋገር፣ ‹‹የአንተ እንጂ፣ የእኔ አይደሉም! እኔ አልችላቸውም! በእነርሱ ላይ ያሻህን የምታደርግ አንተ ነህ›› ማለቱ ነበር።

ከዚያ ይህ ትሑት የጸሎት ሰው ወደ ሥራ ሄዶ በመጀመሪያ፣ የእርሱ ዋነኛ ሐሳብ የእግዚአብሔር ክብር መሆኑን ገለጸ። እነዚህን ሰዎች ከግብፅ ያወጣ እግዚአብሔር እንደ መሆኑ መጠን፣ ግብፃውያን መጀመሪያውኑ ለእነርሱ ክፉ እቅድ ነበረው ይላሉ በማለት ተከራከረ። ቀጥሎ ተስፋውንና ኪዳኑን ለእግዚአብሔር አስታወሰ።

> ለባሪያዎችህ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለእስራኤል ‹‹ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ፤ ለዘርህም ተስፋ አድርጌ የሰጠኋቸውን ይህችን ምድር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም ርስታቸው ትሆናለች በማለት በራስህ የማልኸውን አስታውስ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ታገሠ፤ በሕዝቡም ላይ አመጣባቸዋለሁ›› ያለውን ጥፋት አላመጣባቸውም፡፡ ቁጥር 13-14

የእግዚአብሔርን እጅ ካዘገየ በኋላ ወደ ተራራው ግርጌ ሄዶ ከሕዝቡ ጋር ተነጋገረና እንደ ገና ተመለሰ፡፡

> ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፣ እንዲህ አለው፤ ‹‹ወዮ እነዚህ ሕዝብ የሠሩት ምን ዐይነት የከፋ ኃጢአት ነው! ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት ሠሩ፡፡ አሁን ግን አቤቱ ኃጢአታቸውን ይቅር በል፤ ያለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍ እኔን ደምስሰኝ፡፡ ቁጥር 31-32

ከዚህ ምልልስ ለመለመንና ለመማለድ ለጸሎት የነደደ የሙሴን ልብ እናያለን ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ እነዚህ ሰዎች ከባድ ኃጢአት ፈጽመዋል፡፡ የአንተ ቁጣ ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም፣ ምሕረት እንድታደርግላቸው እለምንሃለሁ፡፡ አለበለዚያ ግን፣ ጌታ ሆይ፣ የእነርሱ ፍርድ እኔ ላይ ይሁን፡፡
መዝሙር 106 ይን ሁኔታ በተመለከተ መለኮታዊ ማብራሪያ ይሰጣል

> ‹‹ በኮሬብ ጥጃ ሠሩ፤ ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ፡፡ ክብራቸው የሆነውንም ሣር በሚበላ፣ በበሬ ምስል ለወጡ፡፡ በግብፅ ታላቅ ነገር ያደረገውን፣ ያዳናቸውን አምላክ ረሱ፤ እርሱ ግን በካም ምድር ድንቅ ሥራ፣ በቀይ ባሕርም አስደናቂ ነገር አደረገ፡፡ ስለዚህ በመቅሠፍቱ



> እንዳያጠፋቸው ይመለስ ዘንድ፣ እርሱ የመረጠው ሙሴ በመካከል ገብቶ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፣ እንደሚያጠፋቸው ተናግሮ ነበር፡፡ ››ቁጥ 19-23

የአንድ ሰው ኃጢአት ክፍተት ሲፈጥር የሚማልድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ይቆምና ‹‹ጌታ ሆይ፣ ክፍተቱን ሞልቻለሁ፡፡ መጀመሪያ እኔ ላይ ሳያርፍ የምትሰነዝረው ምት እነርሱ ላይ አያርፍም›› ይላል፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደምንመለከተው ይህ ምሕረት የሚለምን የጸሎተኛውንም ሁኔታ ያመለክታል፡፡

ይህ የመማለድ ብቸኛ መንገድ ባይሆንም በጣም ከፍ ያለው ነው፡፡ ማላጁ እግዚአብሔር ነው፡፡ ችግር ተኮር አይደለም፤ ሰው ማድረግ የሚችለው ወይም የማይችለው ነገር ላይ አያተኩርም፡፡ እግዚአብሔር ማድረግ ለሚችለው ነገር ራእይ አለው፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ማላጅ ከታጣ ለእግዚአብሔርና ለሰው ልጅ ኃላፊነታችንን ላለመወጣታችን ጉልህ አመልካች ነው፡፡ ለቤተሰቡ ይጸልይ የነበረው የኢዮብ ታሪክ ሌላው ምሳሌ ነው፡፡

> ወንዶች ልጆቹም ተራ በተራ በየቤታቸው ግብዣ ያደርጉ ነበር፤ ከእነርሱም ጋር እንዲበሉና እንዲጠጡ ሦስቱን እኅቶቻቸውን ይጋብዙ ነበር፡፡ የግብዣው ጊዜ ካለፈ በኋላ ኢዮብ ልኮ ያስመጣቸውና፣ ‹‹ምናልባት ልጆቼ ኃጢአት ሠርተው እግዚአብሔርንም በልባቸው ረግመው ይሆናል›› በማለት ጠዋት በማለዳ ስለ እያንዳንዳቸው የሚቃጠል መሥዋዕት (ያ ማለት ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች - ዐሥር የሚቃጠል መሥዋዕት) በማቅረብ ያነጻቸው ነበር፤ ኢዮብ ይህን ዘወትር ያደርግ ነበር፡፡ ኢዮብ 1፡4-5

ይህ ምልጃ ነው፡፡ ምን ያህል የሌሎች ሰዎችን ኃጢአት እንቀበላለን? የሰው አእምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መድረስ የሚችል አይመስለኝም፡፡ ሆኖም በተወሰኑ መልኩ በምልጃ የሌሎች ሰዎችን ኃጢአት መውሰድ እንችላለን፡፡ ለወንዶችና ሴቶች

ልጆቹ ኢዮብ ያደረገው ይኸንኑ ነበር። «ምናልባት በተለያየ አጋጣሚ ኃጢአት አድርገው ቢሆን፣ ይህን መሥዋዕት አቀርብላቸዋለሁ» አለ። ያንንም ለማድረግ ጠዋት በማለዳ ተነሣ።

በኅብረት ስለሚደረግ ምልጃ ሳስብ፣ ለመላው አካል መሥዋእት ለማቅረብ ሕዝቡን በመወከል በእግዚአብሔር ፊት ቆመው፣ «ጉባኤውን ወክለን እዚህ አለን። ጌታ ሰው ኃጢአት ያደረገ ሰው ቢኖር፣ እኛ መሥዋዕት እናቀርባለን። ለሕዝቡ መናገር ከፈለግህ እዚህ የለም። እኛ ግን እዚህ ነን» በማለት የተሰበሰቡ ሰዎችን አስባለሁ።

ምናባትም፣ ኢዮብ ባቀረበው መሥዋዕት ይህን ያህል አልተጠቀመም፤ ምክንያቱም ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ በቅጽበት ሞተውበታል። ሆኖም፣ ለእኔ፣ በተለይም፣ ወዳጆቻችንን ካጣን ሰዎች በጣም ደስ የሚለኝን ጉዳይ ልነግራችሁ እወዳለሁ። በሚገባ ካነበባችሁ፣ ኢዮብ ፈተናውን ካለፈ በኋላ ቀድሞ ከነበረው ዕጥፍ እግዚአብሔር እንደ ሰጠው መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ይናገራል።

> እግዚአብሔርም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን የኢዮብን ሕይወት ባረከ። እርሱም ዐሥራ ሁለት ሺህ በጎች( ቀድሞ ሰባት ሺህ)፣ ስድስት ሺህ ግመሎች (ቀድሞ ሦስት ሺህ)፣ አንድ ሺህ ጥማድ በሬዎች(ቀድሞ አምስት መቶ)፣ አንድ ሺህ እንስት አህዮችም ነበሩት(ቀድሞ አምስት መቶ) ደግሞም ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩት። ኢዮብ፡42፡12-13

ይሁን እንጂ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን እግዚአብሔር እጥፍ አላደረገለትም። ቀድሞ የነበረውን ነው የሰጠው? መልእክቱ ምንድንነው? ቀድመውት ሄዱ እንጂ ኢዮብ ቀድሞ የነበሩት ወንዶችችና ሴቶች ልጆቹን አላጣም። ወዳጃችሁን ካጣችሁ ወይም ወዳጃችሁን የምታጡ ከሆነ፣ ያንን በልባችሁ ያዙ። የኢዮብ መሥዋዕት ለልጆቹ ሠርቷል። ቁጥራቸውን እጥፍ ማድረግ አልፈለገም ምክንያቱም በዘላለም ውስጥ አሁንም ሕያው ናቸው።



ለቤተሰባችሁ እየጸለያችሁ ከሆነ - ብዙዎቻችን ለቤተሰባችን አባሎች መጸለይ አለብን - በርቱ። ጠዋት በማለዳ ተነሡና ተገቢውን መሥዋዕት አቅርቡ። ለውጤቱ በእግዚአብሔር ተማመኑ።

በዳንሁ ጊዜ፣ እኔ እንደማውቀው ከመላው ቤተሰባችን ዳግም የተወለደ እኔ ብቻ ነበርኩ። ቤተ ሰቦቼ ጥሩ ሰዎች ነበሩ፤ የዚያ ዓይነት ሰዎች ግን አልነበሩም። ለወላጆቼ በጣም ብዙ፣ ብዙ ዓመቶች ጸለይኩ። Rኪንሰን በሚሉት ሕመም ታምማ በነበረ ጊዜ እናቴን ወደ ጌታ የመምራት ደስታ አግኝቻለሁ። ምናልባትም መረዳትና ምላሽ መስጠት የምትችለው በዚያ ጊዜ ብቻ ሲሆን ይችላል። እንድትጸልይ በጠየቅኋት ጊዜ እጇን ወደ ላይ መዘርጋቷ ተአምር ሆኗል። በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በምንም ዓይነት እጇን ወደ ላይ የምታነሣ ሴት አልነበረችም።

አንድ ጊዜ ከዳንሁ በኋላ ብዙ ሳይቆም አልጋ ላይ ጋደም ብዬ መዘመር ወይም በልሳን ማዜም ጀመርኩ ስለ ምን እየጸለይኩ እንደ ነበር የማውቀው አልነበረኝም፤ ጌታ ግን ትርጉሙን ሰጠኝ። ጸሎቴ፣ «ጌታ ሆይ፣ አባቴን አድን» የሚል ነበር። ያ ለእኔ ታላቅ በረከት ነበር፤ ምክንያቱም እኔ እስከማውቀው ድረስ በዚያ ጊዜ ስለ አባቴ እያሰብኩ እንኳ አልነበረም። አባቴን የሚያድነው በጌታ መታመን ነበረብኝ። ከዳነ መልካም ያ ተአምር ነው! አባቴ ጥሩ ሰው ነበር፤ ሃይማኖተኛ ግን አልነበረም። ምልጃን በተመለከተ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ልስጣችሁ። ይህ ስለ ነቢይቱ ሐና የሚናገር ከሉቃስ ወንጌል የተወሰደ ትንሽ ምሳሌ ነው።

> ደግሞም ከአሴር ወገን የሆነች የፋኑኤል ልጅ፣ ሐና የምትባል ነቢይት በዚያ ነበረች፤ እርሷም በጣም አርጅታ ነበር፤ በድንግልናዋ ካገባችው ባልዋ ጋር ሰባት ዓመት የኖረች ነበረች፤ ዕድሜዋም ሰማንያ አራት ዓመት እስኪሆናት ድረስ ቀንና ሌሊት ከቤተ መቅደስ ሳትለይ፣ በጾምና በጸሎት የምታገለግል መበለት ሆና ቆየች። በዚያኑም ጊዜ ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም መቤዠት ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ ሕፃኑ ተናገረች። ሉቃስ 2፡36-38

ይህ ለእኔ በጣም ጉልህ ምስል ነበር። ያቺ በጣም የተከበረች አሮጊት ሴት ቀንና ሌሊት ከቤተ መቅደስ አትለይም ነበር። ብዙ ጊዜዋን በጾም ታሳልፍ ነበር። ምን ነበረች? ማላጅ ነበረች። በገዛ ቤቷ ውስጥ መጸለይ ስትችል በቤተ መቅደስ የነበረችው ለምን ነበር? ሕዝቧን እየወከለች ነበር። እስራኤልን በመወከል የእስራኤል መቤዠት እንዲመጣ ወደ እግዚአብሔር እየጮኸች ነበር። አዳኙን አይታ እንድታውቀው በማድረግ እግዚአብሔር ለብዙ፣ ብዙ ዓመት ጸሎትዋ ዋጋ ሰጣት።

በአንድ በኩል የመማለድ ሕይወት ስውር ሕይወት ነው። ይህን ያህል ሕዝብ አይን ውስጥ አይገባም። ሆኖም፣ የእግዚአብሔርን እጆች ያንቀሳቅሳል።

እናንተስ? እንደ ማላጅ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስለ ማቅረብ ኃላፊነታሁን ለማሰብ ፈቃደኞች ናችሁ? በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ከእያንዳንዱ ማላጅ የማያቸው አራት መስፈርቶች አሉ። እነዚህን መስፈርቶች በጣም ግልጽ እንደ ሆኑ አስባለሁ።

ከሁሉም በፊት አንድ ማላጅ ስለ የእግዚአብሔር ጻድቅነት የተሟላ ግንዛቤ ሊኖረውና እግዚአብሔር አመፀኞችን እንደሚቀጣም የተሟላ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። እግዚአብሔር በጣም ደግ ስለ ሆነ ኃጢአትን አይቀጣም የሚል ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ ቦታ የለውም እንደዚያ የሚያስብ ሰው ማላጅ ለመሆን ብቁ አይደለም። ማላጅ ስለ ፍጹማዊ ፍትሕና ስለማይቀረው የእግዚአብሔር ፍርድ ጥርት ያለ ራእይ ሊኖረው ይገባል።

ሁለተኛ በከፍተኛ ደረጃ ስለ እግዚአብሔር ክብር የሚገደው ሰው መሆን አለበት። በምድር ላይ ታላቅ የሆነ ሕዝብ አባት እንደሚሆን ሲነግረው ሙሴ ሁለት ጊዜ አልቀበልም ያለው በዚህ ምክንያት ነበር። ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ ለአንተ ክብር አይሆንም። ለመሆኑ ባሕርያትህን በተመለከተ ግብጻዊያን ምን ይላሉ?›› አለ።

ሦስተኛ፣ እንዲህ ያለው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በጣም የጠበቀ ግንኙነት ሊኖረው እንደሚገባ አምናለሁ። ማላጅ በእግዚአብሔር ፊት መቆም



የሚችልና በፍጹም ግልጽነት ሆኖም በአክብሮት ለእርሱ መናገር የሚችል ሰው ነው።

በመጨረሻም፣ ማላጅ መሆን ቅዱስ ድፍረት ይጠይቃል። ሕይወታችሁን ለአደጋ ለማጋለጥ ፈቃደኛ መሆን አለባችሁ። እግዚአብሔር በላከው ፍርድና በሚያጠፋቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ዕጣን ይዞ ሲቆም አሮን የዚህ ዓይነት ሰው ነበር (ዘኁልቁ 16፡42-48ይመ)። እንደ ማላጅ፣ ‹‹ሞት ሊደርስብን ይችል ይሆናል፤ ግን እዚህ እቆማለሁ›› ማለት መቻል ይኖርባችኋል።

## ጸሎት

በጸሎት ሲምፎኒ ውስጥ ቀጥሎ ያለው መሣሪያ ጸሎት ነው። ጸሎት ለአንዳንድ ሰዎች ግራ የሚያጋባ ቃል ነው። ስትጸልዩ የምትጠይቁት አንድ ነገር ብቻ ነው - ምሕረትን። ብዙ ጊዜ ከምልጃ ጋር ይያያዛል።

ይህን የሚገልጹ ሁለት ክፍሎች እንመልከት። ዘካርያስ 12፡10 እስራኤል ላይ ያተኮረ ትንቢት ነው። እግዚአብሔር ሲናገር እንዲህ አለ፣ ‹‹በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የርኅራኄና የልመና መንፈስ አፈሳለሁ››።

የቃሎቹን ቅደም ተከተል ልብ አድርጉ፤ መጀመሪያ ርኅራኄ ከዚያ ልመና ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ በጸሎት ወደ ፊትህ መቅረብ እፈልጋለሁ›› የምትሉ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ደግሞ፣ ‹‹ጸጋዬን ከሰጠሁህ ትችላለህ›› ይላችኋል። በመሠረቱ ያለ እርሱ ጸጋ ዋጋ የሚሰጠው ማንኛውም ጸሎት ወደ እግዚብሔር መቅረብ አይችልም። በግዚአብሔር ጸጋ ያልተጀመረ ከሆነ ዋጋ የለውም።

ዘካርያስ 12 ላይ ያለው ቀጣዩ ቃል፣ ‹‹ወደ ወጉኝ ወደ እኔም ይመለከታሉ፤ እነርሱም ለአንድያ ልጅ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፤ ለበኩር ልጅ ምርር ተብሎ እንደሚለቀስም አምርረው ያለቅሱለታል›› ይላል።

ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለው ግንኙነት መለወጥን ያመለክታል። በንስሐ የሚመጡበትና መሲሑን የሚቀበሉበት ነጥብ ሲሆን፣ ይህ የሆነው ደግሞ በርኅራኄና በልመና መንፈስ ነበር።

እግዚአብሔር ምክንያታዊ ነው። አያችሁ፣ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ወደ እስራኤል በላከው ጊዜ፣ እስራኤል እንደ ሕዝብ ንቀውት ነበር። እግዚአብሔር

ግን ሕዝቡን ስላልናቀ መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። ግን መንፈስ ቅዱስን ከናቁ ከእንግዲህ እግዚአብሔር ማድረግ የሚችለው ሌላ ነገር አይኖርም። ያ በእግዚአብሔር ላይ የምናሳልፈው የመጨረሻ ውሳኔ ነው። ኢየሱስ፤ «ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ይቅር ይባላል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ግን ይቅር አይባልም» ብሏል(ማቴዎስ 12:31)። አሁን ይህን የምጠቅሰው በእስራኤል ያለው ሁኔታ መለወጥ በመጀመሩ ነው። የመመለስ ሂደት አለ፤ እየተንቀሳቀሰ ያለው የተገላቢጦሽ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በመጀመሪያ አይሁድ ከኢየሱስ ጋር ይጋፈጣሉ ብለው ያስባሉ። ግን እንደዚያ አይደለም! በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ይቀሰቀሳሉ፤ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ይገልጥላቸዋል። ይህ ሂደት ተጀምሯል። ይህ በጣም የሚገርም ነው፤ ምክንቱም እግዚአብሔር እየሠራ ያለው ታውረው ከነበረበት አቅጣጫ ነው። በዚህ ሁኔታ ያሉ ብዙ አይሁድ አናግሬአለሁ። የት ቦታ ንግግርን ማቆምና መንፈስ ቅዱስ እንዲጨርስ መተው እንደሚገባ ማወቅ የተወሰነ ነጥብ ይጠይቃል።

ዕብራውያን 4 ጸሎትን በተመለከተ ቀደም ሲል ተመልክተነው የነበረ ሌላ ውብ ምስል ይሰጠናል። እርግጥ ነው፤ ዕብራውያን የተጻፈው ለአይሁዳውያን አማኞች ነበር። «እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ» (ዕብራውያን 4:16)።

እግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተቀምጧል፤ ዙፋኑ ግን የጸጋ ዙፋን ነው። ወደዚያ የምንመጣው ምን በመፈለግ ነው? በሚያስፈልገን ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድንቀበል። አንድ አይነት ከባድ ችግር ውስጥ ስትገቡና ያንን በተመለከተ ምንም ማድረግ የማይቻል ሲመስላችሁ፣ «የችግር ጊዜ የመምጫ ጊዜ ነው» በማለት እግዚአብሔር ሲናገር ስሙ።

የእግዚአብሔርን ምሕረትና ጸጋ ያልተቀበሉ ሰዎች ወደ ዙፋኑ ያልመጡ ሰዎች ብቻ መሆናቸውን አምናለሁ። የገዛ ራሳችንን ችግር ወይም ጉድለት



አናይም። ራስን በማጽደቅና ሃይማኖተኝነት ታውረናል፤ የእግዚአብሔር ምሕረት በእኛ ጥረት የሚገኝ ቢሆን ኖሮ አያስፈልገንም ነበር ስንመጣ እንቀበላለን።

ትእዛዝ

የትእዛዝ መሣሪያ ወደ ልዩ አቅጣጫ ይወስደናል፤ በድፍረትና ሥልጣን ይናገራል።

ኢያሱ 10 ለመጀመር ጥሩ ቦታ ነው። ይህ ጥቅስ በውጊያ መሐል ስለ ነበር ሁኔታ ነው የሚናገረው። እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እያሸነፉ ነበር፤ ጊዜው ግን እየመሸ ነበር። እየጨለመ ከሄደ ሥራውን መጨረስ አይችሉም።

> እግዚአብሔር አሞራውያንን ለእስራኤል አሳልፎ በሰጠበት ዕለት ኢያሱ እግዚአብሔርን በእስራኤል ፊት እንዲህ አለው፤ «ፀሐይ ሆይ፣ በገባዖን ላይ ቁሚ፤ ጨረቃም ሆይ፣ በኤሎን ሸለቆ ላይ ቀጥ በይ፤ ስለዚህ ሕዝቡ ጠላቶቹን እስኪበቀል ድረስ፣ ፀሐይ ባለችበት ቆመች፤ ጨረቃም አልተንቀሳቀሰችም። ይህም በያሻር መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል። ፀሐይ በሰማዩ መካከል ቆመች፤ ለመንቀሳቀስም ሙሉ ቀን ፈጀባት። እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ እለት ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ አልነበረም። ቁጥር 12-14

ይህ ለእግዚአብሔር የቀረበ የትእዛዝ ጸሎት ነው። ሁኔታዎችና አዝማሚያዎችን በማየት ምን ማድረግ እንደሚገባ ማወቅ እንችላለን፤ ሆኖም፣ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ካልተገናኘን፣ ሁለተኛ ቅባት ካልተቀበልን ውጤት አይኖረንም፤ ለእንዲህ ዓይነቱ ጸሎት መነሳሳትም አይኖረንም።

የአዲስ ኪዳን ምሳሌ የሚሆነን ኢየሱስ የረገማት የበለስ ዛፍ ሁኔታ ነው። የዚህ ታሪክ ሁለት የወንጌል አቀራረብ አለ። የመጀመሪያው ይኸው -

> ኢየሱስም በማግስቱ ማለዳ ወደ ከተማይቱ በመመለስ ላይ ሳለ ተራበ፤ በመንገድ ዳርም አንድ የበለስ ዛፍ አይቶ ወደ እርሷ ሲሄድ ከቅጠል በስተቀር ምንም ስላላገኘባት፣ «ከእንግዲህ ፍሬ አይኑርብሽ» አላት፤ የበለሷ ዛፍ

> ወዲያውኑ ደረቀች። ደቀመዛሙርቱም የሆነውን አይተው በመደነቅ፣ የበለሷ ዛፍ እንዴት ባንዴ ልትደርቅ ቻለች?›› አሉ። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ፤ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን ተራራ፣ ‹ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ› ብትሉት እንኳ ይሆናል። እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ። ማቴዎስ 21፡18-22

እነዚህ የቀረቡ የትእዛዝ ቃሎችን በሁለት መንገድ ጥቅም ላይ እንደ ዋሉ ልብ አድርጉ። መጀመሪያው እግዚአብሔርን በተመለከተ ለነገሮች የተነገረ ነው። ሁለተኛው ነገሮችን በተመለከተ ለእግዚአብሔር የተነገረ ነው። ኢየሱስ ስለ በለስ ዛፊቱ አልጸለየም፤ ያ ጣዖት ማምለክ ይሆን ነበር። በእግዚአብሔር ቦታ ሆኖ ለበለስ ዛፊቱ ተናገረ። ይህ ጸሎት አይደለም። ምን መሆን እንዳለበት ብቻ ለበለስ ዛፊቱ ተናገረ፤ የበለስ ዛፊቱ እንደ ተባለው ሆነች።

እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሠረት በእግዚአብሔር ቦታ በመሆን (ኢየሱስ በበለስ ዛፊቱ እንዳደረገው) ለነገሮች መናገር ወይም ደግሞ በነገሮች ቦታ ሆነን ለግዚአብሔር መናገር እንችላለን፣ ይህ በተለምዶ ጸሎት የምንለው ነው።

ማርቆስ 11 ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ ተጽፏል፤ ነገር ግን እዚያ ላይ ሁሉንም ለመረዳት የሚያስችል ቁልፍ የሆነ እውነት ኢየሱስ ገልጾአል።

> በማግስቱ ጠዋት በመንገድ ሲያልፍ፣ በለሲቱ ከነሥሯ ደርቃ አዩ። ጴጥሮስ ነገሩ ትዝ አለውና ኢየሱስን፣ ‹‹መምህር ሆይ እነሆ የረገምሃት በለስ ደርቃለች›› አለው። ኢሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ‹‹በእግዚአብሐር እመኑ››፤ ማርቆስ 11፡20-22



ቃል በቃል ትርጉሙ፣ ‹‹የእግዚአብሔር እምነት ይኑራችሁ›› ነው። የትእዛዝ ጸሎት በአንደበት የሚገለጽ የእግዚአብሔር እምነት ነው፤ እግዚአብሔር ራሱ የተናገረው ያህል ሥልጣን አለው። በተወሰነ መልክም ቢሆን ይህ ቃል የተነገረውን ስእስትንፋሰ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ በእግዚአብሔር የተነገረ ቃል ነው ቢባል ያስኬዳል።

ይህ የሥልጣን ቃል በዚህ ዘመን ልንጠቀምበት እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል።

> የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይል አለው፤ ታላቅ ነገርም ያደርጋል። ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበር፤ ዝናብ እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ተኩል አልዘነበም። እንደ ገናም ጸለየ፤ ዝናብም ከሰማይ ዘነበ፤ ምድርም ፍሬዋን ሰጠች። ያዕቆብ 5፡16-18

በሌላ አነጋገር አጥብቀን ከጸለይን እናንተና እኔ እንዲሁ እናደርጋለን። ያው ኃይል ለእኛም ነው።

ቀጥሎ ያሉት ሁለት የዘመናችን ምሳሌዎች ናቸው። ምናልባት ሐዋርድ ካርተር ስለሚባል ወንድም ሰምታችሁ አታውቁ ይሆናል። ታሪኩ የጴንጠቆስጤ እንቅስቃሴ በብሪታንያ ወደ ተጀመረበት ዓመታት ወደ ኋላ ይወስደናል። ጸሐፊና በለንደን መጀመሪያውን የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ የመሠረተ ሰው ነበር።

በአንደኛው የዓለም ጦርነት በጣም ተቃዋሚ ነበር፤ በዚህም ምክንያት እንዲታሰር ተደረገ። እስር ቤቱ ቀዝቃዛና ውሃ የሚንጠባጥቡበት ክፍል ነበር። አንድ ቀን አልጋው ላይ ጋደም ብሎ እያለ ከጣራው ውሃ እየተንጠባጠበ እርሱ ላይ መረጨት ጀመረ። ጣቱን ወደዚያ በማመልከት ‹‹በኢየሱስ ስም እንድትመለስ አዝዝሃለሁ›› አለ። እንዳለውም ሆነ።

ይህኛው ደግሞ ሌላ ታሪክ ነው። በዛምቢያ አንዲት በአሥራዎቹ ዓመቶች ያለች ልጃገረድ ብስክሌት እየነዳች ስብሰባ አድርገን ወደ ነበረበት ቦታ እየመጣች ነበር። በዛምቢያ ሂያ ወይም ሠላሣ ጫማ ከፍታ ያሏቸው ብዙ ኩይሳዎች አሉ፤

እነዚህ ኩይሳዎች የእባብ መኖሪያዎች ናቸው። ወደ አንድ ኩይሳ ስትጠጋ አንድ ጥቁር ኮብራ ከጉድጓድ ወጥቶ ወደ እርሷ መጣ። በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች ብስክሌትዋ እነበረበት ቦታ ላይ ቆመች። ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሷ ላይ መጣና፣ ‹‹በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ ጉድጓድህ ተመለስ›› አለች። እባቡ ቆመና ራሱን ወደ ጉድጓዱ አደረገ፣ ግን ምንም አልተንቀሳቀሰም። ‹‹እኔ ያልኩህ ወደ ጉድጓድህ ግባ ነው›› በማለት እንደ ገና ተናገረች። ያኔ ወደ ኋላ ተመልሶ በቀጥታ ጉድጓዱ ውስጥ ገባ። ወደ ስብሰባችን ቦታ ስትደርስ እንኳ እየተንቀጠቀጠች ነበር። በዚያ ትእዛዝ የእግዚአብሔር ብርታት በድካሟ ፍጹም ሆነ።

ይህ የጸሎት መሣሪያ በተለይ አጋንንትን ለማስወጣት የኢየሱስን መመሪያ ስንከተል ተገቢ ነው። (ማርቆስ 16፣17ይመ)።

## መስጠት

የሚከተለው መሣሪያ ማለት የመስጠት ጸሎትን መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው። እንደ ልመና ጸሎት ሁሉ አንዳንዴ ለነገሮች የምንጸልይበት መንገድ ስለዚያ ጉዳይ መጸለይ ማቆም ነው።

እዚህ ላይ የምንመለከተው የመስጠትን ጸሎት ነው። የዚህ ከመዝሙር የተወሰደ ጥቅስ መጀመሪያ ክፍል መስቀል ላይ ኢየሱስ ጠቅሶት እንደ ነበር ትረዳላችሁ። ‹‹መንፈሴን እሰጣለሁ፤ እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ሆይ አንተ ተቤዠኸኝ››(መዝሙር31፡5)

አንዳንዴ ያለንበትን ሁኔታ ለጌታ ማስረከብና እኛ ከጉዳዩ እጃችንን ማውጣት በጣም የበለጠ ውሳኔ የሚሆንበት ጊዜ አለ። በዴንማርክ የሰበክሁበትን የመጀመሪያ ጊዜ አስታውሳለሁ። ዓመቱ 1947 ነበር፣ ወደዚያ የሄድኩት በራሴ ፈቃድ ነበር። የመጀመሪያዋ ባለቤቴ ሊዲያ በኢየሩሳሌም ቀርታ ነበር። በየሄድኩበት ሁሉ የእርሷ ባለቤት መሆኔን እያስተዋወቁኝ ነበር፤ ከነበራት ክፍ ያለና አስደናቂ የዳግም ልደት ልምምድ የተነሣ በእርሷ ምክንያት የዳኒሽ ሰዎች ለእኔም ጥሩ አመለካከት ነበራቸው፡



አስተርጓሚዬ የሚሆነውን የዴንማርክ ሰው ሳገኘው የምነግረውን ነገር 50 እጅ እንኳ መረዳት እንደማይችል አወቅሁ። በዚያ ሁኔታ ምን እንደማደርግ እንኳ ማሰብ አልቻልኩም፤ ይህ ተስፋ የለውም በማለት አሰብሁ። ስለሆነም በተስፋ መቁረጥ ስሜት፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ መንፈሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ›› አልኩ። እንዴት እንደ ሆነ ምንም ሐሳብ የለኝም፣ ግን በጣም ደስ የሚል የስብሰባ ጊዜ ነበርን። እኔ የተናገርኩትን በትክክል ተርጉሞ ይሁን ወይም እርሱ የፈለገውን ይናገር አላውቅም፤ ግን ውጤቱ አስደናቂ ነበር። ከሁኔታው ላይ እጄን ማንሣት ነበረብኝ። ሌላ ምንም ማድረግ የምችለው አልነበረም።

በጣም የሚታወቀው መዝሙር 37፡5 ይህን ማበረታቻ ይሰጣል፣ ‹‹መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፤ በእርሱም ታመን፤ እርሱም ያከናውንልሃል። ዕብራይስጡ መንገድህን እግዚአብሔር ላይ አንከባልለው ነው የሚለው። በምሥራቅ አፍሪካ ከተማሪዎች ጋር እሠራ በነበረ ጊዜ ነበር ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ የሆነልኝ። አንዳንዴ ሩዝ ያልቅብንና ለእራት ምንም አይኖረንም ነበር። ታዲያ እኔ፣ ትንሽዋ መኪናዬን እየነዳሁ በአቅራቢያችን ወዳለው ሰፈር እሄድና ሁለት ከረጢት ሩዝ እገዛለሁ። እንደማስታውሰው እያንዳንዳቸው ሁለት መቶ ሃያ ፓውንድ ይ መዝኑ ነበር።

በአፍሪካ በነበረው ትምህርት ቤታችን በጣም ከሚያስቸግሩን ነገሮች አንዱ ወጣቶች መማር እንደጀመሩ ወዲያውኑ ማንኛውንም የጉልበት ሥራ መሥራት ውርደት ነው የሚል አስተሳሰብ ነበር። ያ እንደዚያ እንዳልሆነ በተግባር ላሳያቸው ፈለግሁ። ሁለቱን ከረጢቶች የያዘ መኪናዬን እስከ ወጥ ቤቱ ድረስ እነዳና አንዱን ጆንያ በትከሻዬ ተሸክሜ ወጥ ቤቱ ውስጥ አገባ ነበር። በጣም የሚገርመው አንድን ኮባድ ነገር ከማውረድ ይልቅ መሸከሙ የሚቀል መሆኑ ነው። በኋላ ምስጢሩ ማንከባለል መሆኑን ተረዳሁ። በዚህ ጥቅስ እግዚአብሔር የሚለውም ይህን ነው። መንገዳችሁ በጣም ከባድ ሲሆንና ከቁጥጥራችሁ ውጪ ሲሆን፣ ወደ ጌታ አንከባሉት፤ እርሱ መፍትሔ ያገኝለታል። መስጠት አንድ ድርጊት ነው። አንድን ነገር አንዴ ከሰጣችሁ ምን ላይ ደርሶ እንደ ሆነ ለማየት ወደ ኋላ አትመለሱ። እምነት ይኑራችሁ። ገንዘባችሁን ወደ ባንክ ወስዳችሁ እንደማስቀመጥ ነው።

አንዴ ያስቀመጣችሁበትን ደረሰኝ ከተቀበላችሁ በኋላ፣ ባንኩ በገንዘባችሁ የሚያደርገውን ለማወቅ ከሰላሣ ደቂቃ በኋላ ተመልሳችሁ አትሄዱም። ለባንክ ሰጥታችሁታል። አንድን ነገር ለጌታ ከሰጣችሁ እዚያው ተውት።

ከዓመታት በፊት በአየርላንድ አንድ የስድስት ዓመት የዐጎቴ ልጅ ጥቂት ድንቾች ተክሎ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ድንቾቹ እያደጉ መሆናቸውን ለማየት በጣም ጓግቶ ስለ ነበር ደጋግሞ ወደዚያ ይሄድና ይቆፍር ነበር። በመጨረሻ ምንም ድንች አላገኘም። ብዙ ክርስቲያኖች እንደዚያ ናቸው። ድንቾች ይተክላሉ፤ እያደጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይቆፍሩዋቸዋል። አንዴ ከሰጣችሁ፣ ከዚያ መተማመን ይኖርባችኋል። እናንተ ስትተማመኑ፣ ጌታ ኃላፊነቱን ይወስዳል።

## መለየት

ቀጥሎ ያለው የጸሎት መሣሪያ መለየት ነው። ይህ ከመስጠት ጸሎት ጋር ይመሳሰላል። በሁለቱም ጊዜ የምንጸልይበትን ነገር ለጌታ እንሰጣለን፤ የመለየት ጸሎት ስናደርግ ግን የምንሰጠው ራሳችንን ነው። በመለየት ጸሎት ለአንድ ዓይነት ሥራ ወይም እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን ላመጣው ጥሪ ራሳችንን እንለያለን፤ ራሳችንን እንቀድሳለን።

ለዚህ ምሳሌ የምናገኘው ከዩሐንስ 17:19 ሲሆን፣ የኢየሱስ ሊቀ ካህናዊ ጸሎት የምንለው ክፍል ነው። ከደቀመዛሙርቱና ከአብ ጋር ስላለው ግንኙነት እየተናገረ ነበር። ‹‹እነርሱ በእውነት የተቀደሱ እንደሆኑ ራሴን ስለ እነርሱ ቀድሻለሁ›› አለ። እንደ ኢየሱስ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መለየት ከመረጥን፣ የእግዚአብሔር ሆነናል ማለት ነው።

በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነን፤ የምንፈልገውን ማድረግ አይፈቀድልንም። በዩሐንስ 10:36 ደግሞ ኢየሱስ አብ እንደ ቀደሰውና ወደ ዓለም እንደላከው ተናግሯል። አብ ኢየሱስን የቀደሰው እንዴት ነበር? መቼም ቅዱስ አላደረገውም ፤ ምክንያቱም እርሱ ቀድሞውኑ ቅዱስ ነበር። ይልቁንም ሌላ ማንም መሥራት ለማይችለው ሥራ ለየው ስለዚህም በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ ‹‹ራሴን አቀርባለሁ። ቀድሞውኑ እግዚአብሔር እኔን ለለየበት ሥራ፣ እኔም ራሴን እለያለሁ›› አለ።



ምንጊዜም ቢሆን በመቀደስ ጉዳይ የመጀመሪያው ርምጃ ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር እናንተን ላልቀደሰበት ነገር ራሳችሁን መቀደስ አትችሉም። እግዚአብሔር እናንተን ለምን ጉዳይ እንደ ለያችሁ እወቁ፣ ከዚያ በፈቃዳችሁ ምላሽ በመስጠት ያንን ለማድረግ ራሳችሁን ለዩ። እጅግ ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ለይተው አለማወቃቸው በጣም የሚገርም ነገር ነው። እግዚአብሔር ለይቶናል፤ እኛ ራሳችንን እስካልለየን ድረስ ግን ውጤታማ አይሆንም።

ይህን ለማድረግ አትገደዱም፤ በፈቃደኝነት የሚደረግ ነው። አንድ ዓይነት ኪዳን (ስዕለት) ካደረጋችሁ በኋላ እንደ ገና ለመለወጥ መጽሐፍ ቅዱስ ፈቃድ እንደማይሰጣችሁ አስታውሱ።

## ጽናት

ደቀ መዛሙርቱ በጽናት ጸሎት መሣሪያ እንዲጠቀሙ ኢየሱስ አስተምሯል።

> ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ ከእናንተ አንዱ ወዳጅ ቢኖረው በእኩለ ሌሊት ወደ እርሱ ሄዶ፣ ወዳጄ ሆይ፣ ሦስት እንጀራ አበድረኝ፤ አንድ ባልንጀራዬ ከመንገድ መጥቶብኝ የማቀርብለት ምንም ነገር የለኝምና ብሎ ለመነው እንበል። በቤት ውስጥ ያለውም፣ አታስቸግረኝ፤ በሩ ተቆልፏል፤ ልጆቼም አብረውኝ ተኝተዋል፤ ከእንግዲህ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም ይለዋልን? እላችኋለሁ፤ ወዳጁ በመሆኑ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፣ ስለ ንዝነዛው ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል። ሉቃስ 11:5-8

በሌላ አነጋገር ማንኳኳታችሁን ቀጥሉ፤ ተነሥቶ እንጀራዉን እስካልሰጣችሁ ድረስ ወዳጃችሁ እንቅልፍ እንደማያገኝ እንዲያውቅ አድርጉት ማለት ነው። ኢየሱስ እንዲህ ያለውን ጽናት ያበረታታል።

> ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ለምኑ (ቃል በቃል በመለመን ጽኑ) ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ (በመፈለግ ጽኑ) ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ (በማንኳኳት ጽኑ)

ይከፈትላችኋል፤ ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ (በመለመን የሚጸና) ይቀበላል፤ የሚፈልግም (በመፈለግ የሚጸና) ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳም (በማንኳኳት የሚጸና) ይከፍትለታል። ቁጥር9-10

ምንም እንኳ ‹‹የግንኙነት መስመሩ እንዲቀጥል ›› ለማድረግ ብዙ ጊዜ ጽናት ቢጠይቅም ይህ የጸለየበትን ነገር ከሚቀበል የልመና ጸሎት በጣም የተለየ ነው። በዚያ ዓይነቱ ጸሎት ትጸልያላችሁ፤ ትቀበላላችሁ፤ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አመሰግንሃለሁ›› ትላላችሁ። ጉዳዩ ይኸው ነው። በዚህ ዓይነቱ የጽናት ጸሎት ግን ማንኳኳታችሁን ትቀጥላላችሁ፤ በሩ እስኪከፈት ድረስ የምትፈልጉትን ነገር መለመናችሁን ትቀጥላላችሁ።

ወደ ሞዛምቢክ ሄዳ የፕሮቴስታንት ሚሽን መክፈት የፈለገች አንዲት ደቡብ አፍሪካዊት ሚሲዮናዊ አውቃለሁ። በዚያ ዘመን አገሪቱ በፖርቹጋል መንግስት ሥር በሩ ዝግ የነበረባት ካቶሊክ አገር ነበረች። ወደሚመለከተው ቢሮ ሄዳ ፈቃድ ጠየቀች። አይሆንም ተባለች። እንደ ገና ሄደች። አይሆንም ተባለች። እንደገና ሄደች። አይሆንም ተባለች ምን ያህል ጊዜ እንደ ተመላለሰች ታውቃላችሁ? ሰላሣ ሦስት ጊዜ፤ ሰላሣ ሦስተኛው ላይ ፈቃድ አገኘች። ያ መጠየቅና በመጠየቅ መጽናት ነው!

የሐዋርያት ሥራ 12 የጥንት ቤተ ክርስቲያን ስላደረገችው የጽናት ጸሎት ምሳሌ ይሰጠናል። ንጉስ ሄሮድስ የዩሐንስን ወንድም ሐዋርያው ያዕቆብን አስገድሎት ነበር። ከዚያም ጴጥሮስን አሳሰረ፤ ፋሲካ እንዳለፈ ወዲያውኑ ሊያስገድለውም እስር ቤት እንዲቆይ አደረገ። በዚሁ ጊዜ በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተክርስቲያን ለጴጥሮስ በጽናት እየጸለየች ነበር። አንዳንዴ እግዚአብሔር በአንድ ሰው ጸሎት ብቻ አይሠራም። ራሳቸውን የሰጡ አማኞች ኅብረት ጸሎት አስፈልጓል።

‹‹ጴጥሮስም በዚህ መሠረት እስር ቤት ተጣለ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ስለ እርሱ አጥብቃ ወደ እግዚአብሐር ትጸልይ ነበር›› (የሐዋርያት ሥራ 12:5)። ግን የሚለውን ቃል ልብ አድርጉ። ያ ግን የሁኔታዎችን አቅጣጫ



ለወጠ። የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ጸሎት ከእግዚአብሔር የመጣ መልአክ ጣልቃ በመግባት ጴጥሮስ ከእስር ቤት እንዲፈታ አደረገ።

በዚህ መንገድ ቤተክርስቲያን ለጴጥሮስ ያደረገችው ጸሎት መልስ አገኘ፤ እግዚአብሔር ግን ገና በንጉሥ ሄሮድስ ላይ የሚያደርገው ነገር ነብረው።

የሐዋርያት ሥራ 12 መጨረሻ ላይ ሄሮድስ ልብስ መንግስቱን ለብሶ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጠና ለጢሮስና ለሲዶና ሰዎች ንግግር እንዳደረገ ይገልጻል። ንግግሩን ሲያበቃ ሕዝቡ፣ ‹‹ይህስ የእግዚአብሔር ድምጽ እንጂ የሰው አይደለም! ›› እያሉ ጮኹ(ቁጥር22)። በገዛ ራሱ ስኬት ትዕቢት አድሮበት የሕዝቡን ሙገሳ ተቀበለ። ጽሑፉ የሚደመድመው ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር መልአክ መትቶ እንደ ገደለው በመግለጽ። ‹‹በትልም ተበልቶ ሞተ››(ቁጥር23)

አጥብቆ ወይም በጽናት የመጸለይን ውጤት እንደ ገና አያችሁ። ቃሉንና የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚቃወም ማንኛውም ነገር ተገለበጠ፤ ሄሮድስም አሳፋሪ አሟሟት ሞተ። የሄሮድስን እቅድ ያፈረሰው የመልአክ ጣልቃ መግባት እንደ ነበር አስተውሉ። በዚህ ታሪክ መሠረት መልአኩ ሁለቴ ጣልቃ እንዲገባ ያደረገው ምን ነበር? የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ነበር።

እንግዲህ ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በእውነት እየገዛ የነበረው ማን ነው? በማለት ራሳችንን እንጠይቅ። ሄሮድስ ነው ወይስ ቤተክርስቲያን? ሄሮድስ ዙፋን ላይ ተቀመጠ፤ በዚህ ታሪክ መሠረት ቤተክርስቲያን ግን በጽናት አጥብቆ በመጸለይ ገዛች የሚል ነው።

አንድን ነገር በእውነት እንደምታገኙት ካወቃችሁ መጸለይ አታቆሙም። የምታጡት ስታቆሙ ብቻ ነው።

አብዛኞቹ የጽናትና እንዲሁም የልመና ጸሎቶች አንዳንድ የፈውስ ገጽታዎችንም የሚመለከቱ በመሆናቸው እዚህ ላይ በተአምራትና በፈውስ መካከል ያለውን ልዩነት ማንሣት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። በመሠረቱ፣ ተአምራት ከፈውስም አልፈው ይሔዳሉ።

በአገልግሎቴ ከአንዴ በላይ የተፈጸሙ ምሳሌ ቀጥሎ ያለው ነው። አንድ ሰው አቲቲስ ሜዲያ ማለትም የመካከለኛው ጆሮ ክፍል መለብለብ ካለበት ልትጸልዩለትና ሊፈወስ ይችላል። ግን የሰውየው ጆሮ መካከለኛ ክፍል በኦፕራሲዮን ከተወገደ በቦታው ያለውን መካከለኛ ክፍል መፈወስ አይቻልም። ተአምር ግን መካከለኛው የጆሮ ክፍል እንደ ገና እንዲኖር ያደርጋል።

ይህ የሆነበት ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎችን አስታውሳለሁ። አንድ ጊዜ አንድ ሰው መጥቶ፣ ‹‹ለጆሮዬ ጸልይልኝ›› አለኝ። የጆሮው ችግር ምን እንደ ነበር ባለ መጠየቄ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ስለዚህ ጸለይኩለት። ከጥቂት ቀኖች በኂላ ተመልሶ መጣና፣ ‹‹ተፈውሻለሁ›› አለኝ። ‹‹ከምንድን ነው የተፈወስከው?›› በማለት ጠየቅሁት።

‹‹መካከለኛው የጆሮዬ ክፍል አልነበረም፤ አሁን ግን አለኝ። ወደ ዶክተር ሄጄ ተመረመርኩ፤ አሁን ጤነኛ ጆሮ አለኝ›› በማለት መለሰልኝ። ያ ተአምር ነው። ከፈውስም አልፎ ይሄዳል።

ልዩነቱ ይህ ነው፣ ብዙ ጊዜ ተአምር ቅጽበታዊና ብዙ ጊዜም የሚታይ ነው፤ ብዙ ጊዜ ግን ፈውስ የማይታይና አዝጋሚ ነው። አንዳንድ ሰዎች ለመፈወስ ይመጣሉ፤ ተአምር ካልተደረገ ግን ምንም የተደረገ አይመስላቸውም። ግን ፈውስ ተቀብለው ይሆናል። ይህን መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ፈውስ ተቀብላችሁ ከሆነ በአመዛኙ የሚደገፈው በሚሰጡት ምላሽ ነው።

ብዙ ጊዜ ተአምር ቀላል በሆነ እምነት ብቻ ይፈጸማል። ብዙ ተአምራት ስላሉት ሰው ማጥናት ከፈለጋችሁ ነቢዩ ኤልሳዕን ተመልከቱ። ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ ተአምራቱ የተፈጸሙት በጣም ቀላል በሆነ የእምነት ርምጃ ነበር። ለምሳሌ ከኢያሪኮ ውጪ አንድ ምንጭ ነበር፤ ውሃው በጣም መጥፎ ነበር። ጨው ውሃው ውስጥ ጣለና፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ይህን ውሃ ፈውሼዋለሁ›› አለ። መቼም ጨው ውሃን እንደማይፈውስ ሁሉም ሰው ያውቃል። ይሁን እንጂ፣ ከሁለት ሺህ ዓመት በኂላ ዛሬ ወደዚያ ምንም ብትሄዱ ውሃው እንደ ተፈወሰ ነው። ጨው ውሃውን አልፈወሰም፤



ሆኖም ተራ የሚመስል የእምነት ርምጃ ተአምራዊ የእግዚአብሔር ኃይል ወደ ውስጡ እንዲለቅ አደረገ(2 ነገሥት 2:19-22)።

በሲምፎኒያችን መሠረት የመጨረሻዎቹ ሁለት ጸሎቶች መባረክና መርገሙ ናቸው። ቀጥሎ ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመባረክ ጸሎት ሲሆን፣ ምናልባትም በጣም የምታውቁት ይሆናል።

> አሮንና ልጆቹን እንዲህ በላቸው፤ እስራኤላውያንን በምትባርኩበት ጊዜ እንዲህ በሉአቸው፤ እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ይመልስልህ ሰላሙንም ይስጥህ። ዘኁልቁ 6:23-26

እዚህ ላይ መባረክ ለምትፈልጉት ሰው የምትጸልዩዋቸው ስድስት በረከቶች ቀርበዋል፤ (1) እግዚአብሔር ይባርክህ፣ (2)ይጠብቅህ፣ (3)ፊቱን ያብራልህ፣ (4) ይራራልህ፣ (5)ፊቱንም ይመልስልህ፣ (6) ሰላሙን ይስጥህ። እነዚህ በረከቶችን በማነብበት ጊዜ ስድስት ፍጹም ቁጥር አይደለም፤ አንድ ተጨማሪ ነገር መኖር አለበት በማለት አስብ ነበር። እግዚአብሔር ይህን ቀጥሎ ባለው ቁጥር ያለውን አመለከተኝ። ‹‹በዚህ ሁኔታ ስሜን በእስራኤላውያን ላይ ያደርጋሉ፤ እኔም እባርካቸዋለሁ›› (ቁጥር27)። ይህ ሰባተኛው በረከት ነው ስሙን በላያቸው ማድረግ በረከቶቹን ፍጹም ያደርጋቸዋል።

ወላጆች ልጆቻችሁን የምትባርኩት እንዲህ ነው፡- ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ሌሎች ጉዳዮቻቸው ሲሄዱ በየዕለቱ የጌታን ስም በላያቸው አድርጉ፤ እርሱም ይጠብቃቸዋል። መባረክ መቻል ምንኛ መታደል ነው።

### መርገም

የመባረክ ሌላው ገጽታ መርገም ነው። የመርገምም ኃላፊነት እንደ ተሰጠን ብዙ ክርስቲያኖች አልተረዱም። ሆኖም፣ ይህ ማለት እናንተ በመረጣችሁ ጊዜ ጥፋት ለማድረስ ፈቃድ አላችሁ ማለት እንዳልሆነ መጀመሪያ እናገራለሁ።

ቅጠል ብቻ እንጂ ምንም ፍሬ ባልነበራት በለስ ዛፍ በኩል ኢየሱስ ማለፉን ታሪክ ወደሚናገረው ማቴዎስ 21 እንመለስ። በዚህ ዘመን ብዙ እቅዶችና

ፕሮግራሞች እንዲሁም የምናያቸው ብዙ ነገሮች ፍሬ ያለባቸው ይመስላሉ፤ ቀረብ ብላችሁ ስትመለከቱ ግን ምንም አታገኙም። ኢየሱስ ይህን በቸልታ አያልፍም። ‹‹አ ለካ ምንም ፍሬ የለም›› አላለም። ‹‹ከእንግዲህ ፍሬ አይገኝብሽ›› ነበር ያለው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በማግስቱ ጠዋት በበለስ ዛፊቱ በኩል ሲያልፍ ከስሯ ደርቃ ነበር። ደቀመዛሙርቱ በጣም ተገረሙ፤ ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው ፡-

> ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ፣ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ይህን ተራራ ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ ብትሉት እንኳ ይሆናል። ማቴዎስ 21፡21

የሁላችንም ትኩረት የተራራ መነቀል ላይ ነው፤ ኢየሱስ ግን እኛም በበለሲቱ ላይ የሆነውን ማድረግ እንደምንችል ነው የተናገረው - በለሲቱ ተረገመች።

በ1960 ዎቹ ዓመቶች በቺካጎ የነበረ አንድ ቤተክርስቲያን የአመራር አካል ነበርኩ። ቤተክርስቲያኑ አንድ ጥግ ቦታ ላይ ሲሆን ግድግዳው ከአንድ መጠጥ ቤት ጋር የተያያዘ ነበር። ያ መጠጥ ቤት የስካር ብቻ ሳይሆን፣ የሴተኛ አዳሪዎችና የዕፅ ተጠቃሚዎች ቤት ነበር።

አንድ ምሽት የጸሎት ስብሰባ ነበረን፤ እኔም መድረኩ ላይ ነበርኩ። አንዳች ነገር እኔ ላይ መጣ፤ ቆምኩና፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ይህን መጠጥ ቤት በኢየሱስ ስም እረግመዋለሁ›› አልኩ። ከዚያ ነገሩ ከአእምሮየ ወጣ።

ይህ የሆነው ጥቅምት ወር ላይ ነበር። የልደት በዓል ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ጠዋት ላይ እኔና ሲዲያ የሥልክ ጥሪ ደረሰን ከቤተክርስቲያኑ አንዲት ሴት ወዲያኛው ጫፍ ላይ ነበረች፣ ‹‹ወንድማችን ፕሪንስ ቤተ ክርስቲያኑ እየተቃጠለ ነው!›› አለችን። በዚያ ጊዜ ውጪ ያለው አየር ሁኔታ ከዜሮ በታች ሃያ ዲግሪ



ነበር። እኔና ሊዲያ ወዲያውኑ እንድንሄድ ይህን ያህል አልተሰማንም ነበር፤ ረጋ ብለን መኪናችንን እየነዳን ሄድን።

ጥቂት ራቅ ብሎ ነበልባሉ ሲነድ ማየት እንችል ነበር። ይሁን እንጂ፣ ወደዚያ ስንቀርብ ቤተክርስቲያኑ እየተቃጠለ እንዳልነበር ተረዳን፤ እየተቃጠለ የነበረው መጠጥ ቤቱ ነበር። ሆኖም ቤተ ክርስቲያኑም ከአደጋ ውጪ አልነበረም፤ ከሚችጋን ሐይቅ የሚነሣ ነፋስ ነበልባሉን በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እያመጣው ነበር። ሆኖም በብርድ እየተንቀጠቀጥኩ እዚያ ቆሜ እያለ የነፋሱ አቅጣጫ አንድ መቶ ሰማንያ ዲግሪ ተለወጠ ነበልባሉን ከቤተ ክርቲያኑ ወሰደው።

ጥቂት በነበልባሉ ጭስ ከመለብለቡ ውጪ ቤተ ክርስቲያኑ ምንም ጉዳት አልደረሰበትም፤ መጠጥ ቤቱ ግን ሙሉ በሙሉ ወደመ። የቺካጎ እሳት አደጋ ባለ ሥልጣን አንዱን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ፣ ‹‹እዚያ ላይ ካለው ሰውዬ ጋር ጥሩ ግንኙነት አላችሁ ማለት ነው›› አለው። ያ መጠጥ ቤት ለምን እንደ ተቃጠለ አውቃለሁ - ረግሜው ነበር። ያ ሁኔታ ኩራት እንዲሰማኝ እንዳላደረገ እነግራችኋለሁ። ይልቁንም አስደነገጠኝ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ስለምንም ነገር በሚገባ ማሰብ እንዳለብኝ ተረዳሁ።

ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ባለው ጸሎት እንድትጠቀሙ መንፈስ ቅዱስ ካሳሰባችሁ የእግዚአብሔርን ዓላማ ወደ ፊት እንደሚያራምድ አስባለሁ። ኢየሱስ ቸልተኛ አልነበረም። ገለልተኛም አልነበረም። ከአንድ ነገር ጋር ይሆናል ወይም ደግሞ አይሆንም፤ ማንኛውም ሰው እንደዚያ እንዲሆን ይጠብቃል፡

## በእምነት መጸለይ

ኢየሱስ፣ ‹‹ሰዎች ሳይታክቱ መጸለይ እንደሚገባቸው›› ተናገረ (ሉቃስ18፡1ይመ)። በሲምፎኒው ውስጥ ትክክለኛ ቦታችንን ለመያዝ ይህ ከትልቅ ፈተናዎች አንዱ መሆኑን እኔና ሩት መረዳታችንን አስባለሁ። ክርስቲያናዊ ባሕርይ በጸሎት መጽናት ይጠይቃል። ወደ አንድ መደብር ዕቃ ለመግዛት ስንሄድ እንደምናወጣው ያለ የዋጋ ዝርዝር ይዞ ወደ እግዚአብሔር መሄድ አይደለም። እንዲህ ያለው ጸሎት መባል አይችልም ኢየሱስ እናንተ ከመለመናችሁ በፊት

አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃል ማለቱን አስታውሱ (ማቴዎስ 6፡8ይመ)። የምትፈልጉትን ለእግዚአብሔር መንገር አያስፈልጋችሁም። ዋናው ጉዳይ የሚያስፈልጋችሁን ነገር ስትነግሩት እንደምታገኙ እርግጠኛ እስከትሆኑ ድረስ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላችሁ መሆኑ ነው።

ለአሥር ዓመት ያህል ስጸልይባቸው የነበሩ ነገሮች አሉ። አሁንም ቢሆን ገና አልሆኑም። እንደዚያ በሚሆንበት ጊዜ እየጸለያችሁ ያለው በእምነት መሆን አለመሆኑን ትረዳላችሁ። ባለ ማመን እየጸለያችሁ ከሆነ፣ ‹‹ዐሥር ዓመት ሙሉ ጸለይኩ፣ ግን ምንም የሆነ ነገር የለም›› ትላላችሁ። በእምነት እየጸለያችሁ ከሆነ፣ ‹‹መጸለይ ከጀመርኩበት ጊዜ ይልቅ አሁን አሥር ዓመት ያህል ወደ መልሱ ቀርቤአለሁ›› ትላላችሁ።

ይህ የተለያዩ መሣሪያዎች የመጫወት ፍላጎትን በእናንተ ውስጥ እንዳሳደረ ተስፋ አደርጋለሁ። መለኮታዊ የጸሎት ሲምፎኒ /ስምረት/ አካል መሆን በጣም ደስ የሚል ነው። በመሪው በመንፈስ ቅዱስ ሥር ሆናችሁ በቃሉ በተገለጸው መሠረት ከሌሎች ጋር ተስማምታችሁ ስትጸልዩ ጸሎታችሁ መልስ እንደሚያገኝ ኢየሱስ ተናግሮአል። አሁን ደግሞ ለጸሎታችን የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንዴት እንደምናውቅ የበለጠ እንማር።

For more spiritual book join our official telegram channel
https://t.me/amharicspritualbooks



# 5

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ

## የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው።

## ዕብራውያን 4፡12

በምድር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድራጊ ሰዎች እነማን ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ?›› በማለት ሰዎችን ብትጠይቁ የተለያዩ መልሶች እንደሚሰጡ አስባለሁ። ምናልባትም የፖለቲካ መሪዎችን ያስባሉ። ወይም ደግሞ ሳይንቲስቶችን ወይም የመከላከያ አዛዦችን ያስባሉ።

እነዚህ ሰዎች በእውነት ተጽእኖ አድራጊ ናቸው ብዬ አላምንም። እኔ እንደምረዳው በዚህ ዘመን በምድር ላይ በጣም ተጽእኖ አድራጊዎች የጸሎታቸውን መልስ የሚያገኙበትን መንገድ የሚያውቁ ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ እጅግ ጥበበኞች ወይም በጣም ብርቱ ሰዎች ማድረግ ከሚችሉት በላይ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ወደ ሁኔታዎቹ እንዲለቀቅ ማድረግ ስለሚችሉ ነው። በዓለማችን ማንኛውም አስደናቂ መልካም ለውጥ ለምሳሌ፣ የጨቋኝ አገሮች ያኖሩት ገደብ መፍረስ ወይም በሶቪየት ዩኒየን ውስጥ የፖለቲካ ነጻነት መስፈን የእግዚአብሔር ሕዝብ - የካህናት መንግሥት ጸሎት ውጤቶች እንጂ፣ የፖለቲከኞች ውሳኔ ውጤቶች እንዳልሆኑ አምናለሁ።

እንግዲህ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ያን ያህል ሥልጣን ከተሠጠን ያንን የማናደንቅና የማንጠቀምበት ከሆነ በእውነትም ቸልተኞች ነን ማለት ነው። እንደ ካህናት መንግስት ምድርን መግዛት የእኛ ኃላፊነት ነው። የታሪክን አካሄድ መለወጥ እንችላለን፤ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅን ማዕከል ያደረገ ነው።